# አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## ዘጠነኛ ክፍል

ትምህርት ሚኒስቴር
MINISTRY OF EDUCATION

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ ዘጠነኛ ክፍል


# አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## ዘጠነኛ ክፍል






ትምህርት ሚኒስቴር
MINISTRY OF EDUCATION

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

## ይህን መፅሐፍ በጥንቃቄ ያዝ/ያዥ

ቀጥሎ መጥሀፉን በጥንቃቄ ለመያዝ የሚረዱ አሥር ነጥቦች ቀርበዋል።

1. መፅሐፉን እንደ ፕላስቲክ ፣ ጋዜጣ ወይንም ወርቀቶች በመጠቀም ሽፍን /ሽፍኝ ፡፡
2. ምንጊዜም መፅሐፉን በንፁህ እና ደረቅ ቦታ አስቀምጥ/አስቀምጭ ፡፡
3. መፅሐፉን በምትጠቀምበት/በምትጠቀሚበት ወቅት እጆችህ/እጆችሽ ንፁህ መሆን አለባቸው ፡፡
4. በመፅሐፉን ሽፋን ላይ ወይንም በውስጥ ገፆች ውስጥ አትፃፍ/አትፃፊ ፡፡
5. ለመፅሐፉ የገፅ ማስታወሻ መያዝ ሲያስፈልግ ቁራጭ ወረቀት ተጠቀም/ተጠቀሚ ፡፡
6. ከመፅሐፉ ውስጥ ገፆችን ወይንም ስዕሎችን በፍፁም ቀደህ/ቀደሽ አታውጣ/ አታውጭ ፡፡
7. የተቀደዱ ገፆች ሲኖሩ በማጣበቂያ ወይም በፕላስተር ጠግን/ጠግኝ ፡፡
8. መፅሐፉን በቦርሳ ውስጥ ስታስገባ /ስታስገቢ ጥንቃቅ አድርግ/ አድርጊ ፡፡
9. መፅሐፉን ለሌላ ሰው በምታቀብልበት/በምታቀብይበት ወቅት ጥንቃቄ አድርግ / አድርጊ ፡፡
10. በአንድ ጊዜ ጥቂት ገጾችን ብቻ በጥንቃቄ ግለጥ/ ግለጭ ፡፡

# አማርኛ እንደ ፌዴራል ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## ዘጠነኛ ክፍል

**አዘጋጆች ፡**

ጥበቡ ሽቴ (ፒ.ኤች.ዲ)

ማንያስዉ አባተ (ፒ.ኤች.ዲ)

**አርታኢዎች ፡**

ታደሠ ሲባሞ (ፒ.ኤች.ዲ)

ጌታቸዉ አዱኛ (ፒ.ኤች.ዲ)

**ሰዓሊ ፡**

ታደሰ ደኸደሰ (ኤም.ኤስ.ሲ)

**ዲዛይነር ፡**

አጥናፉ ዓለሙ (ኤም.ኤስ.ሲ)

**ገምጋሚዎች፡**

ሙኮንን አስማማው (ኤም.ኤ)

ግሩም ጥበቡ (ኤም.ኤ)

ፍሬሕይወት አሰፋ (ኤም.ኤ)

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

ሃዋሳ ዩኒቨርስቲ

# መግቢያ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎች አራቱን የቋንቋ ክሂሎች እና ሁለቱን የዕውቀት ዘርፎች ማዕከል በማድረግ የሚዘጋጅ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መፅሐፍ፣ የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብ እና የመፃፍ ክሂሎች በተደጋጋሚ በማስተማር ክሂላቸው እንዲሻሻል፤ እንዲሁም የስነልሳን እና የስነፅሑፍ ዘርፍ ዕውቀቶችንም በአግባቡ እንዲገነዘቧቸው በሚያስችል መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡ ከእነዚህ ክሂሎችና ዕውቀቶች በተጨማሪ የቃላት ትምህርትም ራሱን ችሎ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ይህም ከዚህ በፊት ከነበሩት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ለየት ያደርገዋል፡፡ እነዚህ አጠቃላይ ዓላማዎችም በመርሃ ትምህርቱ በግልፅ ተቀምጠዋል፡፡

የትምህርቱን አጠቃላይ ዓላማ ከግብ ለማድረስ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥኑ ሃያ ምንባቦች የቀረቡ ሲሆን፤ አስሩ ምንባቦች የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር፤ አስሩ ደግሞ የማንበብ ክሂልን ለማስተማር የተዘጋጁ ናቸው፡፡ የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር የተዘጋጁት ፅሁፎች የሚገኙት በመምህሩ መምሪያ መፅሐፍ ውስጥ ነው፡፡ የምንባቦቹ ዓላማዎች የሚያጠነጥኑት በዋናነት የማዳመጥንና የማንበብን ክሂል በማስተማር ላይ ነው፡፡ ነገር ግን እግረመንገዳቸውን ከምንባቦቹ ይዘት የሚማሩት ዕውቀት ይኖራል፡፡ በመሆኑም ምንባቦቹ በአገር በቀል ዕውቀት፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በፆታ ተኮር ትምህርት፣ በሱስ አስከፊነት፣ ወቅትና ተፈጥሮ፣ ብዝሃነት፣ የግብር ጥቅም፣ አርበኝነት፣ ቱሪዝምና ቅርስ እና የመሳሰሉት ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡

መፅሐፉ የተደራጀው ተፈጥሯዊ የቋንቋ ለመዳ ሂደትን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ አደረጃጀቱም፡-

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

ክል ሁለት፡-   ንግግር

ክፍል ሦሠት፡- ንባብ

ክፍል አራት፡-  ቃላት

ክፍል አምስት፡  ጽህፈት

ክፍል ስድስት፡  ሰዋስው

እነዚህ ክፍለ ትምህርቶች በየምዕራፉ እኩል ትኩረት የተሰጣቸው ሲሆን በተቻለ መጠን ሳቢ እና አሳታፊ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል፡፡ በየምዕራፉ መጀመሪያ ላይም የሚጠበቁ ውጤቶች በተማሪው መፅሐፍ የተሰጡ በመሆኑ፤ ተማሪዎች አስቀድመው ምን መማር እንዳለባቸው ይጠቁማል፡፡ ይህም የመማር ሂደቱን ግልፅ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

# ማውጫ

ይዘት ገጽ


ምዕራፍ አንድ: ባህላዊ ሽምግልና ....................................................1

ምዕራፍ ሁለት: ሥርዓተ ፆታ ....................................................11

ምዕራፍ ሶስት: ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ....................................................21

ምዕራፍ አራት: ወረርሽኝ ....................................................32

ምዕራፍ አምስት: አካታችነት ....................................................41

ምዕራፍ ስድስት: አካባቢ እና የአየር ንብረት ለውጥ ....................................................50

ምዕራፍ ሰባት: በልዩነት ውስጥ አንድነት ....................................................60

ምዕራፍ ስምንት: የግብር ጥቅም ....................................................72

ምዕራፍ ዘጠኝ: ልቦለድ ....................................................80

ምዕራፍ አስር: አርበኝነት ....................................................95

አባሪ ....................................................104

# ምዕራፍ አንድ: ባህላዊ ሽምግልና

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች! በዚህ ምዕራፍ የቀረበውን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- አዳምጣችሁ የምንባቡን ጭብጥ ትናገራላችሁ::
- ምንባቡን አንብባችሁ ዝርዝር መረጃዎችን በፅሑፍ ትዘረዝራላችሁ::
- በቀረበው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ንግግር ታደርጋላችሁ::
- አንብባችሁ የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ ታብራራላችሁ::
- በምንባቡ መሰረት ስለ ባህላዊ የሽምግልና  ሂደት ትጽፋላችሁ::
- በምንባቡ ውስጥ ላሉ አዳዲስ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ትሰጣላችሁ::
- በተሰጣችሁ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ተመስርታችሁ አንቀፅ ትጽፋላችሁ::
- ነጠላ ቁጥር ስሞችን ወደ ብዙ ቁጥር ትቀይራላችሁ::
- ከአረፍተ ነገር ውስጥ የስም ገላጮችን ትለያላችሁ::

## ክፍል አንድ: ማዳመጥ

### የአፋር ባህላዊ የህግ ሥርዓት

መምህራችሁ “የአፋር ባህላዊ የህግ ሥርዓት“ በሚል ርዕስ አጭር ፅሑፍ ያነቡላችኋል፡፡ እናንተም እያዳመጣችሁ ዋና ዋና ሀሳቦችን በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ፃፉ፡፡ በመቀጠልም የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በቃላችሁ መልሱ፡፡ ከዚያ በፊት ግን ከታች በተሰጡት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎቸ ላይ በቡድን ሆናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ መልሶቹን ለመምህራችሁ ተናገሩ::

#### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት (የሽምግልና ስርዓት) አለ? ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት

   ለህብረተሰቡ ምን ምን ጠቀሜታዎችን እንደሚሰጥ ለመምህራችሁ ተናገሩ::
2. የመጀመሪያው የሰው ልጅ ዘር የተገኘው የት አካባቢ ይመስላችኋል?



ሥዕል 1 ፡ የአፋር ህዝብ ልዩ ልዩ የማህበረሰብ ክፍሎች

## ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

ሀ. ከኢትዮጵያ ውጭ የአፋር ህዝብ የሚገኝባቸውን ሀገሮች ዘርዝሩ፡፡

ለ. የአፋር ህዝብ በአፍሪካ የት ሀገር ይገኛል?

ሐ. የአፋር ህዝብ የዘር ግንድ ምን ይባላል? ከማን ከማን ጋር ይዛመዳል?

መ. በምንባቡ ውስጥ የአፋር ባህላዊ ህግ በዓለም ላይ የመጀመሪያው ባህላዊ ህግ ሳይሆን አይቀርም የተባለው ለምንድን ነው?

ሠ. ህግ የተፈጠረው ከሰዎች ስብስብ መፈጠር ጋር መሆኑን የሚያስረዳው ምንድን ነው?

ረ. የአፋር ክልል ከሚታወቅባቸው ነገሮች መካከል ሁለቱን ተናገሩ፡፡

፪. በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን የተጓደሉ ሀሳቦች አሟልታችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. አፋር፣ ሶማሌና ኦሮሞ በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ የ ____________ ህዝቦች አካል ናቸው፡፡

ለ. የአፋር ህዝብ ራሱን የሚያስተዳድርበት የሱልጣኔት፣ የጎሳና የወጣት የተባሉ ባህላዊ __________ እና ____________ ዘርፎች አሏቸው፡፡

ሐ. የአፋር ባህላዊ የፍትህ ሥርዓት ______________ ይባላል፡፡

መ. የአፋር ህዝብ የ_____________፣ የ_____________ እና የ_____________የተባሉ ባህላዊ አደረጃጀቶች አሉት፡፡

## ክፍል ሁለት፡ ንግግር

ተማሪዎች! በአካባቢያችሁ ከሚገኙ ባህላዊ የሽምግልና ስርዓቶች መካከል አንዱን በመምረጥ መረጃ ከሰበሰባችሁ በኋላ በክፍል ውስጥ በንግግር አቅርቡ፡፡ ወይም በቡድን ሆናችሁ አተገባበሩን በድራማ መልክ አሳዩ፡፡

## ክፍል ሦስት፡ ንባብ

### ባህላዊ ሽምግልና

ከዚህ በታች አንብቦ መረዳትን ለማስተማር የሚያገለግል “ባህላዊ ሽምግልና” በሚል ርዕስ የቀረበ ምንባብ አለ፡፡ እናንተም ድምፃችሁን ሳታሰሙ ካነበባችሁ በኋላ ከታች የተሰጡትን የድህረ ንባብ ጥያቄዎች መልሱ፡፡ ከዚያ በፊት ግን ከዚህ በፊት ያላችሁን ዕውቀት በመጠቀም የቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን መልሱ፡፡

## የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

- ባህላዊ ሽምግልና ምንድን ነው?
- በምትኖሩበት አካባቢ በግለሰቦች መካከል አለመግባበት ተፈጥሮ  በሽምግልና ሲፈታ አይታችሁ ታውቃላችሁ? ገጠመኛችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

ባህላዊ ሽምግልና በረዥም ዘመናት የኅብረተሰብ የኑሮ ሂደት ውስጥ ተፈጥሮ እስከ ዛሬ የቆየ፤ወደፊትም እየተሻሻለና እየዳበረ የሚሄድ ባህላዊ ተቋም ነው፡፡ ባህላዊ ሽምግልና ከትውልድ ወደ ትውልድ ያለማቋረጥ የሚተላለፍ እሴት ነው፡፡

ባህላዊ ሽምግልና ዓላማ፣ መርሆ፣ አካሄድና ደረጃ ያለው ሥርዓት ነው፡፡ ባህላዊ ሽምግልና ከቦታ ቦታ የሚለያይ ሲሆን በዓላማውና በግቡ ይመሳሰላል፡፡ መርሆዎቹም እኩልነት፣ ፍትሕ፣ ሚዛናዊነት፣ እውነት፣ ሰብአዊነት፣ ወዘተ…ናቸው፡፡ ዓላማው ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች በተለያዩ ደረጃዎች የሚከሰቱ የግጭት ዓይነቶችን በመፍታት ሰላምና ደህንነትን በማስጠበቅ የማኅበረሰብን ህልውና ማረጋገጥ ነው፡፡

ግጭት በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ሊከሰት ይችላል፡፡ ሽምግልና የሚከሰቱ ግጭቶችን በመፍታት ወደ ተለመደው ሰላማዊ ኑሮ ለመመለስ ጥረት የሚያደረግ ሂደት ነው እንጂ 'ግጭትን ለማስወገድ' የሚከናወን ተግባር አይደለም፡፡ በሽምግልና ቀላልና ከባድ ግጭቶች ይፈታሉ፡፡ በሽምግልና ከሚፈቱት ግጭቶች መካከል ከሀገር ሉዓላዊነት እና ከሕዝብ ሕልውና አንስቶ በተዋረድ በማኅበረሰቦች፣ በማኅበረሰባዊ ቡድኖች፣ በግለሰቦችና በቤተሰብ መካከል የሚፈጠሩትን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

የሽምግልና ሥራ አንድም በራስ ተነሳሽነትና ፈቃደኛነት ኃላፊነት በመውሰድ ወይም በግጭቱ ባለቤቶች በኩል የሚቀርብ የእርቀ-ሰላም ጥያቄን ተከትሎ የሚከናወን ከፍተኛ ዋጋ ያለው ነፃ አገልግሎት ነው፡፡ ባህላዊ ሽምግልና በሀገራችን በሚገኙ በርካታ ማኅበረሰቦች ዘንድ የእውቀትና የግጭት አፈታት ጥበብ የሚታይበት በሚዛናዊነት  የሚከናወን ተግባር ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ነው "ሰማይ ተቀደደ ቢሉት፤ ሽማግሌ ይሰፋዋል!" የሚባለው፡፡ ይህም "ሽማግሌን የሚያቅተው ነገር የለም" እንደ ማለት ነው፡፡ ሽማግሌም በዚህ ከአድልኦ ነፃ በሆነ ተግባሩ በማህበረሰቡ አባላት ቅቡልነት የሚያገኝ ሲሆን፣ አክብሮትና ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡ በመሆኑም በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ግጭት ሲከሰት የመፍቻው ቁልፍ የሚገኘው በሽማግሌዎች እጅ ነው ማለት ነው፡፡

የሽምግልና ተግባር በዘፈቀደ የሚካሄድ አይደለም፡፡ ለምሳሌ የግጭቱ ዓይነት ሀገራዊ ጉዳይ ከሆነ በሽምግልናው የሚሳተፉ ሽማግሌዎች ደረጃና ብቃት ከሌሎች ግጭቶች የመመዘኛ መስፈርት ይለያል፡፡ ምክንያቱም የችግሩ ባሕርይና ደረጃ የሽማግሌዎችን ብቃትና ደረጃ ስለሚወስን ነው፡፡ በመሆኑም ለሽምግልናው የሚመረጡት በሀገር አቀፍ ደረጃ አክብሮት፤ ታዋቂነትና ተሰሚነት ያላቸው የሃይማኖት አባቶችና ሽማግሌዎች ናቸው፡፡ ሂደቱም የሀገር ጉዳይ በመሆኑ ዜናች በጉጉትና በአንክሮ ከመመልከታቸውም በላይ ሀገራዊ ፋይዳውም እጅግ በጣም ከፍተኛ ይሆናል፡፡

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

- የሽምግልና ሂደት እንዴት የሚጀመር ይመስላችኋል?
- ሁለቱ ተቀናቃኝ ወገኖች ጉዳያቸውን ለሽምግልና እንዴት ሊያቀርቡ እንደሚችሉ ገምቱ፡፡

ሽምግልና የሚያልፍባቸው የራሱ ሂደቶች አሉት፡፡ የመጀመሪያው የግጭቱ ቅድመ ምርመራና ትንበያ ነው፡፡ ይህ ማለት በግጭቱ ተዋንያን ማንነት፣ የግጭት ዓይነት፣ ምክንያት፣ ክብደትና አጣዳፊነት፣…ላይ ምርመራ በማድረግ ቀጥሎ መከናወን ወደሚኖርበት ተግባር ማምራት የሚያስችል እርምጃ ነው፡፡

ሁለተኛው ሥራ የእርቅ እሽታን ማግኘት ይሆናል፡፡ የእርቅ እሽታን ከሁለቱም ባላጋራዎች ለማግኘት አንድም በራሳቸው ተነሳሽነት ወይም ችግሩ በሰላም እንዲፈታ የሚፈልግ ወገን በሚልከው መልዕክተኛ ወይም በግራ ቀኙም ተቀባይነትና ተሰሚነት ያላቸው የሀገር ሽማግሌዎች የሚያደርጉት ጥረት ነው፡፡ እንደግጭቱ ክብደት ሂደቱ ጊዜና ድካምን ሊጠይቅ ስለሚችል እሽታን ለማግኘት ባለመታከትና ባለመሰልቸት በጥበብና በትዕግሥት መሥራትን ይጠይቃል፡፡

በሦስተኛ ደረጃ የሚከናወነው፤ በሁለቱ ወገኖች ፍላጎትና ስምምነት አስታራቂ ሽማግሌዎችን የመምረጥ ተግባር ነው፡፡ አስታራቂ ሽማግሌዎችን የመምረጡ ሂደት በሁለቱ ወገኖች ነፃ ፍላጎት ላይ የሚመሠረት በመሆኑ የሁለቱን ወገኖች እሽታ ለማረጋገጥ የደከሙትን ሽማግሌዎች ሊጨምርም ላይጨምርም ይችላል፡፡

አራተኛው ደረጃ የሽማግሌ ዳኛ መምረጥ፣ ቃለ-መሀላ የመፈጸምና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሁለቱም ወገኖች ነገረ-ፈጅ ማቆምን ይጨምራል፡፡ ሽምግልናውን የሚመራ ዳኛ የሚመረጠው ሽምግልናውን እንዲመሩ ከተመረጡት ሽማግሌዎች መካከል ሲሆን የሚመርጡትም ሽማግሌዎቹ ናቸው፡፡ በሽምግልና ዳኝነት ለመመረጥ መመዘኛ ነጥቦች ተደርገው የሚወሰዱትም በሁለቱ ወገኖች የሚቀርቡ ስሞታዎችን ከልብ የሚያዳምጥ፤ ከአድልኦ ነፃ የሆነ፣ በቅደም - ተከተል መልሶ ማስደመጥና የሽምግልና ሂደቱን ሥነ-ሥርዓት በተሻለ ሁኔታ የመምራት ልምድና ክህሎት ያለው መሆኑና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ በሀገራችን ሰዎች ጉዳያቸው ወደ ሽምግልና ሲቀርብ ከሽምግልና ዳኝነት ላይወጡ ቃል ይገባሉ፡፡ ይህ የሚፈፀመው ባላጋራዎቹ እርቀ-ሰላም ለማውረድ ከልብ መቅረባቸውን ለማረጋገጥ ነው፡፡ በመሆኑም የቃል ኪዳን ሥነሥርዓቱ እንደ ቅድመ- ሁኔታ የሚወሰድ ትልቅ ጉዳይ ስለሆነ፤ በሽማግሌ ፊት ሳያረጋግጡ 'ደረሰብኝ' የሚሉትን በደል በቀጥታ ወደማቅረብ አይራመዱም፡፡

ይህ ከተፈፀመ በኋላ፣ ባላጋራዎቹ በየተራ እየተጠሩ ከሽማግሌዎቹ ፊት ቀርበው በደላቸውን ያለፍርሃት እንዲናገሩ ይደረጋል፡፡ በተለይ ግጭቱ ክብደት ካለው ሁለቱ ወገኖች ተራርቀው መቀመጥ አለባቸው፡፡ ሽማግሌዎች ከተቀመጡበት ቦታም እንደዚሁ ርቀው መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ የሚደረግበት ምክንያትም አንዱ ወገን ከሽማግሌ ፊት ቀርቦ የሚናገረው ንግግር ሌላውን ወገን ለበቀል በማነሳሳት ሂደቱን እንዳያደናቅፍ በማሰብ ነው፡፡ በመሆኑም የአንደኛውን ወገን ድምፅ ተቀናቃኝ ወገን በትክክል

እንዲረዳ የሚደረገው በሽማግሌዎች ብስለትና ጥንቃቄ በተሞላበት ሚዛናዊ አገላለጽ ነው፡፡ ስለዚህ ለእርቅ የቀረቡ ወገኖች ሃሳባቸውን ስሜታቸውን በመቆጣጠር በሰከነ፤ በተረጋጋ፣ ተአማኒነትና ጨዋነት በተሞላበት ሁኔታ መግለጽ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ሽምግልና ጥበብ ነውና፡፡

(ባይለየኝ ጣሰው፣ የሽምግልና ባህላችን፣ 2012፤ ለማስተማር እንዲያመች ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡)

## ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ ሐሳብ መሠረት በቡድን ተወያይታችሁ በቃል መልሱ፡፡

1. ባህላዊ ሽምግልና ምን ምን ባህሪያት አሉት?
2. የባህላዊ ሽምግልና መርሆዎችን ዘርዝሩ፡፡
3. ግጭት በሁሉም አካባቢዎች ሊከሰት ይችላል? ለምን?
4. ባህላዊ ሽምግልና ከፍተኛ ዋጋ አለው፤ የተባለው ለምንድን ነው?
5. “ሰማይ ተቀደደ ቢሉት፤ ሽማግሌ ይሰፈዋል፡፡” የሚለው አባባል ምን ለማለት የቀረበ ነው?
6. ለሽምግልና የሚመረጡ ሰዎች ምን ምን ባህሪያትን የሚያሟሉ ናቸው?
7. ሽምግልና የሚያልፍባቸውን ሂደቶች ዘርዝሩ፡፡
8. በሽምግልና ወቅት ባላጋራዎች ተራርቀው የሚቀመጡት ለምንድን ነው?
9. በሽምግልና ወቅት ሁለቱ ባላጋራዎች በሽማግሌዎች ፊት ቃል የሚገቡት ለምንድን ነው?
10. በአሁን ዘመን ባህላዊ ሽምግልና የሚጠቅም ተግባር ነው ብላችሁ ትቀበላላችሁ? ለምን?

## ክፍል አራት፡ ቃላት

ሀ. ቀጥለው ለቀረቡት ቃላት በምንባቡ መሠረት አገባባዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. ሂደት
2. መርሆ
3. ግብ
4. ሉዓላዊነት
5. ተዋረድ
6. ቅቡልነት
7. ትንበያ
8. ቃለ መሐላ
9. ነገረ ፈጅ
10. ስሞታ

፪. ከዚህ በታች በ“ሀ” ሥር ለቀረቡ ቃላትና ሐረጋት በ“ለ” ሥር ከቀረቡት መካከል ተቃራኒ የሚሆነውን ፍች በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. እሽታ | ሀ. ወዳጅ |
| 2. አንክሮ | ለ. ሚዛናዊነት |
| 3. እርቅ | ሐ. ይቅርታ |
| 4. ባላጋራ | መ. የሚቻለው |
| 5. አድልኦ | ሠ. እምቢታ |
| 6. በቀል | ረ. የሚጠፋ |
| 7. የሚተላለፍ | ሰ. ክህሎት |
| 8. የሚያቅተው | ሸ. ቸልታ |
| 9. ፋይዳ | ቀ. ምስጋና |
| 10. የሚከሰት | በ. ጠብ |
| | ተ. ጉዳት |
| | ቸ. ብክነት |
| | ነ. የሚቋረጥ |

## ክፍል አምስት፡ ጽሕፈት

፭. የምንባቡን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ከዚህ በታች ከተሰጡት ቃላት መካከል እየመረጣችሁ በአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ የሚገኙትን ክፍት ቦታዎች በጽሑፍ አሟሉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ጥበብ | እሽታን | ሊጨምርም |
| ፈቃደኛነት | ፍላጎትበመፍታት | ሰላማዊ |
| ያለማቋረጥ | በዘፈቀደ | ሂደቶች |

1. ባህላዊ ሽምግልና ከትውልድ ወደ ትውልድ __________ የሚተላለፍ ሂደት ነው፡፡
2. ባህላዊ ሽምግልና በተለያዩ ደረጃዎች የሚከሰቱ የግጭት ዓይነቶችን__________ሰላምና ደህንነትን በማስጠበቅ የማኅበረሰብን ህልውና ማረጋገጥ ነው፡፡
3. ሽምግልና የሚከሰቱ ግጭቶችን በመፍታት ወደ ተለመደው__________ኑሮ ለመመለስ የሚደረግ ሂደት ነው፡፡

4. የሽምግልና ሥራ አንድም በራስ ተነሳሽነትና__________ኃላፊነት በመውሰድ ወይም በግጭቱ ባለቤቶች በኩል የሚቀርብ የእርቀ-ሰላም ጥያቄን ተከትሎ የሚከናወን ከፍተኛ ዋጋ ያለው ነፃ አገልግሎት ነው፡፡
5. ባህላዊ ሽምግልና በሀገራችን በሚገኙ በርካታ ማኅበረሰቦች ዘንድ የእውቀትና የግጭት አፈታት __________የሚታይበት በሚዛናዊነት የሚከናወን ተግባር ነው፡፡
6. የሽምግልና ተግባር__________የሚካሄድ አይደለም፡፡
7. ሽምግልና የሚያልፍባቸው የራሱ__________አሉት፡፡
8. በሽምግልና እንደግጭቱ ክብደት ሂደቱ ጊዜና ድካምን ሊጠይቅ ስለሚችል__________ለማግኘት ባለመታከትና ባለመሰልቸት በጥበብና በትዕግሥት መሥራትን ይጠይቃል፡፡
9. አስታራቂ ሽማግሌዎችን የመምረጡ ሂደት በሁለቱ ወገኖች ነፃ__________ላይ የሚመሠረት በመሆኑ የሁለቱን ወገኖች እሽታ ለማረጋገጥ የደከሙትን ሽማግሌዎች__________ላይጨምርም ይችላል፡፡

## ክፍል ስድስት፡ ሰዋስው

**፩. በምሳሌው መሰረት ከዚህ በታች የቀረቡትን ነጠላ ስሞች ወደ ብዙ ቁጥር ስሞች ቀይሩ፡፡**

ምሳሌ

ፈረስ-ኦች ⇒ ፈረሶች

ቋንቋ-ዎች ⇒ ቋንቋዎች

ሀ. አንቀጽ

ለ. ሰው

ሐ. ዘመን

መ. ፅሁፍ

ሠ. ድምፅ

ረ. ከተማ

ሰ. ነጋዴ

ሸ. ሽማግሌ

ቀ. መንገድ

በ. ሴት

**፪. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ተዋቃሬ ሆነው የሚገኙትን የስም ገላጮች እና ተገላጭ ስሞች ለይታችሁ ፃፉ፡፡**

ምሳሌ፡- ሀ. ኢትዮጵያ **ትልቅ ግድብ** እየገነባች ነው፡፡

የስም ገላጭ ፡- ትልቅ

ተገላጭ ስም፡- ግድብ

ለ. ተማሪዎች **ጥሩ ስነምግባር** ሊኖራቸው ይገባል፡፡

የስም ገላጭ፡- ጥሩ

ተገላጭ ስም፡- ስነምግባር

ሐ. ተማሪዋ **ረጅም ቀሚስ** መልበስ ትወዳለች፡፡

መ. ቱሉ **አዲስ መኪና** ገዛ፡፡

ሠ. ግመል የሚኖረው **በረሃማ አካባቢ** ነው፡፡

ረ. ዋልያ የኢትዮጵያ **ብርቅዬ እንስሳ** ነው፡፡

ሰ. ደራርቱ ቱሉ የሀገራችን **አንጋፋ አትሌት** ነች፡፡

ሸ. ጫት መቃም **ጎጂ ልማድ** ነው፡፡

ቀ. ከእናትና አባት **ጠቃሚ ምክር** ይገኛል፡፡



## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የማዳመጥና የንግግር ክሂሎችን ለማስተማር የቀረበው "የአፋር ባህልዊ የህግ ሥርዓት" የሚል ፅሑፍ ነው፡፡ ከፅሑፉም የአፋር ህዝብ የራሱ የሆነ ባህላዊ የህግ ሥርዓት ያለው መሆኑን፣ የአፋር ህዝብ በምስራቅ አፍሪካ ከሚገኙ ህዝቦች መካከል አንዱ መሆኑን፣ የመጀመሪያው የሰው ዘር ቅሪት አካል እንደሆነች የምትታመነው ሉሲ (ድንቅነሽ) የተገኘቸው በአፋር ክልል መሆኑንና ሌሎችንም እውነታዎች ተረድተናል፡፡ ካዳመጥነው ምንባብ የወጡ ልዩ ልዩ መረጃዎችን የሚያነሱ ጥያቄዎችንም ሰርተናል፡፡

"የአፋር ባህልዊ የህግ ሥርዓት" የሚለውን ጽሑፍ መነሻ በማድረግ፤ ተማሪዎች በየአካባቢያቸው ስለሚገኙ ልዩ ልዩ ባህላዊ የህግ ስርዓቶች መረጃ በመሰብሰብ ንግግር ተደርጓል፡፡

የንባብ ክሂልን ለማስተማር የቀረበው ጽሑፍ የአገር በቀል ዕውቀት አንድ አካል በሆነው "ባህላዊ ሽምግልና" ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ከቀረበው ጽሑፍ፣ ባህላዊ ሽምግልና ረጅም እድሜን ያስቆጠረ ሀገር በቀል እሴት መሆኑን፤ ከቦታ ቦታ የሚለያይ መሆኑን፤ እኩልነት፣ ፍትህ፣ ሚዛናዊነት፣ እውነት፣ ሰብዓዊነት፣ ወዘተ. በተሰኙ መርሆዎች ላይ የተመሰረተ መሆኑን፣ ተገንዝበዋል፡፡ በተጨማሪም የባህላዊ ሽምግልና ዋና ተግባር ግጭቶችን በመፍታት በልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ሰላማዊ ኑሮ እንዲሰፍን ማድረግ መሆኑን ለማወቅ ችለናል፡፡

ባህላዊ ሽምግልና ከሚለው ምንባብ የወጡ ቃላት፣ ለቃላት ማስተማሪያነት ቀርበዋል። ቃላት አገባባዊ እና ተቃራኒ ፍችዎች ያሏቸው መሆኑን፣ ለቃላት አገባባዊ ፍች የምንሰጠው አብረዋቸው ከተሰለፉት ቃላት አንፃር መሆኑን፣ ተቃራኒ ፍች የምንሰጠው ግን የቃላትን መዝገበ ቃላዊ ፍች መሰረት በማድረግ መሆኑን ተምረናል።

ሰዋስው በሚለው ሥር የቀረበው "ቁጥር" እና "የስም ገላጭ" የተሰኙ ሁለት ርዕሰ-ጉዳዮች ናቸው። ቁጥር ብዙነትን ወይም ነጠላነትን የሚያመለክት ሰዋስዋዊ ተግባር መሆኑን፣ በአማርኛ የብዙ ቁጥር አመልካች ቅጥያ /-ኦች/ የተባለው ቅጥያ መሆኑን፣ ስሞች /-ኦች/ የተባለውን ቅጥያ ካላስቀጠሉ ነጠላ ቁጥር ስሞች መሆናቸውን፣ ለመረዳት ችለናል። ለምሳሌ:- በግ፣ ፍየል፣ ሰው፣ ዶሮ፣ ቤት፣ ወዘተ. ነጠላ ቁጥር ስሞች ናቸው። የስም ገላጮች (ቅጽሎች) ከስም በፊት እየገቡ ስለስሙ ልዩልዩ ባህሪዎች የሚገልፁ መሆኑንም ተረድተናል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የአፋር ባሃላዊ የህግ ሥርዓት ምን ይባላል
2. የባህላዊ ሽምግልና መገለጫዎች ምን ምን ናቸው
3. ትንበያ፣ ቃለ መሀላ፣ ነገረ ፈጅ በሚሉት ቃላት አረፍተነገር መስርታችሁ ትጉማቸውን አሳዩ።
4. ከታች የተሰጡትን ስሞች ነጠላ ቁጥ እና ብዙ ቁጥር በማለት መድቧቸው።

| | | |
|---|---|---|
| ከተሞች | ሽማግሌ | ተማሪዎች |
| ነጋዴ | ፈረሶች | ጥበብ |

## ክፍል ሰባት:- የግንዛቤ ማመሳከፊያ ነጥቦች

ከዚህ በታች በምዕራፉ የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች ምን ያህል እንደተረዳችኋቸው ለማረጋገጥ የሚረዱ ማመሳከፊያ ነጥቦች ተዘርዝረዋል። በመሆኑም ዝርዝሮቹን በጥንቃቄ በማንበብ፣ ተረድታችኋቸው ከሆነ፣ ከፊትለፊታቸው ባለው ሳጥን ውስጥ የ(V) ምልክት በማድረግ አረጋግጡ። ያልተረዳችሁት ወይም የሚያጠራጥራችሁ ከሆነ ግን በሳጥኑ ውስጥ የ (?) ምልክት በማድረግ ያልተረዳችኋቸውን ነጥቦች ደጋግማችሁ ከልሱ።

| ተ.ቁ | ማመሳከሪያ ነጥብ | (√) | (?) |
|---|---|---|---|
| 1 | ካዳመጥኩት ፅሑፍ ጠቃሚ ማስታወሻ ይዣለሁ። | | |
| 2 | ፅሑፉን ተረድቼ ጥያቄዎችን በትክክል መልሻለሁ። | | |
| 3 | በሥርዓት ንግግር አድርጌአለሁ። | | |
| 4 | ምንባቡን አንብቤ መልዕክቱን ተረድቻለሁ። | | |

| ተ.ቁ | ማመሳከሪያ ነጥብ | (√) | (?) |
|---|---|---|---|
| 5 | ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ሰጥቻለሁ:: | | |
| 6 | ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ሰጥቻለሁ:: | | |
| 7 | አንቀፅ በትክክል ፅፌያለሁ:: | | |
| 8 | ነጠላ ቁጥር ስሞችን ወደ ብዙ ቁጥር ቀይሬያለሁ:: | | |
| 9 | ብዙ ቁጥር አመልካች ቅጥያዎችን ለይቻለሁ:: | | |
| 10 | የስም ገላጮችን ለይቻለሁ:: | | |

# ምዕራፍ ሁለት፡ ሥርዓተ ፆታ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ የቀረበውን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- አዳምጣችሁ የጽሑፉን መልዕክት ታስረዳላችሁ፡፡
- እያዳመጣችሁ ማስታወሻ ትይዛላችሁ፡፡
- በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ክርክር ታደርጋላችሁ፡፡
- ምንባቡን ለብቻችሁ አንብባችሁ የምንባቡን መልዕክት ትናገራላችሁ፡፡
- ለቃላት አገባባዊ እና ተመሳሳይ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ገላጭ አንቀፅ ትፅፋላችሁ፡፡
- የተውላጠ ስምን ምንነት ታስረዳላችሁ፡፡
- ተውላጠ ስሞችን በመደብ ትለያላችሁ፡፡

### በማዳመጥ ጊዜ ማስታወሻ ለመያዝ የሚያስፈልጉ ጠቃሚ ምክሮች

ስናነብ ወይም ስናዳምጥ ማስታወሻ መያዝን መልመድ ብልህነት ነው፡፡ በመሆኑም ማስታወሻ መያዝ ስንፈልግ፡-

- ለማስታወሻ መያዣነት የሚያገለግሉ ወረቀት/ማስታወሻ ደብተር እና ብዕር/እርሳስ ማዘጋጀት
- ሀሳብን በሚደመጠው ወይም በሚነበበው ምንባብ ላይ ማሳረፍ
- ዋና ዋና ነጥቦችን በፍጥነት በማስታወሻ ደብተር ላይ ማስፈር
- ማስታወሻችሁን ከጨረሳችሁ በኋላ ወዲያውኑ በማረም ለተፈለገው አላማ መጠቀም

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት ሴት ካፒቴን

ተማሪዎች! መምህራችሁ "የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት ሴት አውሮፕላን አብራሪ" በሚል ርዕስ አጭር ፅሑፍ ያነቡላችኋል፡፡ እያዳመጣችሁ ጠቃሚ መረጃዎችን በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ፃፉ፡፡ ከዚያ በፊት ግን ከጓደኞቻችሁ ጋር በጥንድ ወይም በቡድን በመወያየት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን መልሱ፡፡




ሥዕል 2 ፡ ኢትዮጵያውያን ሴት ካፒቴኖች የበረራ ልብሳቸውን እንደለበሱ ከአውሮፕላን ማረፊያ ሲወጡ

**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

ሀ. የአውሮፕላን ካፒቴን ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. ትምህርታችሁን ስትጨርሱ ምን ለመሆን ትመኛላችሁ? የወደፊት ፍላጎታችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

**ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች**

. ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ፡፡

ሀ. ባዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ ዋና ገጸባህሪዋ ማን ትባላለች?

ለ. ዋና ገጸባህሪዋ ለቤተሰቦቿ ስንተኛ ልጅ ናት?

ሐ. ባለታሪኳ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን የተማረችው የት ነው?

መ. ባለታሪኳ አውሮፕላን ማብረር የጀመረችበት ዓመተ ምህረት መቼ ነበር?

ሠ. ካፒቴኗ ራሷን ችላ ለብቻዋ አውሮፕላን ማብረር የቻለችው መቼ ነበር?

ረ. በምንባቡ ውስጥ የመጀመሪያዋ አውሮፕላን አብራሪ ተብላ የተገለጸችው ማን ናት?

ሰ. ካፒቴኗ ዩኒቨርሲቲ ገብታ የተማረችው ትምህርት ምን ተብሎ ይጠራል?

ሸ. ባለታሪኳ አውሮፕላን አብራሪ እንድትሆን ያነሳሳት ምን ነበር?

ቀ. ባለታሪኳ የአውሮፕላን ካፒቴንነት ባታገኝ ኖሮ በምን ሙያ የምትሰማራ ይመስላችኋል?

፪. ቀጥሎ የተዘረዘሩት ቃላት ካዳመጣችሁት ፅሑፍ የወጡ ናቸው፡፡ በምንባቡ መሰረት የሚያስተላልፉትን ፍቺ በፅሑፍ ከገለፃችሁ በኋላ አረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. ምዘና | ሠ. አርኣያ |
| ለ. ህልሚን | ረ. ስኬታማ |
| ሐ. ሲከንፉ | ሰ. ማጎልበቻ |
| መ. ተሞክሮ | ሸ. ሥነህንፃ |

## ክፍል ሁለት፡ ንግግር

ኢትዮጵያውያን ሴቶች ቀዳሚ ከሆኑባቸው ተግባራት አንዱ የአትሌቲክስ ስፖርት ነው፡፡ በመሆኑም ስለ ታዋቂ ሴት አትሌቶች ቤተሰቦቻችሁን ወይም የሚያውቁ ሰዎችን በመጠየቅ ወይም መጽሀፍ በማንበብ መረጃ አጠናቅሩና ለክፍል ጓደኞቻችሁ የቃል ዘገባ አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሦስት፡ ማንበብ

### የሽማግሌው ምርቃት

**የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

ከዚህ በታች "የሽማግሌው ምርቃት" በሚል ርዕስ አንድ ምንባብ ቀርቦላችኋል፡፡ ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ግን በቡድን ሆናችሁ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡

1. ምርቃት ምንድነው?
2. ምርቃት ለምን ይጠቅማል?
3. የምሳሌያዊ አነጋገሮች ጠቀሜታ ምንድነው?

አንድ ሰርግ ውስጥ አንድ ሽማግሌ ሙሽሮቹን ሊመርቁ ቆሙና «አጣልቶ የሚያፋቅር፣ አጋጭቶ የሚያጣብቅ ፍቅር ይስጣችሁ» ብለው ሲመርቁ ሰማሁ፡፡ እስካሁን በብዙ ሠርጎች ላይ ተገኝቼ ምርቃት ሰምቻለሁ፡፡ ነገር ግን እንዲህ ያለ ምርቃት ሰምቼ አላውቅም፡፡ ምን ማለታቸው ይሆን? እያልኩ በኅሊናዬ ሳብሰለስለው ቆየሁ፡፡ «አጣልቶ የሚያፋቅር፣ አጋጭቶ የሚያጣብቅ ፍቅር? ደጋግሜ አሰብኩት፡፡ ይህንን ሳወጣ እና ሳወርድ እንዳጋጣሚ ሽማግሌው ምርቃታቸውን ፈጽመው እኔ የነበርኩበት ጠረጴዛ አጠገብ መጡና ተቀመጡ፡፡ መጠየቅ አለብኝ አልኩና አንገቴን በጠረጴዛው ላይ ሰገግ አድርጌ፤

«ደኅና ዋሉ አባቴ» አልኳቸው፡፡

«ይመስገነው ደኅና ነኝ» አሉኝ፡፡

«ቅድም የመረቁትን ምርቃት ሰምቼው ስለማላውቅ ገረመኝ» አልኩ ወሬ ለመወጠን ብዬ፡፡

«አንተ ብቻ አይደለህም፤ ብዙዎች ይገርማቸዋል፡፡» አሉ ፈገግ ብለው፡፡

«ምን ማለትዎ ነው ግን?» ብዬ ጠየቅኋቸው፡፡

«መጀመሪያ አንድ ታሪክ ልንገርህ» አሉኝ ጃኖአቸውን ወደ ቀኝ መለስ እያደረጉ፡፡ እኔም ወንበር ቀየርኩና አጠገባቸው ተደላድዬ ተቀመጥኩ፡፡

«አንድ ጊዜ አንዲት እህት ምክር ልትጠይቀኝ መጣች፡፡ እናም እንዲህ ስትል አጫወተችኝ፡ እኔ እና ባለቤቴ ከተጋባን ስምንት ዓመታችን ነው፤ ሁለት ልጆችንም ወልደናል፡፡ የራሳችን ቤት እና መኪና አለን፡፡ ሁለታችንም የየራሳችን በቂ ደመወዝ የሚገኝበት ሥራ አለን፡፡ ይህንን ያህል ዓመት በትዳር ስንኖር ተጋጭተን ወይም ተጣልተን አናውቅም፡፡ እንኳን ለመጣላት ለመፋቀርም ጊዜ አልነበረንም፡፡ ጭቅጭቅ፣ ንዝንዝ፣ በዚህ ወጣ፣ በዚህ ወረደ የሚባል ነገር በቤታችን ታይቶም ተሰምቶም አያውቅም፡፡ ጎረቤቶቻችን እና የሚያውቁን ሰዎች ሁሉ በኛ ይቀናሉ፡፡ እርሱን "ምን የመሰለች ሚስት አለችህ' ይሉታል፤ እኔንም "ምን የመሰለ ባል አለሽ' ይሉኛል፡፡

አንድ ጊዜ ጓደኛዬን ለማየት እና በዚያውም ለመዝናናት ብዬ ናይሮቢ ሄድኩ፡፡ ባለቤቴ ሥራ ስለነበረው አልሄደም፡፡ ጓደኛዬ ትዳር ከያዘች አምስት ዓመቷ ነው፡፡ ባለቤቷ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ ስለሚሠራ ነው፣ ኬንያ የሄዱት፡፡ እነርሱ ቤት አንድ ሳምንት ተቀመጥኩ፡፡ ያን ጊዜ ታድያ የኔን ትዳር ትዳር መሆኑን ተጠራጠርኩት፡፡ ጓደኛዬ ባለቤቷን በስሙ አትጠራውም፤ እርሱም እንዲሁ፡፡ ደክሞት ከመጣ እግሩን ታጥባላች፣ እርሱም እንዲሁ፡፡ ምግብ ሲበሉ እንደተጎራረሱ ነው የሚጨርሱት፡፡ ልጆቹን የሚንከባከቡት፣ ቤቱን የሚያስተዳድሩት፤ ሌላውንም ስራ የሚከውኑት አብረው ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ በኃይል ይከራከራሉ፤ ሊደባደቡ ነው ብዬ ስፈራ ለጥቂት ጊዜ ይኳረፉና ግን መልሰው ይፋቀራሉ፡፡ አንድ ቀን ታድያ ጓደኛዬን «ለመሆኑ ተጣልታችሁ ታውቃላችሁ? » ስል ጠየቅኳት፡፡ «በጣም እንጂ እኛ መጣላትንም መፋቀርንም እናውቅበታለን፡፡ ተጣልተን ተጣልተን ወጥቶልናል፡፡ ከጠብ በኋላ የሚኖረን ፍቅር ሁልጊዜ ምነው በተጣላን ያሰኘኛል» አለችኝ፡፡

ከዚያም ወደራሴ ተመልሼ አሰብኩ፡፡ እኔ እና ባለቤቴ ተጣልተን አናውቅም፡፡ አያድርሰውና አንድ ቀን ብንጣላ እንዴት እንደምንታረቅ የምናውቅበት አይመስለኝም፡፡ ክፉውን አርቅ አልኩ ለራሴ፡፡ ግን እኛ ተጠባብቀን ነው ወይስ ተፈቃቅረን ነው የምንኖረው ብዬም ራሴን ጠይቄዋለሁ፡፡ ሳስበው ግን በመጠባበቅ እንጂ በመነፋፈቅ የምንኖር አይመስለኝም፡፡ እናም ትዳሬን ጠላሁት» አለችኝ፡፡ ችግሯ ገብቶኛል፡፡ አንድ ጥያቄ ጠየቅኳት፡፡ «ላንቺ ፍቅር ማለት የጠብ አለመኖር ነው? ወይስ ጠብን ማሸነፍ? አልኳት፡፡ ቀና ብላ አየችኝ፡፡ አልመለሰችልኝም፡፡ ዝም ብላ አሰበች፡፡ «ለመሆኑ ለምን እንደማትጣሉ ታውቂያለሽ?» አልኳት፡፡ «ለምን ይመስልዎታል?» ብላ እኔኑ መልሳ ጠየቀችኝ፡፡ «የማትጣሉት ስለማትገናኙ ይመስለኛል፡፡ የት ተገናኝታችሁ፣ የት ተነጋግራችሁ፣ የት ተከራክራችሁ፣ የት ተቀራርባችሁ ትጣላላችሁ፡፡ መጋጨትኮ ከመቀራረብ የሚመጣ ነው፡፡ እናንተ ጠብን አይደለም ያሸነፋችሁት፤ ጠብን ነው የሸሻችሁት፡፡ አለመሞት እና ሞትን ማሸነፍ ይለያያል፡፡ አለመጣላትና ጠብን ማሸነፍም እንዲሁ፡፡ «ሐኪሞች ለምን ክትባት እንደሚወጉን ታውቂያለሽ አይደል፡፡ ክትባቱ የሚሠራው ከሞተ ቫይረስ ነው፡፡ ለምን? ያ የተዳከመ

ቫይረስ ወደ ሰውነታችን ሲገባ ሰውነታችን ጦርነት ተከፈተብኝ ብሎ ራሱን ያዘጋጃል፡፡ መድኃኒት ያመርታል፡፡ ራሱን በሽታ ለመከላከል ዝግጁ ያደርጋል ማለት ነው፡፡ ልምድ አዳበረ፤ በሽታውን እንዴት እንደሚያሸንፍ ኃይል እና ዐቅም ገንዘብ አደረገ ማለት ነው፡፡

ትዳርም ይሄ ክትባት ያስፈልገዋል፡፡ ወደፊት ከባዱ የትዳር ቫይረስ መጥቶ በበሽታ እናንተን ጠራርጎ ከመውሰዱ በፊት ደካማውን ቫይረስ መከተብ ያስፈልጋችኋል፡፡ ኃይል እና ዐቅም መፍጠር ያስፈልጋችኋል፡፡ ያልተከተበ ልጅ እና የተከተበ ልጅ ልዩነታቸው የሚታወቀው በሰላሙ ጊዜ አይደለም፡፡ ወረርሽኙ ሲገባ ነው፡፡ ያን ጊዜ ማን መቋቋም እንደሚችል ይታያል፡፡

ሁለታችሁም በየፊናችሁ ትውላላችሁ፡፡ ከዚያ ወደቤት ትገባላችሁ፡፡ ራት ትበላላችሁ፡፡ ይቀጥላል፡፡ ቤትም ውስጥ ብትሆኑ አንቺ ጓዳ ነሽ፤ እርሱም ቴሌቭዥን እያየ ነው፡፡ ልቅሶ ስትሄዱ እርሱ ከወንዶች ጋር ነው አንቺ ከሴቶች ጋር ነሽ፡፡ ዓመት በዓል ሲመጣ እርሱ በግ ይገዛል፣ አንቺ ዶሮ ትገዣለሽ፡፡ እርሱ በቱታ ጎምለል ጎምለል ይላል፤ አንቺ በሐበሻ ቀሚስ ጉድጉድ ትያለሽ፡፡ ይቀርባል ትበላላችሁ፡፡ በቃ፡፡

ወዳጄ የማይፈስ ውኃ ከድንጋይ ጋር አይጋጭም፡፡ የረጋ ውኃ ይሻግታል እንጂ ግጭት የለበትም፡፡ ወንዝ ሆኖ ሲወርድ ግን ገደሉ፣ ዐለቱ፣ ቋጥኙ ይላተመዋል፡፡ ለመላተም አይሄድም፡፡ ሲሄድ ግን ይላተማል፡፡ ከመኖር ብዛት ታድያ ፈለግ ይሠራል፡፡ ከዚህ በኋላ ኩልል ብሎ መፍሰስ ነው፡፡ እዚያ ደረጃ ለመድረስ ግን ስንት ትግል፣ ስንት ልትሚያ፣ ስንት ውጣ ውረድ አለ፡፡

ከዚህ ውይይታችን በኋላ ወደ ባልዋ ሄዳ ለትዳር ጊዜ ስለመስጠት፤ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ስለመነጋገር፤ የቤት ሥራን ለሥራነቱ ብቻ ሳይሆን ለደስታ መፍጠርያነቱ አብሮ ስለመሥራት ማንሣት ስትጀምር ነገር መጣ፡፡ ጭቅጭቅ ጀመርሽ ይላት ጀመር፡፡ የማይስማሙባቸው ነገሮች እየታወቁ መጡ፡፡ ይገርምሃል፡፡ በልቶ የማያውቅ ሰው ሲበላ እንደሚያመው ሁሉ፣ ተጋጭቶ የማያውቅ ሰው ሲጋጭ አያድርስብህ፡፡ አንድ ጋሪ ጠጠር በየቅንጣቱ ቢወረወር ከሚጎዳህ በላይ ጋሪውን እንደሞላ ቢደፋብህ የሚጎዳህ ይበልጣል፡፡ «ተጋጭተን አናውቅም» የሚሉ ሰዎችም ሲጋጩ እንደዚያው ነው፡፡ ለዚህ ነው «አጣልቶ የሚያፋቅር፣ አጋጭቶ የሚያጣብቅ ፍቅር ይስጣችሁ» ብዬ መመረቅ የጀመርኩት፡፡ ጠብን የሚያሸንፍ ፍቅር፣ ጦርነትን የሚያሸንፍ ሰላም፣ ጨለማን የሚያሸንፍ ብርሃን ነው የሚያስፈልገን ብዬ፡፡ ጉልበት ስሜ ተነሣሁ፡፡

(ዳንኤል ክብረት፡፡ 2003፡፡ የሚያሸንፍ ፍቅር፡፡ ለማስተማሪያነት እንዲያመች ተሻሽሎ የቀረበ)

## ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሐሰት በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያቱን በቃላችሁ ተናገሩ፡፡

ሀ. ምክር ጠያቂዋ ባለታሪክ በትዳሯ ደስተኛ ናት፡፡

ለ. በትዳር ደስተኛ ለመሆንና ተፋቅሮ ለመኖር መጣላት አስፈላጊ ነው፡፡

ሐ. የተከተበ ልጅ እና ያልተከተበ ልጅ ጥንካሬ የሚለካው በታመሙ ጊዜ ነው፡፡

መ. በምንባቡ ከቀረቡት ባለታሪኮች መካከል ተከባብረው የሚኖሩት ናይሮቢ ኬንያ የሚኖሩት ባለትዳሮች ናቸው።

ሠ. ምክር ጠያቂዋ ሴት ከባለቤቷ ጋር መጣላት የጀመረችው ሽማግሌው ስለመከሯት ነው።

ረ. ምክር ጠያቂዋ ሴት ኬንያ የምትኖረውን ጓደኛዋን ከመጎብኘቷ በፊት ሁሉንም የቤት ውስጥ ስራ ለብቻዋ ትሰራ ነበር።

፪. ከታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ መልሶቻችሁን በቃል ተናገሩ።

ሀ. በቤት ውስጥ ልጅ የመንከባከብና የማሳደግ ተግባር የማን መሆን አለበት? የሴት ወይስ የወንድ?

ለ. በቤት ውስጥ ምግብ ማብሰል፣ ልብስ ማጠብ፣ ቤት ማፅዳት፣ ወዘተ. ተግባር የሚፈፀመው በሴቶች ነው ወይስ በወንዶች?

ሐ. በምንባቡ መሰረት የባለታሪኳ ባል(ባለቤት) የቤት ውስጥ ስራዎችን በመስራት ባለቤቱን ማገዝ የማይፈልገው ለምን ይመስላችኋል?

መ. በምንባቡ ከቀረቡት ባለትዳሮች መካከል የፆታ እኩልነትን የሚተገብሩት የትኞቹ ናቸው?

፫. በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች ለይችሁ አውጡ። በመቀጠል ምሳሌያዊ አነጋገሮቹ በምንባቡ ውስጥ የሚያስተላልፉትን መልዕክት በፅሁፍ ግለፁ።

ለምሳሌ፡- "የማይፈስ ውሃ አይጋጭም"

ይህ አባባል የሚያስተላልፈው መልዕክት ሰዎች ለተለያዩ ተግባራት ከሰዎች ጋር በሚያደርጉት መስተጋብር ወይም የስራ ሂደት ውስጥ ሊጋጩ ይችላሉ። ነገር ግን ያለስራ ዝምብለው የሚቀመጡ ከሆነ ምንም አይነት ግጭት ውስጥ አይገቡም ማለት ነው። (ሰው የሚጋጨው ሲሰራ ነው) የሚል መልዕክት አለው።

## ክፍል አራት፡ ቃላት

፩. ከዚህ በታች ለቀረቡት ከምንባቡ የወጡ ቃላት አገባባዊ ፍቺ ስጡ።

ሀ. መወጠን

ለ. ወጥቶልናል

ሐ. ፊና

መ. ኩልል

ሠ. መላተም

ረ. ፈለግ

፪. በ"ሀ" ክፍል የተዘረዘሩትን ከምንባቡ የወጡ ቃላት በ"ለ" ክፍል ከተዘረዘሩት ተመሳሳያቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ. | ለ. |
|---|---|
| 1. ሰገግ | ሀ. መጣላት |
| 2. መወጠን | ለ. ኑሮ |
| 3. ጃኖ | ሐ. መጀመር |
| 4. ተጋጭተን | መ. የሚዘጋጀው |
| 5. ጭቅጭቅ | ሠ. በቅቶናል |
| 6. ትዳር | ረ. ተጣልተን |
| 7. መኳረፍ | ሰ. ነጠላ(ጋቢ) |
| 8. ወጥቶልናል | ሸ. ሳብ |
| 9. የሚሠራው | ቀ. ምኞት |
| 10. ተድላ | በ. ንዝንዝ |

## ክፍል አምስት፡ ጽሕፈት

፩. በምትኖሩበት አካባቢ ወይም በሀገራችን ውስጥ በአርአያነታቸው ከሚታወቁ ሴቶች መካከል አንድ በመምረጥ ለህብረተሰቡ አርአያ ስለሆኑበት ተግባር ገላጭ አንቀፅ ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አንብቡ፡፡

፪. ወላጆቻችሁን ወይም የሚያውቁ ሰዎችን በመጠየቅ፤ ከሴቶች ጋር ተያይዘው የሚነገሩ አምስት አምስት ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ከፃፋችሁ በኋላ ትርጉማቸውን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

## ክፍል ስድስት፡-ሰዋስው

### መደብ

መደብ ከተናጋሪ፣ ከአድማጭ እና ከርዕሰ ጉዳይ ጋር የተገናኘ ፅንሰሀሳብ ነው፡፡ አንድ ሰው ሲናገር "እኔ" እያለ፤ ከአንድ በላይ ከሆኑ ደግሞ "እኛ" እያሉ ነው፡፡ በመሆኑም እኔ እና እኛ የሚሉት ተውላጠ ስሞች አንደኛ መደብ ይባላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተናጋሪውን በቅርብ ሆኖ የሚያዳምጥ ሰው ሁለተኛ መደብ ይባላል፡፡ ተናጋሪዎች በቅርብ ሆነው የሚያዳምጧቸውን ሰዎች አንቺ፣ አንተ ወይም እናንተ በማለት ይጠሯቸዋል፡፡ስለዚህም እነዚህ ተውላጠ ስሞች ሁለተኛ መደብ ይባላሉ፡፡

ተናጋሪዎች እና አድማጮች አንድ ላይ ሆነው ስለሌላ ሰው ሊያወሩ ይችላሉ፡፡የተናጋሪዎቹና የአድማጮቹ ተተኳሪ የሆኑት ሰዎች ሶስተኛ መደብ ተብለው ይጠራሉ፡፡ በዚሁ መሰረት እሱ፣ እሷ ወይም እነሱ እየተባሉ ይጠራሉ ማለት ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ተውላጠ ስሞች ሶስተኛ መደብ ይባላሉ፡፡ ከላይ የጠቀስናቸውን ተውላጠ ስሞች በሚከተለው ሰንጠረዥ በቁጥር እና በመደብ ለይቶ ማመልከት ይቻላል፡፡

| መደብ | ነጠላ ቁጥር | ብዙ ቁጥር |
|---|---|---|
| አንደኛ መደብ ተውላጠ ስሞች | እኔ | እኛ |
| ሁለተኛ መደብ ተውላጠ ስሞች | አንተ<br>አንቺ | እናንተ |
| ሦሥተኛ መደብ ተውላጠ ስሞች | እሱ<br>እሷ | እነሱ |

በምንባቡ ውስጥ በአንደኛ መደብ እና በሁለተኛ መደብ የተገለፁ አረፍተ ነገሮችን ለይታችሁ አውጡ፡፡

| ምሳሌ፡- አንደኛ መደብ | ሁለተኛ መደብ |
|---|---|
| (እኛ)ተጣልተን አናውቅም፡፡ | አንቺ ዶሮ ትገዥለሽ፡፡ |
| | |
| | |
| | |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የማዳመጥና የንግግር ክሂሎችን ለማስተማር የቀረበው ጽሑፍ "የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት ሴት ካፒቴን" የሚል ነው፡፡ ከጽሑፉ በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሴት ካፒቴን አስካለ ጓሉ መሆኗን፤ አስካለ ጓሉ ካፒቴን ከመሆኗ በፊት `ለሰባት አመታት በረዳት ፓይለትነትና በፓይለትነት ማገልገሏን፤ ከሷ በፊትም ፓይለት ሆነው ያገለገሉ እንስት ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ፤ ለመረዳት ችለናል፡፡ በተጨማሪም አስካለ ለአዲሱ ትውልድ ሴቶች አርኣያ ስለሆነች፤ በተለይ ሴቶች የእሷን ፈለግ መከተል እንዳለባቸው መክረናል፡፡

በንግግር ክፍለ-ትምህርት በኢትዮጵያ የሚገኙ ታዋቂ ሴት አትሌቶችን በሚመለከት መረጃ በመሰብሰብ የቃል ዘገባ አቅርበናል፡፡ የቃል ዘገባ ለማቅረብ የሚያስችሉ መመሪያዎችም ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ የታዋቂ ሴት አትሌቶችን አርዓያ በመከተል ጠንክረን መስራትና ስኬታማ መሆን አለብን፡፡

የንባብ ክሂልን ለማተማር የቀረበው ምንባብ ይዘት ስርዓተ ፆታን የሚመለከት ነው፡፡ የምንባቡ ዋና ጭብጥ፣ በትዳር ውስጥ ባልና ሚስት የቤት ውስጥ ስራዎችን ተረዳድተው መስራት እንዳለባቸው፤

የቤት ውስጥ ስራዎችን የሴት እና የወንድ ብሎ መከፋፈል ጊዜ ያለፈበት ከመሆኑም ባሻገር በቤት ውስጥ ለሚፈጠር አለመግባባት መነሻ እንደሚሆን፤ ያብራራል፡፡ በመሆኑም በምንኖርበት ቤት ውስጥም ሆነ በአካባቢያችን ስራዎችን የወንድ እና የሴት ብለን ሳንከፋፍል ወላጆቻችንን ማገዝ አለብን፡፡

ቃላት የሚኖራቸው አገባባዊ ፍች አብረዋቸው በገቡት ቃላት የሚወሰን ነው፡፡ ለቃላት ተመሳሳይ ፍች የምንሰጠው ደግሞ የቃላትን መዝገበቃላዊ ፍች መሰረት በማድረግ ነው፡፡

በሰዋስው ክፍል የቀረበው ትምህርት ተውላጠ ስሞችን የሚመለከት ነው፡፡ ተውላጠ ስሞች የስም ምትክ፣ ስምን ወክለው የሚገቡ ቃላት ናቸው፡፡ በአማርኛ ስምንት ተውላጠ ስሞች አሉ፡፡ እነሱም፡- በሦስት መደቦች ስር የሚመደቡ ሲሆን አመዳደባቸው የሚከተለውን ይመስላል፡፡

| | አንደኛ መደብ ተውላጠ ስሞች | ሁለተኛ መደብ ተውላጠ ስሞች | ሦስተኛ መደብ ተውላጠ ስሞች |
|---|---|---|---|
| ነጠላ ቁጥር | እኔ | አንተ፣ አንቺ | እሷ፣ እሱ |
| ብዙ ቁጥር | እኛ | እናንተ | እነሱ |

### የክለሳ ጥያቄዎች

1. “የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት ካፒቴን” የሚለውን ጽሑፍ ጭብጥ ባጭሩ ግለፁ፡፡
2. ፓይለት እና ካፒቴን የሚለያዩባቸውን ነጥቦች በጽሑፍ ግለፁ፡፡
3. “የሸማግሌው ምርቃት” የሚለው ምንባብ የሚያስተላልፈው መልዕክት ምንድን ነው
4. ስለሴቶች የሚነገሩ አዎንታዊ መልዕክት ያላቸው አምስት ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ፃፉ፡፡
5. በብዙ ቁጥር የሚነገሩ የአማርኛ ተውላጠ ስሞች ስንት ናቸው  ቁጥራቸውን ከተናገራችሁ በኋላ በእያንዳንዳቸው አረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

## ክፍል ሰባት:- የግንዛቤ ማመሳከሪያ ነጥቦች

ከዚህ በታች በምዕራፉ የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች ምን ያህል እንደተረዳችኋቸው ለማረጋገጥ የሚረዱ ማመሳከሪያ ነጥቦች ተዘርዝረዋል፡፡ በመሆኑም ዝርዝሮቹን በጥንቃቄ በማንበብ፣ ተረድታችኋቸው ከሆነ፣ ከፊትለፊታቸው ባለው ሳጥን ውስጥ የ(V) ምልክት በማድረግ አረጋግጡ፡፡ ያልተረዳችሁት ወይም የሚያጠራጥራችሁ ከሆነ ግን በሳጥኑ ውስጥ የ (?) ምልክት በማድረግ ያልተረዳችኋቸውን ነጥቦች ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

| ተ.ቁ | ማመሳከሪያ ነጥብ | (√) | (?) |
|---|---|---|---|
| 1 | አዳምጬ የጽሑፉን መልዕክት ተረድቻለሁ፡፡ | | |
| 2 | አዳምጬ ጠቃሚ ማስታወሻ ይዣለሁ፡፡ | | |
| 3 | ሥርዓቱን ጠብቄ ክርክር አድርጌያለሁ፡፡ | | |
| 4 | ያነበብሁትን ምንባብ መልዕክት ተረድቻለሁ፡፡ | | |
| 5 | ለቃላት አገባባዊ ፍች ሰጥቻለሁ፡፡ | | |
| 6 | ለቃላት ተመሳሳይ ፍች ሰጥቻለሁ፡፡ | | |
| 7 | ገላጭ አንቀፅ ፅፌያለሁ፡፡ | | |
| 8 | የተውላጠ ስምን ምንነት አውቄያለሁ፡፡ | | |
| 9 | ተውላጠ ስሞችን በሦሥት መደቦች ስር መድቤያለሁ፡፡ | | |

# ምዕራፍ ሦስት፡ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ የቀረበውን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ:-

- አዳምጣችሁ የምንባቡን መልዕክት ታስረዳላችሁ፡፡
- አዳምጣችሁ ከምንባቡ ዝርዝር ሀሳቦችን ትለያላችሁ፡፡
- በቀረበው የንግግር ርዕሰ ጉዳይ ላይ ንግግር ታደርጋላችሁ፡፡
- አንብባችሁ የምንባቡን መልዕክት ታስረዳለችሁ፡፡
- ለቃላት ተመሳሳይ እና አገባባዊ ፍቺ ትሰጣለችሁ፡፡
- ርዕስ መርጣችሁ አንቀፅ ትፅፋላችሁ፡፡
- የቴክኖሎጂ ውጤቶችን አገልግሎት ትገልፃላችሁ፡፡
- ቃላትን ተጠቅማችሁ አዳዲስ አረፍተነገሮችን ትመሰርታላችሁ፡፡
- ከአረፍ ነገር ውስጥ ባለቤትና ማሰሪያ አንቀፅን ለይታችሁ ታመለክታላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ ሳተላይት

“የመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ ሳተላይት” በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ካዳመጣችሁ በኋላ ከስሩ የቀረቡላችሁን የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች መልሱ፡፡ ከዚያ በፊት ግን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎችን አብረዋችሁ ከተቀመጡት ተማሪዎች ጋር በመሆን ተወያዩባቸው፡፡



ሥዕል 3፡ ሳተላይቷ ወደ ህዋ ከመተኮሷ በፊት



ሥዕል 4፡ሳተላይቷ ህዋ ላይ ካረፈች በኋላ

## ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ከታች የቀረቡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ስመመለስ በቡድን ከተወያያችሁ በኂላ መልሳችሁን ስመምህራችሁ በቃል ተናገሩ፡፡

ሀ. ሳተላይት ምንድን ነው?

ለ. ከላይ በቀረቡት የሳተላይት ምስሎች መካከል የምታዩትን ልዩነት ተናገሩ፡፡

ሐ. ሳተላይት ማምጠቅ ለምን ለምን ያገለግላል?

## ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ፡፡

ሀ. በምንባቡ የተላለፈውን መልዕክት በቃላችሁ ተናገሩ፡፡

ለ. ከኢትዮጵያ ሳተላይት የሚገኘው መረጃ በምን በምን ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነው?

ሐ. የኢትዮጵያ ሳተላይት መቆጣጠሪያ ጣቢያ የሚገኝበት ቦታ ምን ይባላል?

መ. የኢትዮጵያ ሳተላይት ክብደት ስንት ኪሎ ግራም ነው?

ሠ. የመሬት ምልከታ ሳተላይት ተግባር ምንድን ነው?

ረ. ሳተላይት ለግብርናው ዘርፍ ምን ምን መረጃዎችን ይሰጣል?

፪. የሚከተሉትን ቃላት ባዳመጣችሁት ታሪክ መሰረት በአረፍተነገር ውስጥ አስገብታችሁ ፍቻቸውን አሳዩ፡፡

ሀ. እየዘመነ

ለ. ትሸምት

ሐ. ማምጠቅ

መ. ማሰስ

ሠ. መተንበይ

## ክፍል ሁለት፡ ንግግር

፩. በሀገራችን በተለያዩ ከተሞች የኢንዱስትሪ መንደሮች እየተመሰረቱ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም የኢንዱስትሪ መንደር መስፋፋት ለሀገራችን ኢትዮጵያ የሚሰጠውን ጠቀሜታ በሚመለከት (ከመጽሔት፣ ከጋዜጣ፣ ከበይነ መረብ፣ ወዘተ.) መረጃ ከሰበሰባችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ፡፡

፪. ከዚህ በታች የጎጆ ኢንዱስትሪንና ዘመናዊ ኢንዱስትሪን የሚያሳዩ ስዕሎች ቀርበዋል፡፡ ቡድን መስርታችሁ በጎጆ ኢንዱስትሪና በዘመናዊ ኢንዱስትሪ መካከል በሚስተዋለው ልዩነት ላይ በመወያየት የተስማማችሁበትን ሀሳብ በቡድን ተወካያችሁ በኩል ለክፍሉ ተማሪዎች ተናገሩ፡፡ በውይይታችሁ ወቅት፤

አንድን የፋብሪካ ወይም የጎጆ ኢንዱስትሪ ውጤት ለማምረት፡-

- ስለሚፈጀው ጊዜ
- የሚጠይቀው ጉልበት
- በብዛት ማምረት መቻል/አለመቻል
- ችግር ፈች ስለመሆኑ
- የሚጠይቀው በጀት እና ቦታ… የመሳሰሉትን ሀሳቦች እንደመነሻ ተጠቀሙ።



ሥዕል 5፡ በግራ በኩል በባህላዊ መንገድ ልብስ የሚሰራ ሰው፤ በቀኝ በኩል በዘመናዊ መንገድ ልብስ የሚሰራ በርካታ ማሽን

## ክፍል ሦስት፡ ንባብ

## ሳይንስና ቴክኖሎጂ ለዘላቂ ልማት

### የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ የምትሏቸውን ምላሾች ስጡ።

1. 'ሳይንስ' እና 'ቴክኖሎጂ' ስለሚሉት ቃላት ምን ምን ታውቃላችሁ?
2. እንደስልክ፣ መኪና አውሮፕላን የመሳሰሉት የፈጠራ ውጤቶች ባይኖሩ ኖሮ የሰው ልጆች አኗኗር ምን ይመስል ነበር?

'ሳይንስ' እና 'ቴክኖሎጂ' የተሰኙት ቃላት በአብዛኛው አንዳቸው ሌላኛቸውን በመተካት ጥቅም ላይ ሲውሉ ይታያሉ። ሆኖም ግን በጥልቀት ሲመረመሩ ሁለቱ ቃላት የተለያየ ግብና ትርጓሜ አላቸው። የሳይንስ ግብ እውቀትን ለማግኘት ሲባል ብቻ የሚከናወን እውቀት የመፈለጊያ ሂደት ሲሆን፣ የቴክኖሎጂ ግብ ደግሞ የሰው ልጆችን ችግሮች በመፍታት የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩ የሚያደርጉ ምርቶችን መፍጠር መቻል ነው። ስለዚህ «ሳይንስ የቴክኖሎጂ ፅንስ ሲሆን ውልደቱ ደግሞ ቴክኖሎጂ» ነው። በሌላ አገላለፅ «ሳይንስ ማወቅ ሲሆን ቴክኖሎጂ መስራት» ነው። ያለ ሳይንስ ቴክኖሎጂን ማሰብ ወይም ያለ ቴክኖሎጂ ሳይንስ ላይ ብቻ ማተኮር ዉጤት አልባ ነው። በመሆኑም ሳይንስና ቴክኖሎጂ ከፍተኛ ቁርኝት ያላቸው የማይነጣጠሉ ፅንሰ ሃሳቦች ናቸው።

ሳይንስና ቴክኖሎጂ ለአንድ ሀገር ልማት ጉልህ ሚና ይጫወታሉ። አካባቢዎች ከትናንሽ መንደርነት ወደ ትላልቅ ከተማነት የሚለወጡት በሂደት በሚመጣው የሳይንስና ቴክኖሎጂ መስፋፋት ነው። በዚህም ከገጠሬነት ወደ ከተሜነት የሚደረገው ሽግግር በሳይንስና ቴክኖሎጂው ለተገባበር የሚሳካ ይሆናል ማለት ነው። መብራት፣ የቧንቧ ውሃ፣ የተሻለ መንገድ፣ ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎችና ሌሎች የመሰረተ ልማት አውታሮች የሳይንስና ቴክኖሎጂ ስኬትን ተከትለው የሚመጡ ለውጦች ናቸው። ከእነዚህ ለውጦች ጎን ለጎን የጎለበተ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገቶችን ያሻሽላል። ለምሳሌ ያህል ምርትን ከተባይ ከመጠበቅ ጀምሮ ዝቅተኛ ተረፈ ምርት ወዳለው የምግብ ማምረት ሒደት መሸጋገር፣ የአካባቢ ብክለትን ከመቀነስ ወደ ንፁህና አረንጓዴ አካባቢን መፍጠር ማምራት፣ ከመሰረታዊ ኤሌክትሪክ ፍጆታ ወደ ተሻለና ተመጣጣኝ የኮሙኒኬሽንና ትራንስፖርት ስርዓት መሸጋገር፣ ወዘተ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ውጭ ሊታሰቡ አይችሉም።

| የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች |
|---|
| 1. ሳይንስና ቴክኖሎጂ በሚሉት ቃላት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? |
| 2. አካባቢዎች ከትናንሽ መንደርነት ወደ ትላልቅ ከተማነት የሚለወጡት እንዴት ነው? |
| 3. ቀጥሎ የሚመጣው የምንባብ ክፍል ስለምን የሚነግረን ይመስላችኋል? |

ሳይንስና ቴክኖሎጂ የሰለጠነ ማህበረሰብ ቁልፍ መገለጫ እየሆነ በመምጣቱ፣ ዘመናዊው ማህበረሰብ ከዘርፉ ሀሳቦችና ቁሶች ጋር ተቆራኝቷል። የስራ ቦታዎችና ሌሎች የህዝቡ መኖሪያዎች በአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ቁጥጥር ስር ገብተዋል። በአሁኑ ዘመን የሳይንስና ቴክኖሎጂ እውቀት ያለው ሰው ዋጋው ከፍ ያለና በላቀ ሁኔታ ተመራጭ ሆኗል። ስለብነት የኮምፒውተር ቴክኖሎጂን ብንመለከት በ1930ዎቹ አካባቢ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲፈጠር ጠቀሜታው ከሂሳብ ስሌት መስሪያነትና ሰነድን ከመያዝ አልፎ ማንኛውንም ስራ መስራት ከሚቻልበት ደረጃ ላይ ይደረሳል ተብሎ አልተገመተም ነበር። ዛሬ ግን ኮምፒውተሮች ከማንነታችን ጋር ተቆራኝተዋል፤ በየትኛውም የስራ መስክና ቦታ የግዴታ ያህል አስፈላጊ እየሆኑ መጥተዋል።

በአሁኑ ወቅት የእድገት ማማ ላይ የደረሱት ሀገራት ለማደግና ከችግራቸው ለመውጣት በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ፈጠራ ላይ የሰሩት ስራ እጅግ ውጤታማ አድርጓቸዋል። ለሚገኙበት የእድገት ደረጃ ለመድረስ ያስቻላቸውም በሳይንስና ቴክኖሎጂ በመታገዝ ጠንክረው መስራት መቻላቸው ነው። ቴክኖሎጂ ሀብትን በመፍጠር፣ የህይወትን የጥራት ደረጃ በማሻሻል ረገድ ብሎም ለትክክለኛ የኢኮኖሚ እድገትን ለማስመዝገብ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

በ19ኛው ክፍለ ዘመን በኢንዱስትሪ አብዮት የሚጨበጥ ለውጥ ያመጡት እንግሊዝና ፈረንሳይ፣ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ግብርናን ትከተል የነበረችው አሜሪካ ወደ ኢንዱስትሪው ልዕለ ሀያልነት የተሸጋገረችበት ለውጥ፣ ከ1960ዎቹ ጀምሮ ወደ ኢንዱስትሪያዊ ስኬት የተመነደጉት ታይዋንና ኮሪያ፣ በቅርቡም በማምረቻው ዘርፍና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪው መስክ ቻይናና ህንድ የሚመሩበትን ሁኔታ በማሳያነት ማንሳት ይቻላል። የእነዚህ ሀገራት ስኬት የመጣው በጥንቃቄ የተነደፈውን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፖሊሲና ስትራቴጂያቸውን በአግባቡ በመተግበራቸው ነው።

በሳይንስና ቴክኖሎጂው ዘርፍ የተሻለ መሰረት ያላቸው ሀገራት በፍጥነት ያድጋሉ፡፡ እንደማሳያነትም ሩሲያ፣ ጃፓን፣ ብራዚል፣ ቻይና፣ ህንድና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል፡፡ እንደ ዓለም ባንክ መረጃ በቅርብ አመታት ውስጥ በዓለማችን ላይ የግዙፍ ኢኮኖሚ ባለቤት ይሆናሉ ብሎ የጠቀሳቸው ሀገራት ቻይና፣ ጃፓን፣ ህንድ፣ ታይላንድ፣ ኢንዶኔዥያ፣ ደቡብ ኮሪያና ታይዋን ናቸው፡፡ ከጥቂት አስርት ዓመታት በፊት እነዚህ ሀገራት የሚታወቁት በነበሯቸው ደካማ ፖሊሲ፣ ዝቅተኛ የስራ ስነ-ምግባርና ድህነት ነበር፡፡ በኋላም ሳይንስና ቴክኖሎጂዎችን ውጤታማ በሆነና በተገቢው መልኩ በማስተዋወቃቸውና በመተግበራቸው ፈጣን እድገት ሊያስመዘግቡ ችለዋል፡፡ ሀገራቱ ለሌሎች ታዳጊ ሀገራት ጭምርም አርዓያ ለመሆን በቅተዋል፡፡

በአጠቃላይ በየትኛውም አቅጣጫ ያለ የሰው ልጆች ምቾትና ስኬት ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ኤሌክትሪክ፣ አውሮፕላን፣ ስልክ፣ ቴሌቪዥን፣ ኮምፒውተር ወዘተ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጪ ሊታሰቡ የሚችሉ አይደሉም፡፡ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ርቀው ያሉ ሀገራት እንደ ኋላ ቀርና ደካማ ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ ሀገራቱ የዜጎቻቸውን ፍላጎት ማሳካትና ኑሯቸውም የተደላደለ እዲሆን ማድረግ አይቻላቸውም፤ ዜጎቻቸው በምጣኔ ሀብታዊና የደህንነት ስጋቶች የተከበቡ ይሆናሉ፡፡ በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስኮች ደካማ የሆኑ ሀገራት ዜጎቻቸውን ለመታደግ ሲሉ በሌሎች ሀገራት ላይ ጥገኛ መሆናቸው አይቀሬ ነው፡፡ ይህም ሀገራቱን የማይወጡት የችግር አዙሪት ውስጥ በመክተት የሉአላዊነት ስጋት እንዲጋረጥባቸው ያደርጋቸዋል፡፡

(ምንጭ፡ የአማራ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢንፎርሜሽን ኮሚውኒኬሽን ኮሚሽን፤ 2009)

**ድህረ ንባብ ጥያቄዎች**

**፩. የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች የያዙት ሀሳብ በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆነ 'እውነት' ስህተት ከሆነ ደግሞ 'ሐሰት' በማለት መልሱ፡፡**

1. ሳይንስና ቴክኖሎጂ የስልጣኔ መገለጫ እየሆነ በመምጣቱ፣ ዘመናዊው ማህበረሰብ ከዘርፉ ሀሳቦችና ቁሶች ጋር ተቆራኝቷል፡፡
2. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን በአግባቡ አለመተግበር ሀገራትን ለተለያዩ ቀውሶች ሊያጋልጣቸው ይችላል፡፡
3. ዝቅተኛ የስራ ስነምግባርና ድህነት መገለጫቸው የሆኑ ሀገራት ሳይንስና ቴክኖሎጂን ቢገለገሉም እንኳ መለወጥ አይችሉም፡፡
4. በምጣኔ ሀብታዊና በደህንነት ስጋቶች የተከበቡ ዜጎች የየግላቸውን ፍላጎቶች ከማሳካታቸውም በላይ ሀገሮቻቸውን ማሳደግ ይችላሉ፡፡
5. ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ርቀው ያሉ ሀገራት ኋላ ቀርና ደካማ ተደርገው የሚቆጠሩት ሳይንስና ቴክኖሎጂ የስኬትና ምቾት መገለጫ እየሆነ በመምጣቱ ነው፡፡

## ክፍል ስራት፡ ቃላት

፩. ከዚህ በታች ከምንባቡ የተወሰዱ ቃላትና ሐረጋት በ 'ሀ' ስር ተዘርዝረዋል፤ ፍቺ የሚሆኗቸውን ከ 'ለ' ስር በመምረጥ አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የችግር አዙሪት | ሀ. ምሳሌ ወይም ሞዴል |
| 2. አርዓያ | ለ. አፈጻጸም፣ አካሄድ |
| 3. ዘርፍ | ሐ. በከፍተኛ ሁኔታ ያደጉት |
| 4. የተመነደጉት | መ. ተሳስረዋል፤ በደንብ ተያይዘዋል |
| 5. የእድገት ማማ | ሠ. ፍሬ ቢስ፤ ትርፍ የሌለው |
| 6. ተቆራኝተዋል | ረ. የስልጣኔ ምሰሶ |
| 7. ቁልፍ | ሰ. የማይወጣበት መከራ |
| 8. ፍጆታ | ሸ. የስራ መስክ |
| 9. አተገባበር | ቀ. ጥቅም ላይ የሚውል |
| 10. ውጤት አልባ | በ. ዋና፣ ወሳኝ |

፪. ከዚህ በታች 'ከሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ውጭ ሊታሰቡ አይችሉም' በሚል በምንባቡ ውስጥ በጥምረት የቀረቡት ሀሳቦች ተጎድለው ተሰጥተዋል፤ አሟልታችሁ ፃፏቸው።

ሀ. ምርትን ከተባይ ከመጠበቅ እስከ ______________________________

ለ. ________________________ እስከ ንፁህና አረንጓዴ አካባቢን መፍጠር ማምራት

ሐ. ከመሰረታዊ ኤሌክትሪክ ፍጆታ እስከ ______________________________

፫. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ የምትሏቸውን ምላሾች በምክንያት አስደግፋችሁ ስጡ።

1. «ሳይንስ የቴክኖሎጂ ፅንስ ሲሆን ውልደቱ ደግሞ ቴክኖሎጂ ነው» የሚለው አባባል ምን ማለት ነው?
2. በ19ኛውና በ20ኛው መቶ ክፍለዘመን የምጣኔ ሀብታዊ ለውጥ አምጥተዋል የተባሉት ሀገራት ስኬታቸውን ያስመዘገቡት እንዴት ነው?
3. ከሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ውጭ ሊታሰቡ አይችሉም የተባሉት ምን ምን ጉዳዮች ናቸው?
4. አንዳንድ ሀገራት በሌሎች ሀገራት ላይ ጥገኛ መሆናቸው አይቀሬ ይሆናል የተባለው ለምንድን ነው?
5. ሀገራችን ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ቱርፋቶች የበለጠ ተጠቃሚ ለመሆን ምን ማድረግ የሚጠበቅባት ይመስላችኋል?

6. የሳይንስና የቴክኖሎጂ ውጤቶች መጠቀምን በተመለከተ በየአካባቢያችሁ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ የሚያሳይ መረጃ አሰባስቡና ለክፍል ጓደኞቻችሁ የቃል ዘገባ አቅርቡ።

፫. ምሳሌውን በመከተል ከዚህ በታች የቀረቡትን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች አገልግሎት በክፍት ቦታው ላይ ፃፉ።

ምሳሌ፡-

ሀ. ድሮን፡- ያለ ሰው በመብረር መረጃዎችን ይሰበስባል፤የተለያዩ ፎቶግራፎችን ያነሳል፤

ለ. ሮቦት፡- በፋብሪካዎች ውስጥ ሰውን ተክቶ ሥራ ይሰራል፤ የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናል

ሐ. ኮምፒውተር፡- ______________________________

መ. ፎቶኮፒ ማሽን፡-_____________________________

ሠ. ካውያ፡- ___________________________________

ረ. ሳውንደሪ፡-______________________________

ሰ. ካስክ፡-_________________________________

ሸ. ኮምባይነር፡-____________________________

ቀ. ትራክተር፡-______________________________

በ. ፍሪጅ፡-_________________________________

ተ. መኪና_________________________________

ቸ. መርከብ_________________________________

ኀ. ካሜራ_________________________________

ነ. ቴሌቪዥን_______________________________________

ኘ. አምፖል_________________________________

## ክፍል አምስት፡ ጽሕፈት

፩. ከዚህ በታች ጥቅም ላይ እየዋሉ ካሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ጥቂቶች ቀርበዋል። ከተዘረዘሩት መካከል አንዱን በመምረጥ እንዴት እንደሚሰራና ለምን ጥቅም እንደሚውል የሚገልጽ አንቀጽ ጻፉ።

ሀ. ኮምፒውተር

ለ. ቴሌቪዥን

ሐ. ፎቶኮፒ ማሽን

መ. ተንቀሳቃሽ ስልክ (ሞባይል)

## ክፍል ስድስት፡-ሰዋስው

### ማስታወሻ፡-

**ባለቤት፡-** ባለቤት ማለት በአረፍተ ነገሩ ውስጥ የተፈፀመውን ድርጊት የሚከውን፤ ድርጊት ፈፃሚ ወይም ጉኝ ስም ነው፡፡ በአማርኛ የአረፍተ ነገር ባለቤት የሚገኘው በአረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ላይ ነው፡፡

**ማሰሪያ አንቀጽ፡-** ማሰሪያ አንቀጽ ማለት በአረፍተ ነገሩ ውስጥ የተፈፀመውን ድርጊት የሚሸከም ወይም የሚወክል ቃል ነው፡፡ ማሰሪያ አንቀጽ በአረፍተ ነገር መዋቅር ውስጥ የሚገኘው በአረፍተ ነገር መጨረሻ ላይ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ልጁ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡

**ባለቤት፡-** የዚህ አረፍተ ነገር ባለቤት "ልጁ" የሚለው ስም ነው፡፡ ምክንያቱም ድርጊቱን የፈፀመው፤ ማለትም ወደ ትምህርት ቤት የሄደው "ልጁ" ስለሆነ ነው፡፡ የሚገኘውም በአረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ላይ ነው፡፡

**ማሰሪያ አንቀጽ፡-** የዚህ አረፍተ ነገር ማሪያ አንቀጽ ደግሞ "ሄደ" የሚለው ቃል ነው፡፡ ምክንያቱም የተፈፀመውን ድርጊት የተሸከመው "ሄደ" የሚለው ግስ ስለሆነ ነው፡፡ የሚገኘውም በአረፍተ ነገሩ መጨረሻ ላይ ነው፡፡

**፩. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ወስጥ የሚገኙትን የአረፍተ ነገሮች ባለቤቶች እና ግሶች (ማሰሪያ አንቀፆች) ለይታችሁ ፃፉ፡፡**

ሀ. ቶፊቅ በኮምፒውተር ደብዳቤ ፃፈ፡፡

ለ. መምህሩ ተማሪዎቹን ተቆጣጠረ፡፡

ሐ. ሐዋ ከገበያ አራት ብርቱካን ገዛች፡፡

መ. አጭሩ ልጅ በመኪና አዲስ አበባ ደርሶ መጣ፡፡

ሠ. ኀይሌ ገብረስላሴ ታዋቂ አትሌት ነው፡፡

ረ. ዘምዘም በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ የሶማልኛ ቋንቋ መምህርት ናት፡፡

ሰ. አርሶ አደሩ በዚህ አመት ከፍተኛ የስንዴ ምርት አገኙ፡፡

ሸ. ኢትዮጵያ ብዙ ቋንቋዎችና ባህሎች ያሏት ሀገር ናት፡፡

ቀ. ሰው ሳይንስና ቴክኖሎጂን በመጠቀም መኪና፣ መርከብ እና አውሮፕላንን ለመጓጓዣነት ሠራ፡፡

በ. ግመል በአፋር እና በሶማሌ ክልሎች ይኖራል፡፡

፪. ከዚህ በታች የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ በማለት ለሁለት ክፈሏቸው፡፡

ለምሳሌ፡- አንድ ትልቅ ልጅ ከትምህርት ቤት መጣ፡፡

ስማዊ ሀረግ፡- አንድ ትልቅ ልጅ

ግሳዊ ሀረግ፡- ከትምህርት ቤት መጣ

1. ኮምፒውተር የቴክኖሎጂ ውጤት ነው፡፡
2. ሀገር በዜጎች ጥረት ትገነባለች፡፡
3. ብርቱ የቀበሌ መታወቂያ የላትም፡፡
4. እነቶፊቅ ወደ ድሬዳዋ ሄዱ፡፡
5. የሶማሌ ክልል ሰፊ የቆዳ ስፋት አለው፡፡
6. ዝናባማው ወቅት ሰብሎችን ለማምረት አስፈላጊ ነው፡፡
7. ታላቁ የህዳሴ ግድብ የኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጨት ጀመረ፡፡
8. የአባይ ወንዝ ረዥም ርቀት ይጓዛል፡፡
9. ፈረስ፣ አህያ እና በቅሎ የጋማ ከብቶች ናቸው፡፡
10. የግመል ወተት አይረጋም፡፡



## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የማዳመጥንና የንግግር ክሂልን ለማተማር የቀረበው ጽሑፍ “የኢትዮጵያ ሳተላይት” የሚል ነው፡፡ ኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ የሆነውን ሳተላይት ከአጋሯ ቻይና ጋር በመሆን ታህሳስ 10 ቀን 2012 ዓ.ም. አስወንጭፋለች፡፡ ሳተላይቷ በህዋ ላይ በመዘዋወር ከግዙፍ ክንውኖች እስከ ጥቃቅን እንቅስቃሴዎች ትመዘግባለች፡፡ በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ትክክለኛ መረጃዎችን በመሰብሰብ የገንዘብ ወጭንና የሰው ሀይል ጉልበትን ከማዳን አንፃር ከፍተኛ ሚና እየተጫወተች ትገኛለች፡፡ በዚህ ፅሑፍ መነሻነት ዝርዝር መረጃዎችን የሚጠይቁ የድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች ተሰርተዋል፡፡

የንግግር ክሂል የቀረበው በኢንዱስትሪ መንደሮች ግምባታ ዙሪያ ነው፡፡ በመሆኑም የኢንዱስትሪ መንደሮች መስፋፋት ለሀገራችን ኢትዮጵያ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ በሚመለከት በክፍል ውስጥ ንግግር ተደርጓል፡፡

የንባብ ክሂልን ለማስተማር የቀረበው ምንባብ በሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ላይ ያተኮረ ነው። ምንባቡም ሳይንስና ቴክኖሎጂ የሰው ልጆችን ችግሮች በመፍታት የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩ የሚያደርጉ የሰው ልጅ የስልጣኔ ውጤቶች መሆናቸውን፤ በዓለም ላይ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ዕድገት ያሳዩ ሀገሮች በፍጥነት እያደጉ መሆናቸውን፤ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ያላደጉት ሀገሮች ደግሞ ገና ለማደግ ጥረት በማድረግ ላይ መሆናቸውን ተገንዝበናል።

አረፍተ ነገር "ባለቤት" እና "ማሰሪያ አንቀጽ" የተባሉ ሁለት ክፍሎች ያሉት መሆኑን፤ "ባለቤት" በአረፍተ ነገር መጀመሪያ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ "ማሰሪያ አንቀጽ" ደግሞ በአረፍተ ነገር መጨረሻ ላይ የሚገኝ መሆኑን ተረድተናል። በአንፃሩ ደግሞ የአረፍተ ነገር ባለቤት "ስማዊ ሀረግ" እንደሚባል፤ እንዲሁም የአረፍተ ነገር ማሰሪያ አንቀጽ "ግሳዊ ሀረግ" እንደሚባል በምሳሌ ተደግፎ ቀርቦ ተመልክተናል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ኢትዮጵያ ሳተላይት በማስወንጨፏ ምን ጥቅም ታገኛለች
2. ከ"ሳይንስ" እና "ቴክኖሎጂ" የሰው ልጆችን ችግር የበለጠ የሚፈታው የትኛው ነው  እንዴት
3. "አዙሪት፣ አርአያ፣ ፍጆታ" በሚሉት ቃላት አረፍተ ነገር መስርታችሁ ትርጉማቸውን አሳዩ።
4. የአረፍተ ነገር "ባለቤት" እና "ማሰሪያ አንቀጽ" የተባሉትን ፅንሰ ሀሳቦች ምንነት ግለፁ።
5. ቀጥሎ የቀረቡትን አረፍተ ነገሮች ስማዊ ሀረግ እና ግሳዊ ሀረግ በማለት መድቧቸው።
   - 5.1. ትልቅ አንበሳ ሁለት ላሞችን ገደለ።
   - 5.2. ትልቁ ልጅ እንቁላል ገዛ።
   - 5.3. ናሆም ወደትምህርት ቤት ሄደ።
   - 5.4. የቋንቋ ትምህርት ቃላዊ ተግባቦትን ያሳድጋል።
   - 5.5. የመኪና ሹፌር ሁልጊዜ ንቁ ነው።

## ክፍል ሰባት፡ የግንዛቤ ማመሳከሪያ ነጥቦች

ከዚህ በታች በምዕራፉ የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች ምን ያህል እንደተረዳችኋቸው ለማረጋገጥ የሚረዱ ማመሳከሪያ ነጥቦች ተዘርዝረዋል። በመሆኑም ዝርዝሮቹን በጥንቃቄ በማንበብ፤ ተረድታችኋቸው ከሆነ ከፊትለፊታቸው ባለው ሳጥን ውስጥ የ(V) ምልክት በማድረግ አረጋግጡ። ያልተረዳችሁት ወይም የሚያጠራጥራችሁ ከሆነ ግን በሳጥኑ ውስጥ የ (?) ምልክት በማድረግ ያልተረዳችኋቸውን ነጥቦች ደጋግማችሁ ከልሱ።

| ተ.ቁ | ማመሳከሪያ ነጥብ | (√) | (?) |
|---|---|---|---|
| 1 | ያዳመጥሁትን ምንባብ መልዕክት ተረድቻለሁ። | | |
| 2 | ካዳመጥሁት ምንባብ ዝርዝር ሀሳቦችን አውጥቻለሁ። | | |
| 3 | ሥርዓቱን ጠብቆ ንግግር አድርጌያለሁ። | | |
| 4 | ያነበብሁትን ምንባብ መልዕክት ተረድቻለሁ። | | |
| 5 | ለቃላት ተመሳሳይ ፍች ሰጥቻለሁ። | | |
| 6 | ለቃላት አገባባዊ ፍች ሰጥቻለሁ። | | |
| 7 | በመረጥሁት ርዕስ አንቀፅ ፅፌያለሁ። | | |
| 8 | የቴክኖሎጂ ውጤቶችን አገልግሎት ገልጫለሁ። | | |
| 9 | አዳዲስ ቃላትን በመጠቀም አረፍተነገሮችን ሠርቻለሁ። | | |
| 10 | የአረፍተ ነገሮችን ባለቤትና ማሰሪያ አንቀፅ ለይቻለሁ። | | |

# ምዕራፍ አራት: ወረርሽኝ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

**ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ የቀረበውን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-**

- አዳምጣችሁ የምንባቡን መልዕክት ትናገራላችሁ፡፡
- ከምንባቡ ዝርዝር መረጃዎችን ትለያላችሁ፡፡
- በተሰጡት ርዕስ ጉዳዮች ላይ ንግግር ታደርጋላችሁ፡፡
- የምንባቡን ዝርዝር ይዘቶች ለይታችሁ ታስረዳላችሁ፡፡
- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- በተሰጣችሁ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በመመስረት ዘገባ ትፅፋላችሁ፡፡
- የተሳሳቱ አረፍተነገሮችን አስተካክላችሁ ትጽፋላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ: ማዳመጥ

### የወባ በሽታ

መምህራችሁ "የወባ በሽታ" በሚል ርዕስ አጭር ፅሑፍ ያነቡላችኋል፡፡ እናንተም እያዳመጣችሁ ዋና ዋና ሀሳቦችን በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ፃፉ፡፡ በመቀጠልም የአዳምጦ መመለስ ጥያቄዎችን በቃላችሁ መልሱ፡፡ ከዚያ በፊት ግን ከታች የተሰጡትን የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች በቡድን ሆናችሁ ከተወያያችሁ በኋላ መልሶቹን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

#### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. የወባ በሽታ ምንድነው? ከጓደኞቻችሁ ጋር ከተወያያችሁ በኋላ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
2. በወባ በሽታ የታመመ ሰው ምን ምን አይነት ምልክቶች ያሳያል?

#### ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

**፩. በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. የበለፀጉ አገሮች የጤና አጠባበቅ ሁኔታ ካላደጉት አገሮች ይልቅ የተሻለ የሚሆነው በምን ምክንያት ነው?

ለ. ያላደጉ አገሮች መገለጫዎች ምን ምን ናቸው?

ሐ. ተላላፊ በሽታዎች በይበልጥ የሚያጠቋቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ተናገሩ፡፡

መ. በአፍሪካ በይበልጥ በወባ በሽታ የሚጠቁ ሀገሮች በየት አካባቢ የሚገኙ ናቸው?

ሠ. የወባ በሽታ ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፈው እንዴት ነው?

ረ. አንድ ሰው ወባ ወደሚከሰትበት አካባቢ ሲሄድ ማድረግ ያለበትን ቅድመ ጥንቃቄዎች ግለፁ፡፡

ሰ. የወባ በሽታ ምልክቶች ምን ምን ናቸው?

**፪. በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን የተጓደሉ ሀሳቦች አሟልታችሁ ጻፉ፡፡**

ሀ. የወባ በሽታ አምጪ ተህዋስያን ______________ እና ____________ በመባል ይታወቃሉ፡፡

ለ. የወባ በሽታ ካልታከሙት ሰውነትን _____ በተጨማሪ_______ ይዳርጋል፡፡

ሐ. ወባ አምጪ ተህዋስያን የሚራቡት _____________ እና _____________ ውስጥ ነው፡፡

መ. _____________ አልጋን መሸፈን የወባ በሽታን ለመከላከል ይረዳል፡፡

ሠ. በሰው ደም ውስጥ ለረጅም ጊዜ ተደብቆ የሚቆየው የወባ በሽታ አምጪ ተህዋስ ______ ይባላል፡፡

፫. ከዚህ በታች የተሰጡት ቃላት ካዳመጣችሁት ጽሑፍ የተወሰዱ ሲሆን ሁለት ሁለት ፍቺ ያላቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም በ"ሀ" ክፍል የተዘረዘሩትን ቃላት ከምንባቡ ውጭ የያዙትን ፍቺ መሰረት በማድረግ በ"ለ" ክፍል ከተዘረዘሩት ፍቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ድህነት | ሀ. በቁጥጥር ስር የዋሉ |
| 2. መጠበቅ | ለ. ንብረትን ማስከበር |
| 3. እየረገፈ | ሐ. ፈውስ ማግኘት |
| 4. የተያዙ | መ. መቆየት |
| 5. ማስመለስ | ሠ. እየወደቀ |

፬. ከዚህ በታች በተሰጡት ቃላት አረፍተ ነገር ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

| | |
|---|---|
| ሀ. የተዛባ | ረ. ህሊና |
| ለ. የበለፀገ | ሰ. ንክሻ |
| ሐ. አሽቆለቆለ | ሸ. ዑደት |
| መ. ጠንቅ | ቀ. ሥፍራ |
| ሠ. ሳትገላገል | በ. መከለያ |

## ክፍል ሁለት፡ ንግግር

ተማሪዎች! ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል ብሎም ለማጥፋትና ጤናማ የህብረተሰብ ክፍል ለመፍጠር ከመንግስትና ከዜጎች ምን ምን ተግባራት ይጠበቃሉ? አምስት አባላት ያሉት ቡድን መስርታችሁ መረጃ ከሰበሰባችሁ በኋላ ለክፍሉ ተማሪዎች በንግግር አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሦስት፡ ንባብ

### ወረርሽና ስነልቦናዊ ምላሾች

**የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

1. በአካባቢያችሁ ወረርሽኝ ተከስቶ ያውቃል?
2. በቅርብ የሰማችሁት ወይም የደረሰ ወረርሽኝ ካለ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ? ምን ምን ጉዳት አስከትሏል?

የወረርሽኝ በሽታዎች ከሰው ወደሰው፣ ከእንስሳት ወደሰው፣ ከሰው ወደእንስሳትና ከእንስሳት ወደእንስሳት በፍጥነት የሚተላለፉና ለመቆጣጠርም በጣም አዳጋች የሆኑ ህመሞች ናቸው፡፡ የሰው ልጆች በመላው ዓለም እየተስፋፉ ሲሄዱ ተላላፊ የሆኑ በሽታዎችም በዚያው ልክ ሊስፋፉ ችለዋል፡፡ አሁን ባለንበት ዘመን እንኳ ወረርሽኝ ሊያስብል በሚችል ስፋት የሚስፋፉ በሽታዎች በብዛት ባይኖሩም፣ ከቅርብ ወራት ወዲህ ግን መነሻው ያልታወቀ ኮሮና ቫይረስ (ኮቪድ-19) በሽታ በዓለማችን ላይ በፍጥነት እየተስፋፋና ብዙዎችን ለሞት እየዳረገ፤ የዓለም ህዝብ ራስ ምታት ለመሆን በቅቷል፡፡

ከወረርሽኝ በሽታዎች ለመከላከልም ሆነ ለመፈወስ የሰው ልጅ በየዘመኑ እንደ አካባቢው ሁኔታ የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ለምሳሌ እ.አ.አ ከ1918 እስከ 1919 በሀገራችን የተከሰተው ወረርሽኝ በርካታ ሰዎችን እንደገደለና በበሽታው የተያዙትን ለማዳን ባህላዊ የሕክምና ዘዴዎችን ህብረተሰቡ ተጠቅሞ እንደነበር ይነገራል፡፡ እንዲህ ያለው ታሪክ ውስጥ አንድ ታላቅ ነገር እናገኛለን፡፡ ለመሆኑ በወረርሽኙ በጠቅላላ የሞቱትን ማን ገደላቸው? ወረርሽኙ በሽታ ብቻውን ገደላቸው ወይስ ስነ-ልቦናዊ ተፅዕኖ ተደምሮ ገደላቸው? እነዚህን ለመሳሰሉት ጥያቄዎች ሁሉም በየራሱ አስተሳሰብ ላይ ተመርኩዞ አስተያየት ይሰጣል፡፡

**የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች**

1. የስነ-ልቦናው ዓለምስ ስለ ወረሽኝ በሽታዎች ምን የሚል ይመስላችኋል፡፡
2. ኮቪድ-19 ምን አይነት ስነልቦናዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

የስነልቦናው ዓለምስ ስለ ወረርሽኝ በሽታዎችና ስነልቦናዊ የመከላከል አቅም ምን ይላል? እንደሚታወቀው ማሰቢያና ማገናዘቢያ አእምሮአችን በአንጎላችን ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣ አንጎላችን ደግሞ አንዱ የሰውነት ክፍላችን እንደመሆኑ መጠን ማናቸውም በሽታዎች/ወረርሽኖች የተለያዩ አካላት

ክፍሎችን ሲያጠቁ በተመሳሳይ አዕምሮን ማጥቃታቸው የማይቀር ነው፡፡ በቀላሉ ብናስበው እንኳዋን፤ በሽታው/ወረርሽኙ መኖሩን ለማወቅ «ተይዣለሁ ወይስ ነጻ ነኝ» የሚለውን ለማረጋገጥ አዕምሮአችን ንቁ መሆን አለበት፡፡ ወረርሽኙ መኖሩን አዕምሮአችን ካወቀ በኋላም በቅድሚያ የሚደርስበት አሉታዊ ተጽዕኖ "በበሽታው ብያዝስ" የሚል ፍርሃት ነው ፡፡«ብያዝ» በሚል ብቻ ሳያበቃ ከተያዝኩ በኋላ በለይቶ ማቆያ ውስጥ እቀመጣለሁ፤ ከቤተሰብ እለያለሁ፤ እገለላለሁ የሚሉ ሌሎች ፍርሃቶችን ያስከትላል፡፡ እነዚህን ፍርሃቶች ከሚያባብሱት ምክንያቶች ውስጥም ያልተጣሩ መረጃዎችን መስማት፤ በቂ መረጃ ማጣት፤ መድሃኒቱ ተገኘ-አልተገኘ ሃሳብ፤ የቤተሰብ አባላት በወረርሽኙ ተጠቁ-አልተጠቁና የመሳሰሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በሂደትም ሰዎችን ለጭንቀትና ድብርት ይዳርጋሉ፡፡ እዚህ ላይ አስገራሚው ነገር በለይቶ ማቆያ ውስጥ በበሽታው ተጠርጥረው ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ ሰዎች በሂደት የወረርሽኙን ምልክቶች በማሳየት በበሽታው ሳይያዙ የተያዙ ይመስላቸዋል፡፡ ለምሳሌ፡- የወረርሽኙ ምልክት የሰውነት ሙቀት መጨመር ከሆነ፤ ግለሰቦች በፍርሃትና ጭንቀት ውስጥ ሲሆኑ ሲሮቶኒን የተሰኘው የአዕምሮ ኬሚካል ይቀንሳል፡፡ የኬሚካሉ መቀነስ የሰውነት ሙቀትን የማመጣጠን ስራን ያስተጓጉላል፡፡ በጭንቀት ምክንያት ብቻ የሰውነት ሙቀት በመጨመር ከዋናው በሽታ ጋር ተቀራራቢ ምልክት ግለሰቡ(ዋ) ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡

ፍርሃቱ ላይ ተመስርቶ ሌላኛው ተጽዕኖ የሚሆነው፤ ማህበራዊ ትስስሮሽን ማላላትና በቀናት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ማቋረጥ ነው፤ እርስ በእርስ ያለንን መተማመን የሚሰብርና "ያንተ ቤት ሲንኳኳ ይሰማል የኔ ቤት" የሚለውን ብሂል በሚያስዘነጋ ዓይነት ፡፡ በተለይም ማህበራዊ ድጋፍ የሚሰጡ እንደ እምነት ተቋማትና በሃገራችን የቡና ጠጡ ስርዓቶች ላይ የሚገኘው ሰው ወረርሽኙ እንዳይስፋፋ በሚል ስለሚገደብ የባሰውን ማህበራዊ ትስስሮሹ እየላላ ይሄዳል፡፡ በዚህ አይነቱ መላላት ውስጥ የወረርሽኙ ተጠቂ ናቸው የተባሉትን ግለሰቦች አንዳንዴም ሃገራት የተወሰኑ ቦታዎችን የማግለል ነገር ይከሰታል፡፡

ሌላኛው ተጠቃሽ ስነልቦናዊ ተጽዕኖ የሚከሰትባቸው የጤና ባለሙያዎች ናቸው፡፡ ባለሙያዎቹ ረጅም ሰዓት በስራ ላይ ከመቆየታቸው በወረርሽኙ የተነሳ ሰዎች ሲሞቱና በህመም ሲሰቃዩ በተደጋጋሚ በማየታቸውና በቂ የህክምና ግብዓት ካለመኖር የተነሳ የመዳከም፣የመሰላቸት፣የድብርት፣ ተስፋ የመቁረጥ... ምልክቶች ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ ታዲያ ባለሙያዎች በዚህ ከቀጠሉ በህክምና ስራቸው ውጤታማ ካለመሆናቸውም በላይ በቀላሉ ወረርሽኙም ወደ እነሱ ሊተላለፍ ይችላል፡፡ ግለሰብም በህክምና ስርዓቱ ላይ እምነት በማጣት የጤና ተቋማትን መጠቀም ይፈራል፡፡ በወረርሽኙ ቢያዝም እራሱንም ከማጋለጥ ይቆጠባል፡፡ በተጨማሪም መዘንጋት የሌለብን ግለሰብ ራሱን ሊደብቅበት የሚችልበት ሌላኛው ምክንያት መገለልን ካለመፈለግም ይሆናል፡፡ ከላይ እንዳልነው ማናቸውም ወረርሽኞች ሲከሰቱ የፍርሃት፣ የጭንቀት፣ የድብርት፣ ተስፋ የማጣት፣ የመገለል ወይም የማግለል... አሉታዊ ተጽእኖዎች ይከሰታሉ፡፡ ይሁንእንጅ በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ላይም የሚስተዋለው ይሄ ቢሆንም ተጨማሪ ነገሮንችም አያጣም ፡፡ ከሁሉ በፊት ሲያከናውናቸው ከነበሩ ተግባራት ራሱን እንዲገታ ያደርገዋል፡፡ በፊት አቅፍ ድግፍ አድርገን፤ አገላብጠን እንስማቸው የነበረሩትን አሁን ላይ ለመጨበጥ እንኳን እንድንፈራቸው ያደርገናል፡፡ ለጉንፋንም ሆነ ለተለያዩ የመተንፈሻ አካላት ህመም ማሳል ከባድ ይሆናል፡፡ካሳሉም ኮቪድ-19 እንዳልያዛቸውና ይልቁንም የቲቪ ህመም እንደሆነ መንገር ከመገለል እንደሚያድን እንደቀልድ ሲነገር ይሰማል፡፡ ይሄም ወረርሽኙን እጅግ አስፈሪ ገፅታ እንዲላበስ አድርጎታል፡፡



ሥዕል 6፡ ዙሪያውን በኮቪድ 19 ቫይረስ የተከበበና ማስክ የሰበሰ የአለም ካርታ

ሆኖም የስነ-ልቦና ባለሙያዎች እንደሚሉት ከሆነ፤ ወረርሽኝ በሚቀሰቀስበት የመጀመሪያዎቹ ሰሞን ወረርሽኙን በከፍተኛ ሁኔታ አጋኖ ማቅረብና ብዙ ሲቆይ ደግሞ እንደ ቀላልና አሌ የማይባል ነገር መውሰድ ሰዋዊ ባህርይ ነው። ለምሳሌ ኤችአይቪ ኢትዮጵያ ውስጥ በገባበት ወቅትና አሁን ላይ ያለውን የበሽታው ግንዛቤ ማየት ለዚህ ምሳሌ ይሆናል። እንዲህ ያሉት በወረርሽኙ መከሰት የመጀመሪያ ጊዜያት የሚስተዋሉ ስነ-ልቦናዊ ከፍተኛ ሽብሮች በሰዎች ላይ ድንገተኛ መርበትበት ከወረርሽኙ ለማምለጥ ከመፈለግ የሚመጣ የገነነ ራስ ወዳድነትና የተለያዩ የህክምናና ተጓዳኝ ግብኣቶችን ለማግኘት የሚደረግ አላስፈላጊ ግብግብ ያስከትላሉ።

በአጠቃላይ ስነልቦናዊው ተጽእኖ በተመለከተ ይህን ያህል ካልን  ኮቪድ-19ን ለመከላከል ከአካላዊ (ስነ-ህይወታዊ) ህክምና በተጓዳኝ ስነ-ልቦናዊ ድጋፎችን መስጠት አስፈላጊ ይሆናል። እዚህ ላይ በጥቅሉ ሁለት አይነት ስነ-ልቦናዊ ድጋፍ ቢሰጥ የተሻለ እንደሚሆን የሚመክሩ አሉ። አንደኛውና የመጀመሪያው የግለሰቦችን ፍርሃት ከሚጨምሩ ተግባራት ራስን መከልከል ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ተጨማሪ የሰውን አእምሮኣዊ ጤና ማስጠበቅ የሚችሉና ራስን ለማረጋጋት የሚያስችሉ ተግባራትን እንዲፈጽም ማስቻል ነው። በሌላ አነጋገር አሉታዊ ነገሮችን ማስወገድና አዎንታዊ ነገሮችን መጨመር እንደማለት ነው።

(ኖኅ ውብሸት፤ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ስነ-ልቦናዊ ምላሾች (2012) ለማስተማር እንዲያመች ሆኖ የተወሰደ)

## ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

**ሀ. የምንባቡን ሀሳብ መሠረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃል ምላሽ ስጡ።**

1. የወረርሽኝ በሽታዎች ባህሪ ምን ምን ዓይነት ናቸው?
2. የወረርሽኝ በሽታዎችን ለመከላከል የሰው ልጅ በየዘመኑ ያደረጋቸው ጥረቶች ምን ምን ነበሩ?
3. ኮቪድ-19ን በተመለከተ የተጠቀሱት ስነልቦናዊ ተፅዕኖዎች ምንምን ናቸው?
4. የማህበራዊ ትስስሮሽ መላላትን ለማሳየት በምሳሌነት የተጠቀሱት ምንምን ናቸው?
5. በፍርሃትና ጭንቀት ምክንያት የሰውነት ሙቀት ሊጨምር የሚችለው እንዴት ነው?

## ክፍል አራት፡ ቃላት

፩. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት በምንባቡ መሰረት አገባባዊ ፍቺ ስጧቸው፡፡

1. መገለል
2. ጥረት
3. ግብግብ
4. ማጋለጥ
5. ተመረኮዘ
6. ግብኣት
7. አባባሰ
8. መርበትበት
9. ገጽታ
10. አቅም

፪. በ "ሀ" ክፍል የቀረቡትን ቃላት በ "ለ" ክፍል ከቀረቡት ተመሳሳዮቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ማጋለጥ | ሀ. ዝግጁ |
| 2. አጋኖ | ለ. ጎዳ |
| 3. አሉታዊ | ሐ. ተጨማምሮ |
| 4. ንቁ | መ. አሳልፎ ሰጠ |
| 5. ማላላት | ሠ. ማሳወቅ |
| 6. ጻረገ | ረ. የሚዛመድ |
| 7. በርካታ | ሰ. ጨማምሮ |
| 8. አጠቃ | ሸ. ብዙ |
| 9. ተቀራራቢ | ቀ. አፍራሽ |
| 10. ተዳምሮ | በ. መቀነስ |

## ክፍል አምስት:- ጽሕፈት

### የዘገባ አጻጻፍ መመሪያ

ዘገባ አዘጋጅታችሁ በምታቀርቡበት ጊዜ ለሚከተሉት ጉዳዮች ትኩረት አድርጉ፡፡

1. ለዘገባችሁ ያሰባሰባችኋቸውን መረጃዎች በማመዛዘንና በማነጻጸር ሥርኣት ባለው መንገድ ተንትናችሁ ሀሳቡ ግልጽ እንዲሆንላችሁ አድርጉ ፡፡ ዘገባውን ከመጻፋችሁ በፊት አስተዋጽኦ አዘጋጁ፡፡
2. መረጃዎቻችሁን መነሻ በማድረግ በነደፋችሁት አስተዋጽኦ መሰረት የዘገባውን ዋና አካል ጻፉ፡፡
3. በዘገባው ውስጥ ተደጋጋሚና እርስበርስ የሚቃረኑ ሀሳቦች እንዳይኖሩ ጥንቃቄ አድርጉ፡፡
4. ዘገባውን ቀላልና ግልጽ በሆነና በማያሰለች ቋንቋ ጻፉ፡፡
5. መረጃዎቻችሁን ስታሰባስቡ ያጋጠሟችሁን ችግሮችና የተጠቀማችሁባቸውን መፍትሄዎች የሚጠቁም መግቢያ በመጨረሻም አጠር ያለ ማጠቃለያ ጻፉ፡፡

6. በዘገባ ጽሁፉ የመጀመሪያ ገጽ መሀል ላይ የዘገባውን ርእስ ጻፉ፡፡
7. በዚሁ ገጽ ላይ ከርእሱ ስር የዘጋቢውን/ዘጋቢዎችን ሥም ጻፉ፡፡
8. በዚሁ ገጽ የቀኝ ግርጌ ዘገባው የተጻፈበትን ቀንና ቦታ ጻፉ፡፡

፩. በሀገራችን ከኮሮና በሽታ መከሰት ጋር ተያይዞ በርካታ ችግሮችን ማለፋችን ይታወቃል፡፡ በኮሮና ምክንያት ትምህርት ቤቶች ተዘግተው ነበር፤ ቤት እንድንቀመጥ ተደርገን ነበር፣ በትራንስፖርት አጠቃቀም ላይ ህግ ወጥቶ ነበር፤ ወዘተ. ፡፡

እናንተም የኮሮና ወረርሽኝ በተከሰተበት ወቅት ምን ተሰምቷችሁ እንደነበር፣ በአካባቢያችሁ በወቅቱ ምን ምን ሲደረግ እንደነበር፣ ባጠቃላይ ያንን የውጥረት ጊዜ እንዴት እንዳሳለፋችሁት፣ ወዘተ. በመግለፅ ዘገባ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡ ዘገባውን መፃፍ ከመጀመራችሁ በፊት ከላይ የቀረበውን የዘገባ አፃፃፍ መመሪያ ተመልከቱ፡፡

## ክፍል ስድስት፡-ሰዋስው

ቀጥሎ ከምንባቡ የተወሰዱ ሀረጎችና አረፍተነገሮች ቀርበዋል፡፡ በእነዚህ ሀረጎችና አረፍተ ነገሮች ውስጥ የምታዩአቸውን ስህተቶች፤ በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ትክክለኛ ቀርፅ በመፈለግ እንደገና አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡ መምህራችሁ በአረፍተ ነገር ውስጥ ስለሚከሰቱ የስህተት አይነቶች ያስረዷችኋል፡፡

ምሳሌ፡- በበሽታው ተይዣለሁ እንጂ ነጻ ነኝ፡፡ (ይህ ስህተት ያለበት አረፍተነገር ነው፡፡)

ስህተቱ የተፈጠረው እንጂ የሚለው አያያዥ ቃል ያለቦታው በመግባቱ ነው፡፡)

በበሽታው ተይዣለሁ ወይስ ነጻ ነኝ? (ተስተካክሎ የተጻፈ አረፍተነገር ነው)

1. ለመቆጣጠር በጣም አዳጋች የሆነ ህመሞች ናቸው፡፡
2. የሰው ልጅ በመላው አለም እየተስፋፉ ሄዱ፡፡
3. ተላላፊ የሆኑ በሽታዎች በዛው ልክ ሊስፋፋ ችለዋል፡፡
4. የአለም ህዝብ ራስ ምታት ለመሆን በቅቶታል፡፡
5. የሰው ልጅ በየዘመኑ እንደ አካባቢው ሁኔታ የተለያዩ ጥረቶችን ሊያደርግ ቆይቷል፡፡
6. ባህላዊ የህክምና ዘዴዎችን ህብረተሰቡ ተጠቅሞ እያለ ይነገራል፡፡
7. በሂደትም ሰው ለጭንቀትና ድብርት ይዳረጋሉ፡፡
8. የጤና ተቋሙ መጠቀም ይፈራል፡፡
9. ግለሰብ ራሱን ሊደብቅ የሚችልበት ሌላኛው ምክንያት መገለልን ከመፈለግም ይሆናል፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ማዳመጥንና ንግግርን ለማስተማር የቀረበው "የወባ በሽታ" የተሰኘ ጽሑፍ ነው:: ጽሑፉ የወባ በሽታ ፕላዝሞዲየም በሚባል ተህዋስ አማካኝነት የሚከሰት መሆኑን፤ ከሰው ወደሰው የሚተላለፈው ደግሞ "አናፊሊስ" በተባለችው ሴት የወባ ትንኝ ንክሻ አማካኝነት መሆኑን፤ የወባ በሽታ ካልታከሙት ሰውነትን በማጎሳቆል ለሞት የሚዳርግ አደገኛ በሽታ መሆኑን ያስገነዝባል:: ስለሆነም የወባ በሽታ ምልክቶችን ከተመለከትን በፍጥነት ወደህክምና መሄድ ይኖርብናል:: ምንባቡን ተከትሎ የቀረቡ የአዳምጦ መመለስ ጥያቄዎችም ዝርዝር መረጃዎችን ለማውጣት የሚያስችሉ ሆነው ቀርበዋል::

በንግግር ክሂል ስር ወባንና ሌሎች ተላላፊ በሽታዎችን በመከላከልና በማጥፋት ረገድ መንግስትና ዜጎች ርብርብ ማድረግ እንዳለባቸው ሰፊ ውይይት ተደርጓል::

ለንባብ ክሂል ማስተማሪያነት የቀረበው ምንባብ "ወረርሽኝ" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው:: ወረርሽኞች በዓለማችንና በሀገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት ተከስተዋል:: የወረርሽኞችን መከሰት ተከትሎ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ልዩ ልዩ ምላሾችን ሰጥተዋል:: በሌላ በኩል የተከሰተውን ወረርሽኝ በመፍራት የመሸሽና የመገለል ሁኔታዎችም ተከስተዋል:: በሽተኛን በሚያገሉ ማህበረሰቦች ውስጥ ታማሚዎች መገለልን በመፍራት ህመማቸውን ይደብቃሉ:: ይህም ለበሽታዎች መስፋፋት የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል:: ምንባቡን ተከትሎ ለወጡት ጥያቄዎች በቂ ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቷል::

ዘገባ ለመጻፍ የሚያስችሉ መመሪያዎችም በቅደም ተከተል ቀርበዋል:: በመመሪያው መሰረት በቀረበው ርዕሰጉዳይ ላይ መረጃ በመሰብሰብ የጽሑፍ ዘገባ ማዘጋጀት ተችሏል::

በመጨረሻም በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚታዩ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን አስተካክለን ፅፈናል:: በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚከሰቱ ሰዋስዋዊ ስህተቶች የባለቤትና ማሰሪያ አንቀጾች በቁጥር፣ በፆታና በመደብ አለመስማማት ይገኙበታል::

### የክለሳ ጥያቄዎች

1. "የወባ በሽታ" በሚል ርዕስ የቀረበው ፅሑፍ መልዕክት ምንድን ነው ? ባጭሩ ግለፁ::
2. የወባ በሽታ የሚራባው እንዴት ነው ?
3. "ጠንቅ፣ ንክሻ፣ ውደት" የሚሉትን ቃላት ፍች ግለፁ::
4. "እጋኖ፣ አጠጋ፣ ግብግብ" ለሚሉት ቃላት ተቃራኒ ፍች ስጡ::
5. የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች አስተካክላችሁ እንደገና ፃፉ::

   ሀ. ምንባብ መልዕክት ያዳመጥሁትን እችላለሁ መናገር::

   ለ. በፍጥነት ገባ ሩጫ ተራምዶ::

   ሐ. ትምህርት ሴቶች አለባቸው መማር::

## ክፍል ሰባት:- የግንዛቤ ማመሳከሪያ ነጥቦች

ከዚህ በታች በምዕራፉ የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች ምን ያህል እንደተረዳችኋቸው ለማረጋገጥ የሚረዱ ማመሳከሪያ ነጥቦች ተዘርዝረዋል:: በመሆኑም ዝርዝሮችን በጥንቃቄ በማንበብ፤ ተረድታችኋቸው ከሆነ ከፊትለፊታቸው ባለው ሳጥን ውስጥ የ(V) ምልክት በማድረግ አረጋግጡ:: ያልተረዳችሁት ወይም የሚያጠራጥራችሁ ከሆነ ግን በሳጥኑ ውስጥ የ (?) ምልክት በማድረግ ያልተረዳችኋቸውን ነጥቦች ደጋግማችሁ ከልሱ::

| ተ.ቁ | ማመሳከሪያ ነጥብ | (√) | (?) |
|---|---|---|---|
| 1 | ያዳመጥሁትን ምንባብ መልዕክት ተናግያለሁ:: | | |
| 2 | ካዳመጥሁት ምንባብ ዝርዝር መረጃዎችን ለይቻለሁ:: | | |
| 3 | በቀረቡት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ንግግር አድርጌያለሁ:: | | |
| 4 | የምንባቡን ዝርዝር ይዘቶች ለይቼ አስረድቻለሁ:: | | |
| 5 | በተሰጠኝ ርዕስ ዘገባ ፅፌያለሁ:: | | |
| 6 | ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ሰጥቻለሁ:: | | |
| 7 | ለቃላት ተመሳሳይ ፍች ሰጥቻለሁ:: | | |
| 8 | በቀረበው ርዕስ ላይ ዘገባ ፅፌ አቅርቤያለሁ:: | | |
| 9 | የተሳሳቱ አረፍተነገሮችን አስተካክዬ ፅፌያለሁ:: | | |

# ምዕራፍ አምስት: አካታችነት

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- አዳምጣችሁ ዝርዝር መረጃዎችን ትለያላችሁ።
- በቀረበው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ክርክር ታደርጋላችሁ።
- አንብባችሁ የምንባቡን ጭብጥ ትለያላችሁ።
- አንብባችሁ የምንባቡን ይዘት ትለያላችሁ።
- ከምንባቡ ለወጡ ልዩልዩ ጥያቄዎች መልስ ትሰጣላችሁ።
- ከምንባቡ ለወጡ አዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ።
- ሴቶች በማህበራዊ ና ትምህርት ረገድ የደረሰባቸውን ተጽእኖ በፅሑፍ ይዘረዝራሉ።
- በቀረበላችሁ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ዝርዝር ነገሮችን ትፅፋላችሁ።
- በተመረጠ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ገላጭ ድርሰት ትፅፋላችሁ።
- የተዘበራረቁ ቃላትን በማስተካከል ትክክለኛ አረፍተነገር ትመሰርታላችሁ።

## ክፍል አንድ:- ማዳመጥ

### የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ

ተማሪዎች! መምህራችሁ "የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ" በሚል ርዕስ የሚያነቡላችሁን አጭር ጽሑፍ በጥሞና እያዳመጣችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ ደብተራችሁ ፃፉ።ምንባቡን ከማዳመጣችሁ በፊት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩና ሀሳባችሁን ለክፍሉ ተማሪዎች ተናገሩ።

#### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

የቀደመ ዕውቀታችሁን መሰረት በማድረግ ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ።

1. ሴቶችና ወንዶች እኩል የትምህርት ተሳትፎ ያላቸው ይመስላችኋል? ለመልሳችሁ ማስረጃ በቃል አቅርቡ።
2. በሀገራችን ሴት ልጅን አስመልክቶ ያሉ አስተያየቶች ምን ምን ናቸው? ለመምህራችሁ በቃላችሁ ተናገሩ።

#### ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት መልሱ።

ሀ. በዓለም ካልተማሩት የሕብተሰብ ክፍሎች መካከል የሴቶች ቁጥር ከፍ ያለ ነው።

ለ. በማህበረሰቡ ውስጥ ወንዶች የተሻለ ስራ ይሰራሉ ተብሎ ይታመናል ።

ሐ. ሴቶችን ወደ ትምህርት ቤት ከመሄድ ያገዳቸው የቤተሰብ ሃላፊዎች ስለሆኑ ነው።
መ. በሀገራችን ከ1981 ወዲህ የሴቶችን እኩልነት ለማረጋገጥ የሚረዱ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል።
ሠ. ወንዶች ለሴቶች ተብለው የተተው ስራዎችን ለመስራት አይገደዱም።
ረ. ወንዶች በሴቶች ላይ የስራ ጫና እንዲፈጠር አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።
ሰ. በሀገራችን ሴቶች ከወንዶች እኩል የመማር መብት የተደነገገው በ1981 ነው።
ሸ. የ2015 ድንጋጌ ሴቶችን በትምህርት መስክ መገለልን ይቃወማል።
ቀ. ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ የሃገራችን ሴቶች የኢኮኖሚ ተሳትፎ በ10% ጨምሯል።
በ. በአሁኑ ሰዓት በሀገራችን በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለው የትምህር ተሳትፎ ልዩነት ጠቧል።

፪. ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ የሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ምንባቡ የሚያስተላልፈውን መልዕክት በአጭሩ ግለፁ።
ለ. "ሴት ወደማጀት፣ ወንድ ወደችሎት" የሚለው ብሂል በሴቶች ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ምንድነው?
ሐ. በሀገራችን የሴቶችን እኩልነት ለማረጋገጥና በትምህርት መስክ የተደረጉት ጥረቶች ምን ምን እንደሆኑ አስረዱ።
መ. በኢትዮጵያ በሥርዓተጾታ ረገድ ያሉትን ልዩነቶች ለማስወገድ የተደረጉ ጥረቶችና ውጤታቸው ምን ይመስላል?
ሠ. ሴቶችንና ወንዶችን እኩል የማስተማር በሁሉም የዓለም ክፍሎች ያለው ልምድ ምን ይመስላል? አብራሩ።

## ክፍል ሁለት፡ ንግግር

፩. "ለሴቶች የተለየ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል ወይም አያስፈልግም" ከሚለውን ሀሳብ አንዱን በመደገፍ ወይም በመቃወም ተከራከሩ። ለመከራከር ቀጥሎ የተጠቀሱትን መመሪያዎች ከግምት ውስጥ አስገቡ።

### ክርክር ለማድረግ ስንዘጋጅ የምንከተላቸው ነጥቦች

- የክርክሩን ርዕሰ ነገር በበቂ ሁኔታ መረዳት
- ለክርክሩ በቂ ዝግጅት ማድረግ
- ንግግራችንን የተመጠነና ግልፅ ማድረግ
- ተራን ጠብቆ መናገር
- ከተከራካሪው ለሚቀርበው ሃሣብ አጥጋቢ ምላሽ በመስጠት ማሣመን
- ለሌላው ሀሳብ ዋጋ መስጠት/ማክበር
- ክርክሩን የሚመሩ ሰዎች መምረጥ

፪. ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ በተጠቀሱት ዓመታት የሴቶችን ተሳትፎ ለማሻሻል ደረጃው የተባሉ ልዩ ልዩ እርምጃዎች ተወስደዋል። እናንተም እነዚህን ልዩ ልዩ ጥረቶች የሚያሳዩ ዝርዝር ሃሳቦችን በተተውት ባዶ ቦታዎች ውስጥ አሟልታችሁ ጻፉ።

| በ1981 | በ1990 | በ1995 | በ2005 | በ2015 |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

## ክፍል ሦስት፡ ማንበብ

### ፀሐይና ተግዳሮቶቿ

**ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

የቀድሞ ዕውቀታችሁን መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ መልስ ስጡ።

1. የልዩ ፍላጎት ትምህርት ማለት ምን ማለት ነው?
2. ልዩ ትኩረት የሚሹ ተማሪዎች ምን አይነት ችግር ያለባቸው ናቸው?

… የአሥራ አንደኛ ክፍል የእንግሊዝኛ ትምህርት ከምታስተምረው መምህርት ጕን የቀመችው የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ትምህርቱን መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች ታስተረጉማለች። የ24 ዓመቷ ፀሐይ ግን ትምህርቱን በትኩረት እየተከታለች አልነበረም። የተበላሸባትን የአንደኛ ሴሚስተር ውጤት እያሰላሰለች ነበር።

ፀሐይ እስከ 12 ዓመቷ ድረስ የዓይን ብርሃኗ አብሯት ነበር። ከዚያ በኋላ ግን ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ ዕይታዋ ይደበዝዝ ጀመር። በመጨረሻም ሙሉ ብርሃኗን አጣች። ሆኖም በደረሰባት ችግር ተስፋ ቆርጣ ጓዳ አልተቀመጠችም። ትምህርት ቤት ገብታ መደበኛ ትምህርት ትማር ጀመር።

ነገር ግን ትማር የነበረው ማየት ለተሳናቸው ተማሪዎች ተብሎ በተዘጋጀ ብሬል አልነበረም። በብሬል አለመማሯ ችግር ይሆንብኛል ብላ አስባ አታውቅም ነበር። የክፍል ደረጃዋ እየጨመረ ሲሄድ ግን የሚያስጨንቃት ጉዳይ እየሆነ መጣ። ፀሐይ ‹‹እስከ አሥረኛ ክፍል የተማርኩት በትግል ነው፤›› በማለት ብሬል ማጣቷ ምን ያህል ዋጋ እያስከፈላት እንደሆነ ትገልጻለች። ሌላው አማራጭ መምህር ክፍል ገብቶ ሲያስተምር በመቅረፀ ድምፅ መቅዳት ቢሆንም መቅረፀ ድምፅም የላትም።

በእርግጥ ብሬል የተማሩትም ሆኑ መቅረፀ ድምፅ ያላቸው ማየት የተሳናቸው ተማሪዎች፤ ፈተና ለመፈተን የግድ የሌላ ሰውን ዕርዳታ ይሻሉ። የፈተና ጥያቄዎችን የሚያነብላቸውና የሚነግሩትን መልስ የሚጽፍላቸው ሰው ያስፈልጋቸዋል። ነገር ግን ለማጥናት አይቸገሩም።

ፀሐይም ዋናው ችግሯ ለፈተና ዝግጅት የሚያነብላት ሰው ማጣት ነው። ብሬል ላይ የተጻፈ ማስታወሻ ወይም መምህሩ ያስተማራቸውን ቁርጣ የምታደምጥበት መቅረጸ ድምፅ የላትምና ለፈተና ለመዘጋጀት ትቸገራለች። ‹‹የማጠናው የሰዎች ጥገኛ ሆኜ ነው፤›› የምትለው - ፀሐይ፤ ፈተና በደረሰ ጊዜ ሁሉ የምታውቃቸውን ሰዎች እንዲያስጠኗት መለማመጥ ግድ ይላታል።

አንዳንዶቹ ፈቃደኛ ሆነው ቢያስጠኗትም እሷ በምትፈልገው መጠን የሚያነብላት ሰው ግን አታገኝም። በዚህም ዕውቀት ሳያንሳት ማጥናት ባለመቻሏ ብቻ ፈተና እንዳትሠራና ጥሩ ውጤት እንዳታስመዘግብ ሆናለች። ያለፈው ሴሚስተር ውጤቷም የተበላሸው ለፈተና ዝግጅት የሚያነብላት ሰው ባለማግኘቷ ነው። ይህንን ሁሉ ችግሯን የሚቀርፍላትን መቅረፀ ድምፅ ማግኘት ካልቻለች ትምህርቷን አቋርጣ ብሬል ለመማር መቁረጧን ትናገራለች።

### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ማየት ከተሳናቸው ተማሪዎች በተጨማሪ ልዩ ድጋፍ የሚፈልጉ ተማሪዎችን ዘርዝሩ።
2. ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ሊደረጉላቸው የሚገቡ ድጋፎች ምን ዓይነት ናቸው?

ማየት ከተሳናቸው ተማሪዎች በተጨማሪ፣ የየትምህርት ቤቶችን አሰልቺ ደረጃዎች ለመውጣት የሚቸገሩ አካል ጉዳተኞችም ብዙ ናቸው። የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ባለመኖሩ መምህሩ የሚለውን ሳይሰሙ ክፍል ውስጥ የሚቀመጡ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎችም ጥቂት አይደሉም።

በሀገራችን የኦቲዝም ተጠቂዎችን የሚቀበሉ ትምህርት ቤቶች ውስን በመሆናቸው የትምህርት ዕድል ለማግኘት ለዓመታት የሚጠባበቁ በርካታ ናቸው።

በሀገራችን ልዩ ትኩረት የሚሹ ተማሪዎች ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ተቀላቅለው መማር የሚያስችላቸው የአካቶ ትምህርት ትግበራ ከተጀመረ ሰነባብቷል።

አካቶ ትምህርት እክል ያለባቸውን ልጆች ልዩ ልዩ ፍላጎቶች ለማሟላት፣ አስፈላጊ በሆነ መልኩ፣ በልዩ ሁኔታ የተዘጋጀ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ማቅረብ ነው። እክል ያለባቸው ተማሪዎች የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ናቸው። እነዚህ እክል ያለባቸው ተማሪዎች በተቻለ መጠን በመደበኛ ትምህርት ቤት፣ እክል ከሌለባቸው ልጆች ጋር አብረው እንዲማሩ ይመከራል። ነገር ግን የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ያለባቸው እክል፣ እክል ከሌለባቸው እኩዮቻቸው ጋር ለመማር የማያስችላቸው ከሆነ፤ በመደበኛው ሳይሆን በልዩ ትምህርት ቤቶች እንዲማሩ ማድረግ የአካቶ ትምህርት ዓላማ ነው።

በየትምህርት ቤቶች አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የልዩ ፍላጎት ትምህርት ተማሪዎች ይኖራሉ። ተማሪዎቹም ማየት የተሳናቸው፣ መስማት የተሳናቸውና የእንቅስቃሴ ችግር ያለባቸው ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ተማሪዎች ከሌሎቹ ጋር ተቀላቅለው መማራቸው የመገለል ስሜት እንዳያድርባቸው ልዩ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል። በመሆኑም መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚዎች እንዲቀጠርላቸው፤ ማየት ለተሳናቸው ተማሪዎች የብሬል ወረቀት፣ ስታለስና ኬን እንዲቀርብላቸው፤ የእንቅስቃሴ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ደግሞ ተሽከርካሪ ወንበሮችና ሌሎች አስፈላጊ ድጋፎች ሊደረጉላቸው ይገባል።

የማየት፣ የመስማትና የእንቅስቃሴ ችግር ካለባቸው ተማሪዎች በተጨማሪ ያልታወቀ ችግር ያለባቸው፣ ወጣ ያለ ባህሪ የሚያሳዩ፣ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች ጋር የሚጋጩ ተማሪዎችም በልዩ ፍላጎት ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም ልዩ ድጋፍ የሚፈልጉ መሆናቸውን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

አካቶ ትምህርት ብዙ ጥሩ ጎኖች ቢኖሩትም መስተካከል ያለባቸው ብዙ ተግዳሮቶች አሉት፡፡ መስተካከል ካለባቸው ነገሮች ዋናው የአመለካከት ችግር ነው፡፡ መምህራን፣ ወላጆችና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች መማር እንደሚችሉና ትልልቅ ነገሮችን የማሳካት አቅም ያላቸው መሆናቸውን ማመን ይኖርባቸዋል፡፡

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ማየት የተሳናቸው፣ መስማት የተሳናቸው፣ የእንቅስቃሴ ችግር ያለባቸው፣ መናገር የማይችሉና የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸውን ልጆች ጓዳ ከመደበቅ ባለፈ ትምህርት ቤት የሚልኳቸው በጣት የሚቆጠሩ ዘመናዊ ወላጆች ብቻ ነበሩ፡፡ ባብዛኛው ራሳቸውን እንዲችሉ ስለማይደረጉም በአዋቂነት የዕድሜ ዘመናቸው እንኳ የቤተሰብ ጥገኛ ሆነው ለመኖር ይገደዳሉ፡፡

በተጨማሪም ልዩ ድጋፍ የሚሹ ልጆች፣ ያለባቸውን ችግር ሥር ሳይሰድ በጊዜ ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ወላጆች ሕፃኑ ማውራት፣ መዳህ፣ መሄድና ሌሎችንም ተፈጥሮአዊ ሂደቶች በወቅቱ አድርጓል ወይ የሚለውን በመከታተል፤ ልጆቻቸው የሚያሳዩትን ወጣ ያለ ባህሪ ተከታትለው መፍትሔ መፈለግ አለባቸው፡፡

(ምንጭ፡- ሻሂዳ ሁሴን፤ ፍላጎታቸው ያልሞላ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች፣ ሪፖርተር ጋዜጣ፤ የካቲት 2009፣ ማሻሻያ ተደርጎበት የተወሰደ)

## ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

፩. ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሰረት በማድረግ ከታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ፡፡

ሀ. የምንባቡን መልዕክት ባጭሩ ግለፁ፡፡

ለ. የ11ኛ ክፍል ተማሪ የሆነችው ባለታሪክ ውጤቷ የተበላሸው በምን ምክንያት ነው?

ሐ. ማየት ለተሳናቸው ተማሪዎች የሚያስፈልጉት ዋና ዋና የትምህርት ቁሶች ምን ምን ናቸው?

መ. ብሬል መማር ለምን ይጠቅማል?

ሠ. የአካቶ ትምህርት ዓላማ ምንድን ነው? አብራርታችሁ ግለፁ፡፡

ረ. በምንባቡ መሰረት በየትምህርት ቤቱ የሚገኙ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች የመገለል ስሜት እንዳያድርባቸው ምን መደረግ አለበት?

ሰ. የአካቶ ትምህርትን ውጤታማነት የሚያደናቅፉ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው?

ሸ. አንድ ህፃን ሲያድግ የሚያልፍባቸውን ተፈጥሯዊ የእድገት ሂደቶች ዘርዝራችሁ ግለፁ፡፡

፪. ከዚህ በታች የተሰጡትን ከምንባቡ የወጡ ሀረጎች በራሳችሁ አባባል አስረዱ፡፡

ሀ. በጣት የሚቆጠሩ

ለ. ሥር ሳይሰድ

ሐ. ወጣ ያለ

መ. ተስፋ መቁረጥ

ሠ. ትኩረት የሚሹ

## ክፍል አራት፡ ቃላት

፩. በምንባቡ መሰረት በ"ሀ" ክፍል የተዘረዘሩትን ቃላት በ"ለ" ክፍል ከተዘረዘሩት አውዳዊ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. እይታ | ሀ. አቻ |
| 2. ጓዳ | ለ. ጥቂት |
| 3. እርዳታ | ሐ. ችሎታ |
| 4. ቀርፃ | መ. ችግር |
| 5. ውስን | ሠ. ልመና |
| 6. መለማመጥ | ረ. ብርሃን |
| 7. መቁረጥ | ሰ. ድጋፍ |
| 8. እክል | ሸ. ቤት |
| 9. እኩያ | ቀ. መቅዳት |
| 10. ተሰጥኦ | በ. መወሰን |

፪. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቁሶች የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች በመማር ሂደት የሚገለገሉባቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ቁሶች ምን አይነት እክል ላለባቸው የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች እንደሚያገለግሉ እና አገልግሎታቸው ምን እንደሆነ የመጀመሪያውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ በጽሑፍ መልሱ፡፡

| የቁሳቁስ ስም | የትኞቹ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ይጠቀሙበታል? | ቁሳቁሶቹ ለምን ይጠቅማሉ? |
|---|---|---|
| ብሬል | ማየት የተሳናቸው | የብሬል ወረቀቱን አጣብቆ ለመያዝና መስመር ጠብቀው እንዲፅፉ ያግዛቸዋል፡፡ |
| ኬን | | |
| የብሬል ወረቀት | | |
| ስታይለስ | | |
| ተሽከርካሪ ወንበር | | |
| ክራንች | | |
| የእይታ መነፅር | | |
| ማዳመጫ መሳሪያ | | |

## ክፍል አምስት፡ ጽሒፈት

ከልዩ ፍላጎት ተማሪዎች መካከል የኦቲዝም ተጠቂዎች ይጠቀሳሉ፡፡ ኦቲዝም ምንድን ነው? ከሦሥት እስከ አምስት አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት የኦቲዝም በሽታ ምን ዓይነት ባህሪ እንዳለው ከተወያያችሁ በኋላ የተስማማችሁበትን ሀሳብ በጽሑፍ ግለፁ፡፡

## ክፍል ስድስት፡-ሰዋስው

በአማርኛ ትክክለኛው የአረፍተ ነገር አወቃቀር ህግ (ቀመር) ባለቤት - ተሳቢ - ግስ በመባል ይታወቃል፡፡ ማንኛውም ትክክለኛ አረፍተ ነገርም የሚዋቀረው ይህን ቀመር መሰረት በማድረግ ነው፡፡

ቃላት ለአረፍተ ነገር መመስረቻነት ሲውሉ የሚሰለፉበት የራሳቸው ቦታ አላቸው፡፡ በተሰለፉበት ቦታም የሚፈፅሙት ሰዋስዋዊ ተግባር አላቸው፡፡ ይህን ሁኔታ ግልፅ ለማድረግ ከቃላት መካከል የስምና ግስን መሰለፊያ ቦታና በሚሰለፉበት ቦታ የሚፈፅሙትን ተግባር እንመልከት፡፡ ስም በአረፍተ ነገር ውስጥ መጀመሪያ ላይ፤ ወይም ከግስ በፊት መሐል ላይ ይሰለፋል፡፡ በአረፍተ ነገር መጀመሪያ ላይ ከገባ የሚፈፅመው ተግባር የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ሆኖ ማገልገል ነው፡፡ በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ሰውና መምህር የሚሉትን ስሞች በአስረጅነት ተመልከቱ፡፡

1. ሰው ለመንንዣነት ባቡር ሠራ፡፡
2. መምህር ትውልድን ሲያንፅ ይኖራል፡፡

ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች ውስጥ ሰው እና መምህር የሚሉት ስሞች በአረፍተ ነገሮቹ መጀመሪያ ላይ በመሰለፍ እንደ ባለቤት አገልግለዋል፡፡ በአረፍተ ነገሮቹ ውስጥ የተፈፀሙትን ተግባራትንም ሲፈፅሙ ይታያል፡፡ በሌላ በኩል ስሞች በአረፍነገር ውስጥ ከግስ ቀድመው መሐል ላይ ሊገቡ ይችላሉ፡፡

3. አንበሳ ነብርን ገደለ፡፡
4. ልጅቱ ብርጭቆ ሰበረች፡፡

በተራ ቁጥር 3 እና 4 በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ስሞች የአረፍተ ነገሩ ተሳቢዎች ናቸው፡፡ ተሳቢ ማለት ተጠቂ፤ በግሱ የተገለፀውን ድርጊት ተቀባይ ማለት ነው፡፡ በዚህም መሰረት በጥያቄ ሦሥት ለተገለፀው የግድያ ድርጊት የተጠቃው (የሞተው) ነብር ሲሆን፤ በጥያቄ አራት በተገለፀው የሰበራ ድርጊትም የተሰበረው ብርጭቆ ነው፡፡ ድርጊቱን የፈፀሙት ደግሞ በአረፍተ ነገሮቹ መጀመሪያ ላይ በመግባት ባለቤት የሆኑት ስሞች ናቸው፡፡ ማለትም በተራ ቁጥር ሦሥት አንበሳ፤ በተራ ቁጥር አራት ደግሞ ልጅቱ የሚሉት ስሞች ድርጊቱን የፈፀሙ ባለቤቶች ናቸው፡፡

ግስ በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚሰለፈው ሁልጊዜም በአረፍተ ነገር መጨረሻ ላይ ነው፡፡ ከላይ ከአንድ እስከ አራት በቀረቡት ምሳሌዎች ውስጥ መጨረሻ ላይ የተሰለፉት ሁሉም ግሶች ናቸው፡፡ ግስ በአረፍተ ነገር መጨረሻ ላይ በመሰለፍ የአረፍተ ነገሩን አጠቃላይ ሀሳብ ያስራል፡፡ በዚህም ምክንያት ማሰሪያ አንቀፅ እየተባለ ይጠራል፡፡

፩. ቀጥሎ የተሰጡትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ ከታች የተሰጡትን የአገባብ ስህተት ያለባቸው አረፍተ ነገሮች በማስተካከል እንደገና ፃፏቸው፡፡

ምስሌ፡- .ሀ አዳኙ አንበሳውን ገደለው በጦር፡፡

ሲስተካከል፡- አዳኙ አንበሳውን በጦር ገደለው፡፡

ለ. የማንጎ ችግኝ ሰይፉ ተከለ፡፡

ሲስተካከል፡- ሰይፉ የማንጎ ችግኝ ተከለ፡፡

ሀ. ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ  ሱስ ውስጥ ይከታል፡፡

ለ.  ያስተሳሰብ ማንበብ አድማስን ያሰፋል ፡፡

ሐ.  ለእንስሳት ደን መኖሪያነት ያገለግላል፡፡

መ. ታላቁ የህዳሴ ለኢትዮጵያ ግድብ ኩራት ነው፡፡

ሠ. በማስታረቅ ሽማግሌው የተጣሉ ሰዎችን ይታወቃሉ፡፡

ረ. አቶ ሰይፉ ሾፌር የከባድ መኪና ነው፡፡

ሰ. ዓላማ ዩኒቨርሲቲ ገብታ ህግ የልጅቱ ማጥናት ነው፡፡

ሸ. ኢትዮጵያ ያላት አገር የራሷ ፊደል ናት፡፡

ቀ. ወላጆች ማስተማር ልጆቻቸውን  አለባቸው፡፡



## የምዕራፉ ማጠቃለያ

“የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ” በሚል ርዕስ የቀረበውን ጽሑፍ ተከትሎ ለቀረቡት የአዳምጦ መመለስ ጥያቄዎች ተገቢ መልሶች ተሰጥተዋል፡፡

የንባብ ክሂልን ለማስተማር የቀረበው ጽሑፍ ደግሞ “ፀሐይ እና ተግዳሮቶቿ” በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ ፀሐይ ማየት የተሳናት የ11ኛ ክፍል ተማሪ ነች፡፡ እስከ 10ኛ ክፍል ድረስ ስትማር በከፍተኛ ትግል ነበር፡፡ ፀሐይ 11ኛ ክፍል ከገባች ጀምሮ ለማጥናትና ለፈተና ለመዘጋጀት እንድትችል የሚያነብላት ሰው እንደልብ ባለማግኘቷ በጣም ተቸግራለች፡፡ በዚህም ምክንያት “ብሬል” መማር እንዳለባትና “መቅረፀድምፅ” መግዛት እንዳለባት በቁጭት በማሰብ ላይ ነች፡፡ ሌሎች አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችም ትምህርታቸውን ለመማር ሲቸገሩ ይስተዋላል፡፡ አካቶ ትምህርት እነዚህንና ሌችንም የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ችግር ለመፍታት ተቋቁሟል፡፡ ነገር ግን በአፈፃፀሙ ረገድ ከማህበረሰቡ አመለካከትና ከወላጆች ፈቃደኛ አለመሆን የተነሳ ተግዳሮቶች ገጥመውታል፡፡

የኦቲዝም ተጠቂዎችና ሌሎች ልዩ እገዛ የሚፈልጉ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን ለማገዝ የሚያስፈልጉ ነጥቦች ተዘርዝረው በድርሰት መልክ ቀርበዋል፡፡

በሰዋስው ክፍል የአገባብ ችግር ያለባቸውን አረፍተ ነገሮች በማስተካከል ትክክኛ አረፍተ ነገር መመስረት ችለናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የአካቶ ትምህርት ምንድን ነው ?
2. በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ክርክር ለማድረግ ስንነሳ የምንከተላቸው ነጥቦች ምን ምን ናቸው?
3. "ፀሐይ" የተባለችው ገጸባህሪ 11ኛ ክፍል ስትደርስ ውጤቷ የተበላሸባት ለምንድን ነው ?
4. "ሥር ሰደደ፣ ተስፋ ቆረጠ" የሚሉትን አባባሎች ፍች በአረፍተ ነገር አሳዩ።
5. የአረፍተ ነገሮቹን "ባለቤት" እና "ማሰሪያ አንቀጾች" ለይታችሁ ፃፉ።
   ሀ. ማንበብ የአስተሳሰብ አድማስን ያሰፋል።
   ለ. አቶ ሰይፉ የከባድ መኪና ሹፌር ነው።
   ሐ. ፋጡማ እናቷን ትመስላለች።
   መ. ልጁ ብርቱካን መመገብ ይወዳል።

## ክፍል ስባት:- የግንባቤ ማመሳከሪያ ነጥቦች

ከዚህ በታች በምዕራፍ የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች ምን ያህል እንደተረዳችኋቸው ለማረጋገጥ የሚረዱ ማመሳከሪያ ነጥቦች ተዘርዝረዋል። በመሆኑም ዝርዝሮቹን በጥንቃቄ በማንበብ፤ ተረድታችኋቸው ከሆነ ከፊትለፊታቸው ባለው ሳጥን ውስጥ የ(√) ምልክት በማድረግ አረጋግጡ። ያልተረዳችሁት ወይም የሚያጠራጥራችሁ ከሆነ ግን በሳጥኑ ውስጥ የ (?) ምልክት በማድረግ ያልተረዳችኋቸውን ነጥቦች ደጋግማችሁ ከልሱ።

| ተ.ቁ | ማመሳከሪያ ነጥብ | (√) | (?) |
|---|---|---|---|
| 1 | ካዳመጥኩት ምንባብ ዝርዝር መረጃዎችን ለይቻለሁ። | | |
| 2 | በቀረበው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ስርዓቱን ጠብቄ ተከራክሬያለሁ። | | |
| 3 | ምንባቡን አንብቤ ጭብጥ ለይቻለሁ። | | |
| 4 | የምንባቡን ይዘት ዘርዝሬያለሁ። | | |
| 5 | ከምንባቡ ለወጡ ልዩልዩ ጥያቄዎች መልስ ሰጥቻለሁ። | | |
| 6 | ለአዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍች ሰጥቻለሁ። | | |
| 7 | በቀረበው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ገላጭ ድርሰት ፅፌያለሁ። | | |
| 8 | የተዘበራረቁ ቃላትን በማስተካከል አረፍተነገሮችን አስተካክያለሁ። | | |

# ምዕራፍ ስድስት፡ የአካባቢ ጥበቃና የአየር ንብረት ለውጥ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ የቀረበውን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- አዳምጣችሁ የምንባቡን ፍሬ ነገር በማስታወሻችሁ ትፅፋላችሁ::
- በቀረበው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ንግግር ታደርጋላችሁ::
- አንብባችሁ የምንባቡን ጭብጥ ትለያላችሁ::
- አንብባችሁ የምንባቡን ይዘት ታብራራላችሁ::
- ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለቃላት ተመሣሣይ ፍቺ ትሰጣላችሁ::
- ድርሰት ትፅፋላችሁ::
- የምዕላድን ምንነት ትበይናላችሁ::
- የምዕላድ አይነቶችን ትለያላችሁ
- ከቃላት ውስጥ ነፃ እና ጥገኛ ምዕላዶችን ትለያላችሁ::

## ክፍል አንድ:- ማዳመጥ

### በረሃማነትን እንከላከል



ሥዕል 7 ፡ የዓለማችንን የበርሃማነት ስጋትና የሰው ልጆችን ተፅዕኖ የሚያመላክት

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

መምህራችሁ “በረሃማነትን እንከላከል” በሚል ርዕስ አጭር ፅሑፍ ያነቡላችኋል:: ምንባቡን ከማዳመጣችሁ በፊት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ከጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት በቃላችሁ መልሱ::

1. በረሃማነት ምንድን ነው?
2. ለበረሃማነት መከሰት ምክንያቱ ምን ይመስላችኋል?
3. በረሃማነትን ለመቀነስ ምን ምን ተግባራትን ማከናወን አለብን?

## ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ከታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ፡፡

ሀ. የፅሑፉን ጭብጥ ከሶስት በማይበልጡ አረፍተ ነገሮች ባጭሩ ግለፁ፡፡

ለ. በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉትን ተፈጥሯዊ አደጋዎች ዘርዝራችሁ አስረዱ፡፡

ሐ. የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ ምን መደረግ አለበት? ቢያንስ ሁለት ነጥቦችን ጠቅሳችሁ አስረዱ፡፡

መ. ደኖች የአየር ንብረት ለውጥን የሚቆጣጠሩት እንዴት ነው?

ሠ. የደን መጨፍጨፍ ምን ምን ጉዳቶችን እንደሚያስከትል ዘርዝራችሁ ግለፁ፡፡

፪. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍት ነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ክፍት ቦታዎች በሳጥኑ ውስጥ ከተሰጡት ቃላት መካከል እየመረጣችሁ በማስገባት የአረፍተነገሮቹን ሀሳብ አሟሉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| መዛባት | ለምነት | መጠን |
| የትሮፒካል | በምግብነት | መቆጣጠር |
| አእዋፍ | ካርቦን | ለመግታት |
| በምድር ወገብ | | |

ሀ. ደን ማልማት የአየር ንብረት ለውጥን ______________እና የአካባቢ ስርዓተ-ምህዳርን ለመጠበቅ ያስችላል፡፡

ለ. የደን ልማት የአፈር መሸርሸርን በመከላከል የመሬትን________________ ይጠብቃል፡፡

ሐ. ደን ለዱር እንስሳት እና ______________ በመኖሪያነት እና ____________ያገለግላል፡፡

መ. የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ የደን ጭፍጨፋን ________________ ይገባል፡፡

ሠ. ዛፍን በመትከል ሊከሰት የሚችልን የአየር ሚዛን ____________ችግር ማስተካከል ይቻላል፡፡

ረ. የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ከፍተኛ ሚና ያላቸው ____________አካባቢ የሚገኙ _______________ ደኖች ናቸው፡፡

ሰ. የአየር ንብረት ሲለወጥ የውሃ አካላት ________________ ይቀንሳል፡፡

ሸ. ዛፎች ሲቆረጡ ________________ ወደከባቢ አየር ይለቀቃል፡፡

## ክፍል ሁለት፡ ንግግር

፩. የአየር ንብረት ለውጥን ለመቆጣጠር ከሚደረጉ ጥንቃቄዎች መካከል የደን ሀብትን ማልማትና መጠበቅ ዋናው ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም የደን ሀብትን ማልማትና መጠበቅ የሚቻልባቸውን መንገዶች መሰረት በማድረግ በክፍል ውስጥ ንግግር አድርጉ፡፡ ከታች የቀረበውን ቢጋር ለንግግራችሁ በመነሻነት ተጠቀሙት፤

ደንን ለማልማት፡-

- ዛፍ መትከል
- በተራቆቱ ቦታዎች ችግኝ መትከል
- ተስማሚ ችግኞችን መምረጥ
- መንከባከብና መጠበቅ

፪. የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች በተለያዩ መንገዶች በመረዳዳት ሥራቸውን በጋራ ይሰራሉ፡፡ እናንተ በምትኖሩበት አካባቢ ሰዎች በባህላዊ መንገድ እየተረዳዱ ከሚያከናውኗቸው የስራ አይነቶች መካከል አንዱን በመምረጥ በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ፡፡ በመቀጠልም ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ማጠቃለያ በንግግር አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሦስት፡ ንባብ

### የተራቆተ አካባቢን ማልማት

**የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች አጠገባችሁ ከተቀመጡ ተማሪዎች ጋር በመነጋገር መልሱ፡፡

ሀ. በአካባቢያችሁ የተራቆቱ ቦታዎች አሉ? በምን ምክንያት የተራቆቱ ይመስላችኋል?

ለ. የተራቆቱ አካባቢዎችን መልሶ ለመተካት የሚቻል ይመስላችኋል? እንዴት?

በአንድ በተራቆተ የገጠር ተራራማ ክፍል የሚኖሩ ማህበረሰቦች አካባቢያቸው ለረጅም ጊዜ በመታረሱና ለምነቱ በመቀነሱ ምክንያት ምርት አልሰጥ ስላላቸው አርሶአደሮች ተቸግረዋል፡፡ የሚዘሩት እህል አልፎአልፎ በሚጥለው ዝናብ በጐርፍ ይወሰድባቸዋል፡፡ በበጋ ወቅት እንስሶቻቸው የሚጠጡት ውኃ አያገኙም፡፡ የሙቀት መጠኑም ከለመዱት የተለየ ሆኖባቸዋል፡፡ በአካባቢያቸው የሚገኘው የምንጭ ውኃ መጠኑ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የመንደሩ ሰዎች ውኃ ለመቅዳት በማለዳ ሄደው የሚመለሱት ቀትር ላይ ነው፡፡ በአጠቃላይ የነዋሪዎቹ ችግሮች ከዕለት ወደዕለት እየተበራከቱ ናቸው፡፡ ነዋሪዎቹም ችግሩን መፍታት ባለመቻላቸው እንዲሁ ፈጣሪያቸውን እያማረሩ ይኖራሉ፡፡

ይህ ጉዳይ የአካባቢ እንክብካቤና ጥበቃ ባለሙያ የሆነችውን ሠራተኛ እያሳሰባት መጣ:: አንድ ቀን የአካባቢውን ነዋሪዎች ለማወያየት ስብስባ ጠራች:: ነዋሪዎቹም የስብሰባውን ሰዓት አክብረው ተገኙ:: ባለሙያዋ የመወያያው ርዕሰጉዳይ የአካባቢ ልማት መሆኑን አስተዋወቀች::

ከዚያም ንግግሯን እንዲህ በማለት ቀጠለች:: «እንደምታዩት በአካባቢው የሚታይ ሳርም ሆነ ቅጠል የለም:: የአንዳንድ አርሶአደሮች ከብቶች የሚግጡት ሳር የለም:: እኛም የመጠጥ ውኃ እንደልባችን ማግኘት አልቻልንም:: በአጠቃላይ የአካባቢው የድሮው ልምላሜ አሁን የለም:: የችግሩ ፈጣሪዎች እኛው ራሳችን ስለሆንን መፍትሔውንም ራሳችን መፈለግ አለብን:: ስለዚህ አካባቢውን ወደነበረበት ይዞታ ለመመለስ የራሳችንን ጥረት ማድረግ ይኖርብናል» በማለት ገለጸች::

**የንባብ ጊዜ ጥያቄ**

1. በተራቆተ አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰቦች በረሃማነትን ለመከላከል ምን ምን ተግባራን ማከናወን አለባቸው?

ተሰብሳቢዎችም የየራሳቸውን ሀሳብ ሰነዘሩ:: ሀሳባቸውን ከተለዋወጡ በኋላ የመጀመሪያ ሥራቸው በዝናብ እየታጠበ የሚሄደውን አፈር ሰብስቦ ለመያዝና ርጥበትን ጠብቆ ለማቆየት ችግኝ አፍልተው መትከል እንዳለባቸው ተስማሙ:: በዚህ ሥራም ሁሉም የማኅበረሰቡ አባላት መሳተፍ እንዳለባቸው ተነጋገሩ:: በመጨረሻም ሥራውን ለመጀመር ቀጠሮ ይዘው ተለያዩ::

በቀጠሮው ቀን ዕድሜው ለሥራ የደረሰ ሁሉ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ እንደአካፋ፣ ዶማ፣ ወዘተ. ያሉትን መሣሪያዎች ይዘው በቦታው ተገኙ:: በመጀመሪያ ምን አይነት ችግኝ ማፍላት እንዳለባቸው ከባለሙያዋ ትምህርት ወሰዱ:: ለችግኝ ማፍያ የሚሆን ቦታና መደብ አዘጋጁ:: ችግኙን ዘሩ፤ በአቅራቢያው ያለችውን የምንጭ ውሃ እንዳትደርቅ በጥልቀት ቆፈሩና በዙሪያዋ ካብ ካቡ፤ ተራ በተራ ችግኙን መንከባከብ እንዳለባቸው ተመካከሩ:: በተራራው ላይም እልፎ እልፎ እርከን አዘጋጁ፤ ይህንን ሁሉ አድርገው የችግኝ መንከባከብ ተግባርና ሃላፊነት ተከፋፍለው ተለያዩ::

ችግኝ ተከላው ከመካሄዱ ቀደም ብሎ የተወሰኑት ነዋሪዎች ለችግኝ መትከያ ጉድጓድ ቆፈሩ:: በቀጠሯቸው መሠረት ክረምት በገባ በሁለተኛው ሳምንት ለነዋሪዎቹ በጥሪምባ ጥሪ ተላለፈ:: በስምምነታቸው መሠረት ሁሉም ነዋሪዎች ከችግኝ ጣቢያው የሚችሉትን ያህል ችግኝ በመያዝ ወደተራራው ሸመቱ:: ከተራራው ላይ እንደደረሱም በአስተባባሪዎች አማካይነት የሥራ ክፍፍል አደረጉ:: የተወሰኑት ችግኝ ሲያቀርቡ ሌሎቹ ተቆፍሮ በተዘጋጀው ጉድጓድ ውስጥ ችግኝ መትከል ጀመሩ:: በዚህ ሁኔታ ተረዳድተው ያለምንም ድካም የተለያዩ ችግኞችን ተከሉ:: በመጨረሻው ቀን የችግኝ ተከላው ሥራ እንደተጠናቀቀ ለአጭር ጊዜ በመወያየት «ችግኝና ሕጻን እንክብካቤን ይወዳል» በሚለው አባባል መሠረት ተራ ገብተው ችግኞችን ለመንከባከብ ወሰኑ::

ችግር አስተምሯቸዋልና ሁሉም የተሰጣቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ጥረት አደረጉ:: በአካባቢው የሚገኙ የቤት እንስሳትም ወደችግኙ እንዳይሄዱ ለማድረግ እንዲሁም ጭፍጨፋ እንዳይካሄድ የመተዳደሪያ ደንብ አወጡ:: የአካባቢ እንክብካቤና ጥበቃ ባለሙያዋ ችግኞቹ ከተተከሉ በኋላ ክትትል ማድረጓን አላቋረጠችም::

በዚህም መሠረት ችግኙ አድጎ ጥብቅ ደን ሆነ፡፡ ካመታት በኋላ አካባቢው ለምቶ ለዓይን ማረፊያ ሆኗል፡፡ በአካባቢው ይከሰት የነበረው ጐርፍ ቀንሷል፡፡ አፈሩም ለምነቱን ጨምሯል፡፡ ውኃም እንደልብ ማግኘት ተችሏል፡፡ እንስሳትም ከቤት እየዋሉ የሚዘጋጅላቸውን ሣር እንደልብ ማግኘት ችለዋል፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎችም የእርከን ሥራንና የችግኝ ተከላን ጥቅም በመረዳት በየጓሯቸውና በየእርሻቸው ተግባራዊ እያደረጉት ይገኛሉ፡፡

(አብክመ አካባቢና ደን ጥበቃ ባለስልጣን፣ ስኬታማ የደን ልማትና ጥበቃ ተሞክሮ፣ የካቲት፣ 2013፡፡ ማሻሻያ ተደርጎበት የተወሰደ)

## ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

**፩. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት አብራርታችሁ በጽሑፍ መልሱ፡፡**

ሀ. ከላይ የቀረበው ጽሑፍ የሚያስተላልፈውን መልዕክት ባጭሩ ግለፁ፡፡

ለ. ነዋሪዎቹ ውሀ ለመቅዳት በማለዳ ሄደው ቀትር ላይ የሚመለሱት ለምን ይመስላችኋል?

ሐ. የአርሶአደሮቹ ምርት የቀነሰው በምን ምክንያት ነው? አብራርታችሁ ግለጹ፡፡

መ. የአካባቢ ጥበቃ ባለሙያዋ "የችግሩ ፈጣሪዎች እኛው ራሳችን ነን" ስትል ምን ማለቷ ነው? አብራሬርታችሁ ግለፁ፡፡

ሠ. ነዋሪዎቹ ባደረጉት ስብሰባ በመጀመሪያ የተስማሙት ምን ለማድረግ ነው?

ረ. ነዋሪዎቹ በተራራው ላይ እርከን የሰሩት ለምን ይመስላችኋ? አብራርታችሁ ግለጹ፡፡

ሰ. "ችግኝ እና ህፃን እንክብካቤ ይወዳል" የሚለውን አባባል አብራሩ፡፡

**፪. ከዚህ በታች ከምንባቡ የተወሰዱ ልዩ ልዩ ሀሳቦች ተዘርዝረዋል፡፡ እነዚህን ሀሳቦች፡-**

- ለልማት መነሻ ምክንያት
- ችግኝ ለመትከል ቅድመ ዝግጅት
- ችግኙ እንዳይደረቅ የተደረገ ጥንቃቄ እና
- ከልማት የተገኘ ዉጤት

በማለት መልሱ፡፡

ለምሳሌ፡-

ሀ. የግብርና ምርት መቀነስ ለልማት መነሻ ምክንያት ነው፡፡

ለ. ችግኝ ማፍያ ቦታ ማዘጋጀት ችግኝ ለመትከል ቅድመ ዝግጅት ነው፡፡

1. የመሬት መራቆት ______________________________

2. ችግኝ መትከያ ጉድጓድ መቆፈር____________________

3. መተዳደሪያ ደምብ ማውጣት________________________
4. የእንስሳት መኖ መጨመር__________________________
5. የእርከን ሥራ ማከናወን____________________________
6. የግጦሽ ሣር እጥረት________________________________
7. የውሀ እጥረት መከሰት_____________________________
8. ምንጭ ማጎልበት____________________________________
9. ችግኝ ማፍላት_____________________________________
10. ጥብቅ ደን መፍጠር______________________________
11. የአፈር ለምነት መጨመር_________________________
12. እንስሳት ወደ ችግኙ እንዳይሄዱ ማድረግ_____________
13. ችግኙ እንዳይደርቅ መንከባከብ______________________
14. የአፈር ለምነት መቀነስ______________________________
15. ችግኝ መትከል_____________________________________

## ክፍል አራት፡ ቃላት

፩. በ"ሀ" ክፍል የተዘረዘሩትን ቃላት በ"ለ" ክፍል ከተዘረዘሩት ተቃራኒያቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ማለዳ | ሀ. እንግዳ |
| 2. ተራራ | ለ. ነቀለ |
| 3. አልፎአልፎ | ሐ. ዛፍ |
| 4. የተለመደ | መ. ምሽት |
| 5. ምርት | ሠ. ያልዳበረ |
| 6. ልምላሜ | ረ. ገለባ |
| 7. ችግኝ | ሰ. ልቅ |
| 8. ጥብቅ | ሸ. ሜዳ |
| 9. ተከለ | ቀ. ድርቅ |
| 10. ለም | በ. ዘወትር |

፬. በምንባቡ መሰረት ከታች ለቀረቡት ቃላት አገባባዊ ፍች ስጡ፡፡

ሀ. የሚግጡት
ለ. እንዲሁ
ሐ. አንፀባረቁ
መ. ማፍላት
ሠ. ካብ
ረ. እርከን
ሰ. ጥሩምባ
ሸ. አመሩ
ቀ. ደንብ
በ. መኖ

## ክፍል አምስት፡ ጽሕፈት

፩. በሀገራችን ከሚገኙት አራት ወቅቶች መካከል አንዱን መሰረት በማድረግ የወቅቶቹን ትክክለኛ ባህሪ የሚገልፅ መግቢያ፣ ሀተታ እና መደምደሚያ ያለው ድርሰት ፃፉ፡፡

ክረምት፡- የውሃ ወር
ቀዝቃዛ ወቅት

ፀደይ፡- የነፋስ ወቅት
የአበባ ወቅት

በጋ፡- አዝርት የሚደርቅበት
እህል የሚወቃበት
የሙቀት ወቅት

በልግ፡- የቡቃያ ወቅት
ዝናብ የሚጀምርበት ወቅት

## ክፍል ስድስት፡ ሰዋስው

### ምዕላድ

ምዕላድ የምንለው ትርጉም አዘል የሆነና አነስተኛ ወደሆኑ ትርጉም አዘል ክፍሎች ሊሸነሸን የማይችል የመጨረሻ ትርጉም አዘል ንዑስ አሀድ ነው፡፡ ለምሳሌ “በግ” የሚለውን ቃል ወስደን ምዕላድን በምሳሌ እንመልከት፡፡ “በግ” በመጀመሪያ ትርጉም ያለው (አንድን የቤት እንስሳ የሚያመለክት) አሀድ ነው፡፡ ሁለተኛ ይህ አሃድ አነስተኛ ወደሆኑ ትርጉም አዘል ክፍሎች ሊከፈል አይችልም፡፡ እንክፈለው ብንል እንኳን የምናገኘው ትርጉም የሌላቸውን ተናጠላዊ ድምፆች ነው፡፡ ስለዚህ ሁለቱን የምዕላድ መለኪያ መስፈርቶች በማሟላቱ “በግ” ምዕላድ ነው፡፡

በተመሳሳይ አኳኋን "በጋችን" የሚለውን አሀድ ስንመለከት፤ በመጀመሪያ ትርጉም አዘል ነው። ይሁን እንጂ ምዕላድ ለመባል ከሱ በታች ወደሆኑ አነስተኛ ትርጉም አዘል አሃዶች አለመከፈሉ መረጋገጥ አለበት። ይህንን ስናደርግ ቃሉ "በግ" እና "-ኣችን" ተብሎ ሊከፋፈል የሚችል በመሆኑ ቃል እንጂ ምዕላድ አይደለም።

በአንፃሩ "በግ" እና "-ኣችን" የሚሉት አሃዶች ትርጉም ኖሯቸው ከነሱ ወደአነሱ ትርጉም አዘል አሃዶች ልንከፋፍላቸው ስለማንችል ምዕላድ ናቸው። ሆኖም ሁለቱ ምዕላዶች ልዩነት አላቸው። "በግ" ራሱን ችሎ የሚቆም ሲሆን፤ "-ኣችን" ግን እንደ "በግ" ባሉ አሃዶች ላይ ካልተቀጠለ በስተቀር ትርጉም መያዝና ራሱን ችሎ መቆም አይችልም። ስለዚህም እንደ "በግ" የመሳሰሉ ምዕላዶች ራሳቸውን ችለው ስለሚቆሙ ነፃ ምዕላድ ሲባሉ፤ እንደ "-ኣችን" ያሉት ደግሞ ራሳቸውን ችለው ስለማይቆሙ ጥገኛ ምዕላድ ይባላሉ።

(ባየ ይማም፣ የአማርኛ ሰዋስው፣ 2000፣ ገፅ 73 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ)

፩. ከዚህ በታች በቀረቡት ቃላት ውስጥ የሚገኙትን ምዕላዶች ነፃ እና ጥገኛ ምዕላድ በማለት መልሱ።

| ምሳሌ፡- ቃል | ነፃ ምዕላድ | ጥገኛ ምዕላድ (ምዕላዶች) |
|---|---|---|
| ላሞቻቸው | ላም | -ኦች -ኣቸው |
| ስለሀገር | ሀገር | ስለ- |

ሀ. ወንድሜ

ለ. ሸሻችሁት

ሐ. ከሴቶች

መ. ውይይታችን

ሠ. መሄዱ

ቀ. ስለትምህርቱ

ሰ. ፍየልዋ

ሸ. አገኘቻቸው

ረ. በረኛው

በ. በሰላሙ

፪. ከዚህ በታች የቀረቡትን ነፃ እና ጥገኛ ምዕላዶች በማጣመር ቃላት መስርቱ።

ሀ. የ-ቤተሰብ-ኣችን

ለ. ድምበር-ተኛ

ሐ. ሆድ-ኣም-ኦች

መ. ድርቅ-ኦሽ

ሠ. ስለ-እናት-ኣችን

ረ. ጥናት-ኣዊ

ሰ. ሰብር-ኦ-ኣል

ሸ. አይ-ት-ሄድ-ም

ቀ. እን-ሰጥ-ኣችሁ-ኣል-ኧን

በ. ትርፍ-ኣማ-ው

ፎ. ከዚህ በታች የተሰጡትን ጥገኛ ምዕላዶች ከታች በቀረቡት ቃላት ላይ በመቀጠል የተለያዩ ቃላትን መስርቱ፡፡

| መስራች ቅጥያዎች | | |
|---|---|---|
| -ነት | -ኣም | -ኣማ |
| -ኧኛ | -ኣዊ | |

ሀ. ወተት

ለ. ድንጋይ

ሐ. ልጅ

መ.በር

ሠ. ዘመን

ረ. ልብ

ሰ. አሸዋ

ሸ. ዜጋ

ቀ. ሰማይ

በ. ፈረስ

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ለማስተማር የቀረበ ምንባብን ጭብጥ አሳጥሮ ማቅረብን የሚመለከት ልምምድ ተደርጓል፡፡ በዐረፍተ ነገር ውስጥ የተተውትን ባዶ ቦታዎች ተገቢ ቃላትን በመምረጥ አሟልቶ መፃፍ፣ ጅምር ሃሳቦችን መነሻ በማድረግ በየአካባቢው ያሉ ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በባህላዊ መንገድ እየተረዳዱ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት መካከል አንዱን በመምረጥ የቡድን ውያይት ተደርጎ ለክፍሉ ተማሪዎች በንግግር ቀርቧል፡፡

ማንበብ የሚለው ትምህርት ክፍል ትኩረቱ የተራቆተ አካባቢን ማልማትን የሚመለከት ሲሆን የጽሑፍን መልዕክት ባጭሩ ለመግለጽ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከምንባቡ የተወሰዱ ሃሳቦችን በመጠቀም ጅምር ዓረፍተ ነገሮች ተሟልተው ቀርበዋል፡፡ ለቃላት ተቃራኒና አገባባዊ ፍች ተሰጥቷል፡፡ መፃፍ በሚለው የትምህርት ክፍል ደግሞ የወቅቶችን ትክክለኛ ባህሪ የሚገልፅ መግቢያ፣ ሀተታ እና መደምደሚያ ያለው ድርሰት ተጽፏል፡፡ ሰዋስው የምዕራፉ የመጨረሻ ክፍል ሲሆን ስለ ምዕላድ ምንነት እና አይነቶቹ በመረዳት በቃላት ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ የምእላድ አይነቶች ተተንትነዋል፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች

1. በረሃማነትን እንዴት መከላከል ይቻላል?
2. በአካባቢያችሁ ያሉ ልዩ ልዩ ባህላዊ የመረዳጃ መንገዶችን ዘርዝሩ፡፡
3. ባህላዊ የመረዳጃ አይነቶችን አስመልክቶ ያያችሁትን ገጠመኝ የሚመለከት አንድ ድርሰት ፃፉ፡፡
4. አምስት ውስብስብ ቃላትን በመምረጥ በውስጣቸው ያሉትን ነፃና ጥገኛ ምዕላዶች ተንታናችሁ አሳዩ፡፡

## ክፍል ሰባት፡- የግንዛቤ ማመሳከሪያ ነጥቦች

ከዚህ በታች በምዕራፉ የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች ምን ያህል እንደተረዳችኋቸው ለማረጋገጥ የሚረዱ ማመሳከሪያ ነጥቦች ተዘርዝረዋል፡፡ በመሆኑም ዝርዝሮቹን በጥንቃቄ በማንበብ፤ ተረድታችኋቸው ከሆነ ከፊትለፊታቸው ባለው ሳጥን ውስጥ የ(V) ምልክት በማድረግ አረጋግጡ፡፡ ያልተረዳችሁት ወይም የሚያጠራጥራችሁ ከሆነ ግን በሳጥኑ ውስጥ የ (?) ምልክት በማድረግ ያልተረዳችኋቸውን ነጥቦች ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

| ተ.ቁ | ማመሳከሪያ ነጥብ | (√) | (?) |
|---|---|---|---|
| 1 | ያዳመጥሁትን ምንባብ ፍሬ ነገር በማስታወሻዬ ፅፌያለሁ፡፡ | | |
| 2 | በቀረበው ርዕስ ጉዳይ ላይ ስርዓቱን ጠብቄ ንግግር አድርጌያለሁ፡፡ | | |
| 3 | ካነበብሁት ምንባብ ጭብጡን ለይቻለሁ፡፡ | | |
| 4 | ያነበብሁትን ምንባብ ይዘት አብራርቻለሁ፡፡ | | |
| 5 | ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሣሣይ ፍች ሰጥቻለሁ፡፡ | | |
| 6 | በቀረበው ርዕስ ድርሰት ፅፌያለሁ፡፡ | | |
| 7 | የምዕላድን ምንነት ተረድቻለሁ፡፡ | | |
| 8 | የምዕላድ አይነቶችን ለይቻለሁ፡፡ | | |
| 9 | ከቃላት ውስጥ ነፃ እና ጥገኛ ምዕላዶችን ለይቻለሁ፡፡ | | |

# ምዕራፍ ሰባት፡ በልዩነት ውስጥ አንድነት

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ ስር የቀረበውን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- እያዳመጣችሁ ማስታወሻ ትይዛላችሁ፡፡
- አዳምጣችሁ ጥያቄዎችን በቃል ትመልሳላችሁ፡፡
- በቀረበው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ውይይት ታደርጋላችሁ፡፡
- ምንባቡን በፀጥታ በማንበብ ጭብጡን ትለያላችሁ፡፡
- ካነበባችሁት ምንባብ ዝርዝር መረጃዎችን ታወጣላችሁ፡፡
- ለቃላት ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- በመረጣችሁት ርዕስ ላይ ገላጭ ድርሰት ትፅፋላችሁ፡፡
- የአረፍተ ነገር ባለቤትን ለይታችሁ ታወጣላችሁ፡፡
- የአረፍተ ነገር ግስን ለይታችሁ ታወጣላችሁ፡፡
- የፈሊጣዊ አነጋገሮችን ፍቺ ታስረዳላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### የዘይሴ ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻ

ተማሪዎች! መምህራችሁ “የዘይሴ ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻ ” በሚል ርዕስ አንድ አጭር ጽሁፍ ያነቡላችኋል፡፡ ምንባቡን በጥሞና ካዳመጣችሁ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን እየሆናችሁ በመወያየት መልሱ፡፡

#### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ባህላዊ ጋብቻ ሲባል ምን ማለት ነው?
2. በአካባቢያችሁ ባህላዊ ጋብቻ ሲከናወን አይታችሁ ታውቃላችሁ? እስኪ ስለክንውኑ የምታስታውሱትን ለመምህራችሁ በቃል ንገሯቸው፡፡

#### ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ቀጥሎ የተሰጡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ስንት የህይወት ዑደቶችን ያልፋል?
2. የመቀላቀያ ሥነ ስርዓት በሚያካሂዱበት ጊዜ ምን ምን ተግባራት የሚከናወኑ ይመስላችኋል?

3. የመጨረሻው የሰው ልጅ የህይወት ዑደት ምን ይባላል? በዚህ ደረጃ የሚፈፀምን አበይት ክዋኔ አስረዱ፡፡
4. የዘይሴ ብሔረሰብ የሚገኘው የት ነው?
5. በዘይሴ ብሔረሰብ ስንት የባህላዊ ጋብቻ አይነቶች ይገኛሉ?
6. የልጁንና የልጅቷን ተሳትፎ የማይጠይቀው የትኛው የጋብቻ አይነት ነው?
7. ልጅቷ እንደተጠለፈች ወደአሳቻ ቦታ የምትወሰደው በየትኛው የጋብቻ ዐይነት ነው? ለምን?
8. ዕድሜው በጣም አጭር የሆነ ጋብቻ ምን ይባላል?
9. በልጅቷ ፍቃድ ብቻ የሚፈፀም ጋብቻ አይነት ምን ይባላል፡፡የዚህ ምክንያቱ ምንድነው?
10. ያዳመጣችሁት ጽሁፍ ፍሬ ሀሳብ ምንድን ነው?

## ክፍል ሁለት፡ ንግግር

በአካባቢያችሁ ስለሚከናወኑ የጋብቻ አይነቶች በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ፡፡ ቀጥሎም ወጣቶች ጥሩ የጋብቻ ህይወት እንዲኖራቸው ትዳራቸውን በቤተሰብ ምርጫ መመስረት አለባቸው ወይንስ በራሳቸው ምርጫ በሚሉት ሀሳቦች ላይ በቡድን እየሆናችሁ በክፍል ውስጥ ክርክር አድርጉ፡፡

## ክፍል ሦስት፡ ንባብ

### ተበቺሳ

**የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

1. በአካባቢያችሁ ወጣቶች ለብቻቸው ተገናኝተው ሲጫወቱ አይታችሁ ታውቃላችሁ?
2. ወጣቶች እንዲሰባሰቡ የሚያደርጓቸው ተግባራት ምንድን ናቸው? በቃላችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

የተፈጥሮ ልምላሜ የታደለ አካባቢ ነው፡፡ «ስምን መላክ ያወጣዋል» እንዲሉ ስሙም ለሚ ይሰኛል፡፡ በደቡብ ወሎ ዞን በከለላ ወረዳ የሚገኝ ገጠር ነው፡፡ የዚህ አካባቢ ሴቶች መልከ መልካሞች ናቸው፡፡ በተለይ የልጃገረዶቹ ውበት ልብ ይሰርቃል፡፡ የሚያጌጡት በተፈጥሮ ውበታቸው ነው፡፡ ዞማ ፀጉራቸው ጋሜ፣ ሳዱላ፣ ኩልኩሎ፣ወዘተ.. በሚባሉ የአሰራርና የአለጫጨ ስልቶች ይበጃጃል፡፡ አልፎ አልፎ ቅቤ በአደስ ይቀባል እንጂ ሌላ ዘመን አመጣሽ ቅባትና ተኩስ አያውቅም፡፡ብዙዎቹ ኮረዳዎች ጠያይሞችና ወዛሞች ናቸው፡፡ በአካባቢው አገላለጽ «እርጥብ ልምጭ»ይመስላሉ፡፡ በጠይም ፊታቸው ላይ እንደፈርጥ የሚያንፀባርቀው ውብ አይናቸው ትዳር ከመያዛቸው በፊት ኩል አያዘወትሩም፡፡ ከብርና ከነሀስ የተሰሩ መስቀሎች ድምብሎዎች በጥቁር የሐር ክር ለክተው መለል ባለው አንገታቸው ላይ ያስራሉ፡፡ማርዳ ተጨምሮባቸው በደረታቸው ላይ ደረጃ በደረጃ የሚኮለኩሉት መስቀሎችና ድንብሎዎች ጎንበስ ቀና ባሉ ቁጥር በጡታቸው መሀል ድብብቆሽ ሲጫወቱ ይውላሉ፡፡ብዙውን ጊዜ የሚለብሱት ቀሚስ በሰፌር ጥበበኛ የተሸመነ ሽብሽቦ ነው፡፡ ትዳር ከመመስረታቸው በፊት ግን መቀነት አይታጠቁም ፡፡

### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

የለሚ ወጣቶች ከፍቅረኞቻቸው ጋር ሲገናኙ የሚያከናውኗቸው ተግባራት ምን ምን ይመስላችኋል?

የለሚ ማህበረሰብ እነዚህ ኮረዳዎች የተፈጥሮ ውበታቸውን እንዲጠቀሙበት የሚያደርግና በጉ ጉኑ የላቀ ወንዝ በቀል ባህል አለው፡፡ የአካባቢው ኮረዳዎች ትዳር ከመያዛቸው በፊት ከመረጡት ጉብል ጋር የከንፈር ወዳጅነት ግንኙት የመመስረት ሙሉ ነፃነት አላቸው፡፡ ከከንፈር ወዳጃቸው ጋር የሚገናኙባቸው በርካታ አጋጣሚዎች አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል አክርማ ቀጨታ ፣ እንጨት ሰበራ ፣ ኩበት ለቀማ፣ ልብስ አጠባ፣ ጥምቀት፣ እንቁጣጣሽና «ተበቺሳ» ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ከነዚህ የመገናኛ አጋጣሚዎች ግጥም የማይደረደርበት ወይም የማይዜምበት ፣እንጉርጉሮ ወይ ዘፈን የሌለበት አይገኝም፡፡ ለለሚ ኮረዳዎች ሙዚቃ ሕይወታቸው ነው፡፡ የአካባቢው ማሕበራዊ ሕይወት በሙዚቃ ኃይል የሚንቀሳቀስ ነው፡፡ የሚመስለው፡፡ ኮረዳዎቹ በየአጋጣሚው የሚጫወቷቸው አጥንት ሰርስረው ዘልቀው ሥሜትን የሚሞግቱ ውብ ዜማዎች አሏቸው፡፡

የአንድ ሰፈር ኮረዳዎች ተጠራርተው አክርማ ቀጨታ ወይ እንጨት ሰብራ ወይ ኩበት ለቀማ በሚሄድበት ጊዜ በዚያ አውላላ ሜዳ ላይ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሕብረት ሲያዜሙ እንኳን የከንፈር ወዳጃቸውን ወፎችን ይጠራሉ፡፡ በነዚህ አጋጣሚዎች ብዙውን ጊዜ የከንፈር ወዳጃቸውን የሚያሞግሱ ግጥሞችን ነው የሚያዜሙት እንደሚከተለው ያሉትን፡-

አይኑን በቀጫጭን የተኳኳለው፣

ጥርሱን ጉራማይሌ የተወቀረው፣

እንደነብር ጅራት የሚወራጨው፣

እንዴት ነው ጠይም ልጅ ለሚ ላይ ያለው?

ኸረ ጠይም ጠይም ጠይም እትውደዱ፣

እኔን አታዩም ወይ ሲጠፋኝ መንገዱ፣

ይሄ ወንዛወንዙ ያበቅላል እንዶድ ፣

ያካል መጨረሻ ጠይም ልጅ መውደድ፣

ጠይም ወዶ ወዶ በቀይ ሲመለሱ ፣

ሆድ ይበረብራል ጠጅ እንደቀመሰ፡፡

የከንፈር ወዳጅ ከሚገናኙበት አጋጣሚ ሁሉ የተለየ ግምት የሚሰጠው ለተበቺሳ ነው፡፡ (ተበቺሳ ከኦሮሚኛ የተወሰደ ቃል ሲሆን ትርጉሙም አጫውት ማለት ነው፡፡) ተበቺሳ የሚባለው ድግስ ከሚጀመርበት ዕለት ጀምሮ የአካባቢው ኮረዳዎችና ጎረምሳዎች ማታ ማታ እየተሰባሰቡ ሲጨፍሩ የሚያድሩበት አጋጣሚ ነው፡፡ ልዩ የሚያደርገው ቤተሰብ «እባካችሁ ልጃችንን ታጫውትልን» የሚል

መልእክት አስይዞ በየሰፈሩ ልጅ በመላክ ኮረዳዎችን ይለምናል፡፡የኮረዳዎቹ ወለጆች ያለማመንታት ይፈቅዱላቸዋል፡፡ ኮረዳዎቹም ሲዘገጃጁ ውለው ምሽት ላይ ለጫወታቸው ማድመቂያ የምትሆን አታሞ እየያዙ ወደ ደጋሾቹ ቤት ይሄዳሉ፡፡ ጫወታው ሲጀምር ኮረዳዎቹ ክብ ሰርተው አታሟቸውን እየመቱ በሚስረቀረቅ ድምጽ በሕብረት ያዜማሉ፣ እስክስታም ይወርዳሉ፡፡የአታሞ ድምጽ ሰምተው ከየመንደሩ የመጡት ጎረምሳዎች ደግሞ ራሳቸውን ላለማስለየት ለአይናቸው ብቻ ቀዳዳ በመተው በጋቢያቸው ተሸፋፍነው ዱላቸውን ትከሻቸው ላይ አንግሰው ከኮረዳዎቹ ጀርባ በቡድን በቡድን ይቆማሉ ፡፡ ከዚያም ኮረዳዎቹ የሚያዜሙት ግጥም ቤት በደፋ ቁጥር በጉርናና በሚያስገመግም የአንበሳ ድምጽ በህብረት ያገሳሉ፡፡በዚህ አኳኋን አንድዙር ጭፈራ እንዳለቀ ጎረምሳዎቹ የከንፈር ወዳጃቻቸውን እጅ በመያዝ እየጎተቱ ወደዳር ካወጧቸው በኃላ በጋቢያቸው ይሸፍኑና የፍቅር ጫወታ ይጫወታሉ፡፡ ይህ አይነቱ የጭፈራ አጋጣሚ የዳንስ ምሽት (ፖርቲ) የሚባለውን አይነት መሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን የዱባና የቅል አበቃቀሉ ለየቅል እንደሚባለው ሁለቱ የወጣቶች የመገናኛ አጋጣሚዎች በባህሪያቸው እጅግ የተለያዩ ናቸው ፡፡ በተበቺሳ ከከንፈር ያለፈ ጫወታ ፈጽሞ የለም ፡፡ ወጣቶች የከንፈር ወዳጅነት ግንኙነት የመመስረት ነፃነት እንዳላቸው ሁሉ በህብረተሰቡ የተጣለባቸውን ራሳቸውን የመጠበቅ ኃላፊነት በሚገባ ይወጣሉ፡፡

በተበቺሳ የከንፈር ወዳጃቻቸው የመጣላቸው ኮረዳዎች የሚያዜሟቸው ግጥሞች የሙገሳ ግጥሞች ናቸው፡፡ የሚከተሉትን ለአብነት ማየት ይቻላል፡-

እኔስ ከቅድሙ አሁን ተሻለኝ ፣

የንትን ሰፈር ልጆች መጡ መሰለኝ፣

አይናማ በኤሞት እኔ አፈር ስሆን፣

አንዴ ሳቅና ልየው ጥርስህን፣

አየ ጉድ ዋ ሆዩ ወገብ አቀጣጠን፣

አያበቅለው የለ ክረምትና ማጠን፣

የጣዝማ ወለላ የሸጉ ከንፈር፣

አዙሮ ይጥላል እንደምች አደር፡፡

በተበቺሳ የከንፈር ወዳጃቸው ያልተገኙላቸው ኮረዳዎች የሚከተለውን አይነት ግጥም ያዜማሉ፣

አሁን ይህን ጊዜ ያልመጣ ወዳጅ ፣

እናቱ ገርድፋ ይሰልቃል ልጅ፡፡

ጎረምሳዎቹ ለከንፈር ወዳጆቻቸው ግጥሞችን የማያዜሙት እንደ ከብት ጥበቃ፣እርሻ፣አረምና አጨዳ ባሉ የግብርና ተግባራት ላይ በሚሰማሩበት ጊዜ ነው፡፡ በተበቺሳ አጋጣሚ በአስገምጋሚው የአንበሳ ድምፃቸው የኮረዳዎቹን ዜማ ከማድመቅ ሌላ የሚጠበቅባቸው ድርሻ የለም፡፡ በሥራ ላይ እያሉ የሚያዜሟቸው የፍቅር ግጥሞች የሚከተሉትን የመሳሰሉ ናቸው፡፡

ቱሉ ለሚ ሆኖ ይታያል ወለቃ፣

አንገቷ የሚመስለው የማሽላ መቃ፣

የትዝታዬ እሸት የልቤ መብራት፣

ላገኘሽ ነው መሰል መታኝ እንቅፋት፣

የሹምን በረሃ ስትሄድ ብቻዋን፣

ምነው ባደረገኝ ያንን ድምብሏን፣

ሳንቃ ደረቷ ላይ የሚዘለውን፡፡

የከንፈር ወዳጆች በነፃነት የሚገናኙበት መልካም አጋጣሚ ሆኖ ሳለ ተበቺሳ አንድ ጉልህ ጎጂ ገጽታ አለው፡፡ ይሄውም አንዳንድ ጊዜ በጥቃቅን ምክንያት የሰው ሕይወት የሚያልፍበት አጋጣሚ መሆኑ ነው፡፡ ጎረምሳዎቹ ከተለያዩ መንደሮች የሚሰባሰቡ እንደመሆናቸው በቡድን እየተከፋፈሉ ጠብ በመፍጠር ርስበርስ ይደባደባሉ ፡፡ የጠቡ መንስኤ በሌላ አጋጣሚ የተፈጠረና የቆየ ቁርሾ ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም ደግሞ የአንደኛውን ጎረምሳ የከንፈር ወዳጅ ያለፍላጎቷ አስገድዶ ለመወዳጀት የሚደረግ ሙከራ ሊሆን ይችላል ፡፡ ሰበቡ ምንም ይሁን ምን ጠብ እየተፈጠረ የሰው ደም በከንቱ የሚፈስበት የተበቺሳ አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡

ይህ አይነቱ ጎጂ ጎኑ ቀስ በቀስ ከተወገደ ተበቺሳ ነፃነት የተሞላበትና ሕብረተሰቡ በአወንታ የተቀበለው ባህል ስለሆነ ለወጣቶች ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡

(መስፍን መሰለ፣ የቦረና ወሎ ከንፈር ወዳጆችና ግጥሞቻቸው፤ 1985፡፡ ለማስተማር እንዲመች ተደርጎ የተወሰደ)

## ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. የለሚ ኮረዳዎች አንገታቸው ላይ የሚያስሯቸው ማጌጫዎች ምን ምን ናቸው?
2. በሁሉም አጋጣሚዎች የከንፈር ወዳጆች ሲገናኙ ግጥም የሚደረድሩ ይመስላችኋል ?
3. ተበቺሳ ምንድን ነው?
4. በተበቺሳ አጋጣሚ ወጣቶች የሚገናኙት እንዴት ነው?
5. የለሚ ጎረምሶች ጋቢ የሚሸፋፈኑት ለምንድን ነው?
6. በከተማ የዳንስ ምሽትና በተበቺሳ መካከል ያለው  ልዩነት ምንድነው?
7. ተበቺሳ ጎጂ ገጽታ አለው ትላላችሁ? ለምን?
8. የምንባቡ መልእክት ምንድን ነው?

፪. ቀጥሉ በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት ፍቺ በምንባቡ ሃሳብ መሰረት በቃል አስረዱ፡፡

1. የልጃገረዶቹ ውበት ልብ <u>ይሰርቃል</u>፡፡
2. ብዙዎቹ ኮረዳዎች ጠያይሞችና <u>ወዛሞች</u> ናቸው፡፡
3. <u>ከከንፈር</u> ያለፈ ጫወታ ፈጽሞ የለም ፡፡

4. ራሳቸውን ላለማስለየት ይጥራሉ፡፡
5. ሕይወት በሙዚቃ ኃይል የሚንቀሳቀስ ነው፡፡
6. በህብረተሰቡ የተጣለባቸውን ኃላፊነት በሚገባ ይወጣሉ፡፡
7. ለወጣቶች ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡

## ክፍል አራት፡ ቃላት

፩. በምንባቡ ሀሳብ መሰረት በ"ሀ" ክፍል የቀረቡትን ቃላትና ሐረጋት በ"ለ" ክፍል ከተዘረዘሩት ተመሳሳያቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
| --- | --- |
| 1. የሚኮለኩሉት | ሀ. መንከራተቴ |
| 2. አታሞ | ለ. እንዳላበላሽብህ |
| 3. በሚስረቀረቅ | ሐ. ልውደቅልህ |
| 4. አንግበው | መ. ከበሮ |
| 5. በሚያስገመግም | ሠ. ሲሰወርብኝ |
| 6. በቅምጫና | ረ. የሚደረደሩት |
| 7. እንዳላጎሽብህ | ሰ. ነጎድጓዳዊ |
| 8. መባከኔን | ሸ. መጠጫ |
| 9. ልንኮትኮትልህ | ቀ. በሚመስጥ |
| 10. ሲጠፋኝ | በ. የሚያንቀጠቅጥ |
| | ተ. ይዘው |

፪. ቀጥሎ የቀረቡት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ለነዚህ ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ፡፡

1. ልምላሜ
2. ተበጀ
3. ለካ
4. ጉብል
5. ጠራ
6. ጠፋ
7. አምንታ
8. ሰበሰበ
9. ሕብረት
10. ደመቀ

፫. የሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች የሚያስተላልፉትን ፍች ግለፁ

| ተ/ቁ | ፈሊጣዊ አባባል | ፍች |
|---|---|---|
| | ሆደ ሰፊ | ቻይ፣ ትዕግስተኛ |
| 1 | ሀብቷ ቀና | |
| 2 | ስርግና ምላሽ | |
| 3 | ቀዳውን አስወደደ | |
| 4 | ሆድና ጀርባ | |
| 5 | ጥራዝ ነጠቅ | |
| 6 | እጅ አጠረው | |
| 7 | መሬት ላሰ | |
| 8 | ጥቁር እንግዳ | |
| 9 | ሲበሉ የላኩት | |
| 10 | ቀርጦ ቀጥል | |

## ክፍል አምስት: ጽሕፈት

፩. ቀጥሎ ለተሰመረባቸው አባባሎች በምንባቡ ሀሳብ መሰረት ፍቺ በጽሑፍ ስጡ::

ምሳሌ:- የጠቡ መንስኤ በሌላ አጋጣሚ የተፈጠረና የቆየ ቁርሾ ሊሆን ይችላል::

የቃሉ አውዳዊ ፍቺ:- ቂም

1. የተፈጥሮ ልምላሜ የታደለ አካባቢ ነው::
2. የዚህ አካባቢ ሴቶች መልከ መልካሞች ናቸው::
3. የልጃገረዶቹ ውበት ልብ ይሰርቃል ::
4. ጋሜ፣ ሳዱላ፣ ኮልኮሎ፣ወዘተ.. በሚባሉ የአሰራርና የአለጫጨት ስልቶች ይበጃጃል::
5. ብዙዎቹ ኮረዳዎች ጠያይሞችና ወዛሞች ናቸው::
6. በጉ ጉኑ የላቀ ወንዝ በቀል ባህል አለው::

7. ስሜትን <u>የሚሞግቱ</u> ውብ ዜማዎች አሏቸው፡፡
8. እንኳን <u>የከንፈር ወዳጃቻቸውን</u> ወፎችን ይጠራሉ፡፡
9. የኮረዳዎቹ ወለጆች <u>ያለማመንታት</u> ይፈቅዱላቸዋል፡፡
10. በተበቺሳ <u>ከከንፈር ያለፈ</u> ጫወታ ፈጽሞ የለም ፡፡

፪. በሚከተሉት ቃላት መካከል ያለውን የፍቺ ልዩነት አረፍተ ነገር በመስራት አሳዩ፡፡

ምሳሌ ሀ) ወገን ፡- ልጁ የኛ ወገን ነው፡፡

ለ) ዘመድ ፡- ሰውየው ምንም ዘመድ የለውም ፡፡

ሐ) ወዳጅ ፡- እህቴ ለስራ በሄደችበት አገር ብዙ ወዳጅ አፍርታለች፡፡

1. ሀ) መንዝ
   ለ) መራመድ
   ሐ) ማዝገም
2. ሀ/ ማስተሳሰር
   ለ) ማገናኘት
   ሐ) ማቆራኘት
3. ሀ) ቆየ
   ለ) ሰነበተ
   ሐ) ከረመ
4. ሀ) አብነት
   ለ) ምሳሌ
   ሐ) ማስረጃ
5. ሀ) ምስጢር
   ለ) ድብቅ
   ሐ) ስውር
6. ሀ) በርካታ
   ለ) ብዙ
   ሐ) ከፍተኛ
7. ሀ) ልማድ
   ለ) አመል
   ሐ) ፀባይ

፫. ቀጥሎ የተሰያዩ የስርዓት ነጥብ አይነቶች ቀርበዋል :- እነዚህን ሥርዓተ ነጥቦች ከታች በቀረቡት አረፍ ነገሮች ውስጥ በትክክለኛ ቦታቸው በማስገባት አረፍተ ነገሮቹን አስተካክላችሁ እንደገና ፃፉ፡፡ ስመስራት ከመሞከራችሁ በፊት ከታች ስለ ስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም የተሰጠውን ማስታወሻ ተመልከቱ፡፡

፣ ፤ ? ! « » …

1. ከለምለም ማህፀንዋ የሚመነጨው ቡናዋ ውብ ሀሳቦች እያዋለደኝ ጅማ ገባሁ፡፡
2. የሥነጽሑፍ መምህርህ በዓሉ ግርማን ያፈራው ማህፀን የሆንኩትን እኔን ና ተመልከተኝ፡፡
3. ሰው ተሰብስቧል ውይይቱ ግን ገና አልተጀመረም፡፡
4. አይሻ ጫልቱ በለጠችና ሐዋ የሀዳስ ጓደኞች ናቸው፡፡
5. ወይኔ እኔ ኖሬ ቢሆን ኖሮ
6. ዳገቱን ጨርሰን ጉብታው ላይ እንደወጣን ይሄውላችሁ ትምህርት ቤቱ ተባልን፡፡
7. ከመቼው ደረስን
8. ልብሷን ለብሳለች ፀጉርዋን ተሰርታለች አይኗን ተኳኩላለች ማለፊያ ጫማ ተጫምታለች ከአኳኋኗ ወደ አንድ የበዓል ቦታ ለመሄድ የተዘጋጀች መሆኗን መረዳት ይቻላል፡፡
9. የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ከጥቂት ዓመታት በፊት ህያው ጉዞ በሚል ዝግጅት የፍቅር እስከ መቃብርን መቼት ያካለለ ጉዞ ማድረጉ ይታወሳል፡፡
10. ለጊዜው ሥነጽሁፍን ለቱሪዝም ማዋል ባይሆንልን እንኳ የደራሲዎቻችንና የሰዓሊዎቻችን መኖሪያ ቤቶች የተማሩባቸውን ትምህርት ቤቶች መንከባከብ ይገባናል፡፡

## ሥርዓተ ነጥብ

ሥርዓተ ነጥቦች ቃልን ከቃል፣ ሀረግን ከሀረግ፣ አረፍተ ነገር ከአረፍተ ነገር እየለዩ የማመልከቻ ዘዴዎች ናቸው፡፡ በጽሑፍ ስራ ውስጥ በጣም ተዘውትረው ከሚሰራባቸው የስርዓተ ነጥብ አይነቶች መካከል የሚከተሉትን መመልከት ይቻላል፡፡

ሀ/ ነጠላ ሰረዝ ( ፣ )

የሚዘረዘሩ ነገሮችን ለመለየት ያገለግላል፡፡

ለ/ ድርብ ሰረዝ ( ፤ )

ራሳቸውን የቻሉ ነገር ግን አንዱ ከሌላው ጋር ግንኙነት ያላቸውን አረፍተ ነገሮች ለመለየት ያገለግላል፡፡

ሐ/ ቃለ አጋኖ ( ! )

የመደሰትን ፣የመቆጣትን ፣የመቆጨትን፣ የመገረምንና የመሳሰለውን ሀይለኛ ስሜት ከሚገልጽ ቃል፣ ሀረግ ወይም አረፍተ ነገር ቀጥሎ ይገባል፡፡

መ /የጥያቄ ምልክት ( ? )

በመጠይቃዊ ቃላት አማካኝነት ጥያቄ ሲቀርብ በዐረፍተ ነገሩ መጨረሻ የጥያቄ ምልክት ይደረጋል፡፡

ሠ. የጥቅስ ምልክት ( « » )

በጽሑፋችን ውስጥ አንድ ሰው የተናገረውን ነገር ምንም ሳንለውጥ እንዳለ ለማመልከት ስንፈልግ እንገለገልበታለን።

ረ. ነጠብጣብ (… )

ከመጀመሪያም ሆነ ከመሀል ወይም ከመጨረሻ ለምንፈልገው ጉዳይ የሚያገለግለንን ገልብጠን የማንፈልገውን ቃል መዝለላችንን ለማሳየት እንጠቀምበታለን።

፬. በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ወጣቶች በልዩ ልዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች እየተገናኙ የሚጫወቷቸው በርካታ ባህላዊ ጨዋታዎች አሉ። እናንተም በአካባቢያችሁ ያሉ ወጣቶች በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች እየተገናኙ ከሚጫወቷቸው ጨዋታዎች መሀከል አንዱን መርጣችሁ በቡድን ገላጭ ድርሰት ፃፉ።

## ክፍል ስድስት፡-ሰዋስው

ቀጥሎ ተራና ውስብስብ አረፍተ ነገሮች ቀርበዋል። በመሆኑም አረፍተ ነገሮቹን ተራና ውስብስብ በማለት ለያይታችሁ አሳዩ። በቅድሚያ ግን ስለ ውስብስብና ተራ አረፍተ ነገር የተሰጠውን አጭር ማስታወሻ በጥሞና በማንበብ ግንዛቤ ሊኖራችሁ ይገባል።

1. ልጁ ብርጭቆውን ሰበረው።
2. ጀማል መጽሐፍ የላከላት ልጅ መጣች።
3. አስቴር ወንድሟ መኪና እንደገዛ ሰማች።
4. ልጁ በብሩ ደብተር ገዛበት።
5. ጫላ ለወንድሙ ገንዘብ ላከለት።
6. ንግስቲ ከእህቷ የበለጠች ቆንጆ ናት።
7. ገረሱ ጎበዝ አስተማሪ ነው።
8. ሐዋ ለዘገየ መጽሐፍ ሰጠችው።
9. መንሱር አስቴር ቤት እንደሰራች ሰምቷል፤፤
10. አብርሃ ትናንት ሁለት በጎች ገዛ።

### ተራና ውስብስብ አረፍተ ነገር

አረፍተ ነገር ሙሉ ሀሳብን መግለጽ የሚችል ሰፊ ሀረግ ነው። አረፍተ ነገር ከመዋቅር አንጻር ሲታይ የሁለት ሀረጎች ቅንጅት ውጤት ነው። ሁለቱ ሀረጎችም ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረጎች ሲሆኑ፤ አሰላለፋቸውም መጀመሪያ ስማዊ ሀረግ፣ ቀጥሎ ግሳዊ ሀረግ በመሆን ነው። እነዚህ ሁለት ሀረጎች ተቀናጅተው አረፍተ ነገርን ይመሰርታሉ። አረፍተ ነገሮች በውስጣቸው ከሚኖራቸው የግስ ብዛት አንጻር ተራና ውስብስብ  አረፍተ ነገር ተብለው በሁለት ይከፈላሉ።

ሀ. ተራ አረፍተ ነገር፡- በውስጡ አንድ ግስ ብቻ የያዘ አረፍተ ነገር ነው፡፡

ምሳሌ ፡-ታደሰ ከአዲስ አበባ መጣ፡፡

ግስ - መጣ

ለ. ውስብስብ አረፍተ ነገር፡- በውስጡ ከአንድ በላይ ግሶችን በተዋቃሪነት የያዘ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስብስብ ናቸው፡፡

1. ታደሰ የገዛው የሱፍ ኮት ያምራል፡፡
2. ጫላ ሀዊ ወደገበያ እንደሄደች ሰማ፡፡

በእነዚህ አረፍተ ነገሮች ውስጥ ሁለት ሁለት ግሶች ይገኛሉ፡፡ ግሶቹም ተሰምሮባቸዋል፡፡ በመሆኑም እንደነዚህ አይነት አረፍተ ነገሮች ውስብስብ አረፍተ ነገር ይባላሉ፡፡



## የምዕራፉ ማጠቃለያ

የምእራፍ ሰባት ዋነኛው ትኩረት በልዩነት ውስጥ ያለ አንድነትን የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህም የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ማስተማሪያነት ይረዳ ዘንድ “የዘይሴ ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻ” በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መነሻ በማድረግ ስለ ባህላዊ ጋብቻ ምንነት፣ የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ስለሚያልፍባቸው የህይወት ዑደቶች ወዘተ. የሚመለከቱ ዝርዝር ሃሳቦች ሲነበቡ በማድመጥ የምንባቡ ዋና ሃሳብ አጠር ተደርጎ ቀርቧል፡፡ በትምህርቱ በመጨረሻ ላይም ተማሪዎቹ በአካባቢያቸው ስለሚከናወኑ የጋብቻ አይነቶች በቡድን ከተወያዩ በሁዋላ በክፍል ውስጥ ክርክር ተደርጓል፡፡

የንባብ ክሂልን ለማስተማር የቀረበው ተበቺሳ የሚል ምንባብ ሲሆን በደቡብ ወሎ ዞን የለሚ ማህበረሰብ ወጣቶች ስለሚገናኙበት ማህበራዊ አጋጣሚ (ተበቺሳ) ክዋኔ የሚመለከቱ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡ ከተበቻሳ ባህላዊ የወጣቶች ጨዋታ ዝርዝር ክወና በተጨማሪ ስለባህላዊና ዘመናዊ የወጣቶች ውሎ ንጽጽራዊ ቅኝት ተደርጓል፡፡ ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች እንዲሁም ፈሊጣዊ አነጋገሮች የሚያስተላልፉት ሓሳብ ፍች ተሰጥቷል፡፡ ከምንባቡ የተወሰዱ አባባሎች ሀሳብ ፍች፣ በተመሳሳይ ቃላት መካከል ያለው የፍች ልዩነት በጽሁፍ የቀረበ ሲሆን የሥርዓተ ነጥቦችን ምንነት፣ አይነትና ጠቀሜታ የሚመለከት ማስታወሻም ተካቷል፡፡ ሥርዓተ ነጥቦች በዓረፍተ ነገር ውስጥ በትክክለኛ ቦታቸው ገብተው የተሟሉ ዓረፍተ ነገሮች እንደገና ተጽፈው ቀርበዋል፡፡ በሰዋስው ክፍል አረፍተ ነገር ከመዋቅር አንጻር የሁለት ሀረጎች ማለትም የስማዊ ሀረግና የግሳዊ ሀረጎች ቅንጅት ውጤት መሆኑና አሰላለፋቸውም መጀመሪያ ስማዊ ሀረግ፣ ቀጥሎ ግሳዊ ሀረግ እንደሆነ ተብራርቶ በተጨማሪ አረፍተ ነገር ተራ እና ውስብስብ ተብሎ እንደሚከፈል ተገልጧል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የህይወት ዑደቶች ሲባል ምንን ይመለከታል?
2. በዘይሴ ብሔረሰብ ጋብቻ አፈጻጸም ወሳኝ ሚና ያለው ማነው?
3. በአካባቢያችሁ የወጣቶች መዋያ ምን እንደሚመስል ባጭሩአስረዱ፡፡
4. በተበቺሳ ባህላዊ ጨዋታ መነሻነት በአካቢያችሁ ስላለ አንድ ባህል አስረዱ፡፡
5. የሚከተሉት ስርዓተ ነጥቦችን በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን ጽፋችሁ አቅርቡ፡፡

ሀ. ፤ ለ. ፥ ሐ. ? መ. ! ሠ. « »

## ክፍል ሰባት፡- የግንዛቤ ማጠሳከፊያ ነጥቦች

ከዚህ በታች በምዕራፉ የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች ምን ያህል እንደተረዳችኋቸው ለማረጋገጥ የሚረዱ ማጠሳከፊያ ነጥቦች ተዘርዝረዋል፡፡ በመሆኑም ዝርዝሮቹን በጥንቃቄ በማንበብ፤ ተረድታችኋቸው ከሆነ ከፊተስፊታቸው ባለው ሳጥን ውስጥ የ(√) ምልክት በማድረግ አረጋግጡ፡፡ ያልተረዳችሁት ወይም የሚያጠራጥራችሁ ከሆነ ግን በሳጥኑ ውስጥ የ (?) ምልክት በማድረግ ያልተረዳችኋቸውን ነጥቦች ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

| ተ.ቁ | ማመሳከሪያ ነጥብ | (√) | (?) |
|---|---|---|---|
| 1 | ካዳመጥሁት ምንባብ ጠቃሚ ማስታወሻ ይዣለሁ፡፡ | | |
| 2 | አዳምጬ ጥያቄዎችን መልሻለሁ፡፡ | | |
| 3 | በቀረበው ርዕስ ጠቃሚ ውይይት አድርጌያለሁ፡፡ | | |
| 4 | ምንባቡን በፀጥታ በማንበብ ጭብጡን ለይቻለሁ፡፡ | | |
| 5 | ካነበብሁት ምንባብ ዝርዝር መረጃዎችን አውጥቻለሁ፡፡ | | |
| 6 | ለቃላት ተመሳሳይ ፍች ሰጥቻለሁ፡፡ | | |
| 7 | ለቃላት ተቃራኒ ፍች ሰጥቻለሁ፡፡ | | |
| 8 | በተሰጠኝ ርዕስ ላይ ገላጭ ድርሰት ፅፌያለሁ፡፡ | | |
| 9 | ከአረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤትን ለይቼ አውጥቻለሁ፡፡ | | |
| 10 | ከአረፍተ ነገር ውስጥ ግስን ለይቼ አውጥቻለሁ፡፡ | | |
| 11 | ተራ እና ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን ለይቻለሁ፡፡ | | |

# ምዕራፍ ስምንት፡ የግብር ጥቅም

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ የቀረበውን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- አዳምጣችሁ የምንባቡን መልዕክት ትናገራላችሁ።
- አዳምጣችሁ ጥያቄዎችን በቃል ትመልሳላችሁ።
- በቀረበው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ውይይት ታደርጋላችሁ።
- ምንባቡን በፀጥታ በማንበብ ጭብጡን ታብራራላችሁ።
- ካነበባችሁት ምንባብ ዝርዝር መረጃዎችን ታወጣላችሁ።
- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ።
- አስረጅ ድርሰት ትፅፋላችሁ።
- ከስማዊ ሀረጎች ውስጥ ቅፅሎችንና ስሞችን ትለያላችሁ።

## ክፍል አንድ፡ ማዳመጥ

### የግብር ውዴታና ግዴታ

ተማሪዎች መምህራችሁ " የግብር ውዴታና ግዴታ" በሚል ርዕስ አጭር ፅሑፍ ያነቡላችኋል። እናንተም በጥሞና ተከታተሉ። ስታዳምጡ ማስታወሻ መያዝ አትርሱ።

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ምንባቡን ከማዳመጣችሁ በፊት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ከጎናችሁ ካሉት ጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት በቃል መልሱ።

1. ግብር ምንድን ነው?
2. ቤተሰባችሁ ግብር በምን በምን ጉዳዮች ይከፍላሉ?
3. እናንተ ወይም ቤተሰባችሁ ግብር በመክፈላችሁ ምን የምትጠቀሙ ይመስላችኋል?

### ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልሶችን በቃል መልሱ።

ሀ. ለአንድ ሀገር ልማትና ዕድገት አስፈላጊ ነው የተባለው ምንድን ነው?

ለ. ዜጎች ግብር የሚከፍሉት ከየት ነው?

ሐ. ግብር የሚከፍሉት የህብረተሰብ ክፍሎች እነማን ናቸው?

መ. ኢትዮጵያ ውስጥ ግብራቸውን ሳያቋርጡና ሳያጓድሉ የሚከፍሉትን የህብረተሰብ ክፍሎች ተናገሩ።

ሠ. በህገወጥ መንገድ እየነገዱ ከፍተኛ ትርፍ እያገኙ ግብር የማይከፍሉ የህብረተሰብ ክፍሎች እነማን ናቸው?

፪. ቀጥሉ የቀረቡትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በፅሑፍ መልሱ፡፡

ሀ. ግብር ለአንድ ሀገር የሚሰጠው ጠቀሜታ ምን ምን እንደሆነ ዘርዝራችሁ ግለፁ፡፡

ለ. ግብር በወቅቱ ካልተከፈለ በሀገር እና በዜጎች ላይ ምን ጉዳት ሊያስከትል ይችላል?

ሐ. ብዙ ዜጎች ግብር ግዴታ መሆኑን እንጅ ለሀገር ጥቅም እንደሚሰጥ አያውቁም፡፡ ለምን እንደማያውቁ አብራርታችሁ ግለፁ፡፡

መ. ግብር ገማች ሠራተኞች ታማኝ ካልሆኑ መንግስት ወይም ነጋዴው ሊጎዳ ይችላል፡፡ መንግስትም ሆነ ነጋዴው እንዴት ሊጎዱ እንደሚችሉ አብራርታችሁ ግለፁ፡፡

ሠ. ሀገርን ከመጥቀም ወይም ከመጉዳት አንፃር በህገወጥ መንገድ በሚነግዱ እና የህግ ስርዓቱን ተከትለው በሚነግዱ ነጋዴዎች መካከል ያለውን ልዩነት አብራሩ፡፡

## ክፍል ሁለት፡ ንግግር

ከታች በቀረቡት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ንግግር ለማድረግ በቅድሚያ አምስት አምስት አባላት ያሉት ቡድን መስርቱ፡፡ በየቡድኑ አወያይና ራፖርተር ምረጡ፡፡ በመቀጠል ትዕዛዙን መሰረት በማድረግ ንግግር አዘጋጅታችሁ ለክፍሉ ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

ከዚህ በታች ንግግር ለማድረግ የሚያገለግሉ ግብር ነክ ርዕሰ ጉዳዮች ተሰጥተዋል፡፡ ርዕሰ ጉዳዮቹም፡-

• ግብር መክፈል ግዴታም ክብርም ነው፡፡

• በኮንትሮባንድና በህገወጥ መንገድ መነገድ ዜጎችንና ሀገርን ይጎዳል፡፡ የሚሉት ናቸው፡፡ በመሆኑም ከሁለቱ ሀሳቦች አንዱን በመምረጥ ግብር መክፈል እንዴት ግዴታና ክብር እንደሆነ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በህገወጥ መንገድ መነገድ እንዴት ዜጎችንና ሀገርን እንደሚጎዳ፤ ከቡድን አባላት ጋር ከተወያያችሁ በኋላ በቡድን ተወካዮቻችሁ በኩል አጭር ንግግር አድርጉ፡፡

## ክፍል ሦስት፡ ንባብ

### ግብር መክፈል

#### የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ግብር መክፈል ምን ጠቀሜታ ያለው ይመስላችኋል?
2. ግብር መሰብሰብ ያለበት ማን ነው?

አንዲት ሀገር ሁለንተናዊ የኢኮኖሚያዊ፣ የማህበራዊና የፖለቲካዊ አድገቶቿን ለማቀላጠፍ ያልተቋረጠ ገቢ መሰብሰብ ያስፈልጋታል፡፡ የገቢ ማግኛ ምንጮች በመሆን ከሚያገለግሉት መካከል ደግሞ ግብር አንዱና ዋነኛው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ለዚህም ነው ግብር ወይም ታክስ ዋናው የመንግስት የፋይናንስ ምንጭ በመሆን የአንድ አገር የምጣኔሀብት፣ የልማትና የእድገት የጀርባ አጥንት ነው የሚባለው፡፡ ዜጎች ህይወታቸው፣ ነጻነታቸውና ንብረታቸው ላይ ሊደርስ ከሚችለው ማናቸውም ጉዳት እንዲከላከልላቸው መንግስት የሚባለውን አካል ፈጥረው ይኖራሉ፡፡ ይህ መንግስት የሚባለው አካልም የተጣለበትን አደራ ለማሳካትና የገባውን ቃል ለማስፈጸሚያነት ከዜጎች ግብር የመሰብሰብና ስራ ላይ የማዋል ሀላፊነት አለበት፡፡ ዜጎችም መንግስታቸው እንዲሰጣቸው የሚፈልጓቸውን አገልግሎቶች በአግባቡ ያገኙ ዘንድ ግብር መክፈልን ግዴታቸውን እንደመወጣት በመቁጠር በወቅቱ ተፈጻሚ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ድሮ ድሮ የመንግስት ሀላፊነት ነው ተብሎ የሚታሰበው ነዋሪዎችን ወይም ዜጎችን ከጥቃት በመከላከል ደህንነታቸውን ማስጠበቅ ብቻ ነበር፡፡ በዘመናዊው አለም ግን የመንግስት ሚና ጥንታዊ ከሆነው የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ከማስከበር አልፎ መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ማሟላት፣ እንዲሁም መሰረተ ልማቶችን ማስፋፋትና ሁለንተናዊ እድገትን ለማፋጠን የሚያስፈልጉ ስራዎችን እንዲያከናውንና ማህበራዊ ፍትህን እንዲያሰፍን ይጠበቃል፡፡ እነዚህን ሰፊ ተግባራት ለመከወን ነው እንግዲህ መንግስት ወጪውን የሚሸፍንበት የገቢ ምንጭ ያስፈልገዋል የሚባለው፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰውም ግብር ዋነኛው የገቢ ምንጭ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከመንግስት አገልግሎት የሚሰበሰብ ክፍያ፣ ከተለያዩ አካላት የሚገኝ እርዳታና የመሳሰሉት ደግሞ ከግብር በተጨማሪ ለመንግስት በገቢ ምንጭነት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. መንግስት ግብር ከሰበሰበ በኋላ ለዜጎቹ ምን ምን አገልግሎቶችን የሚያቀርብ ይመስላችኋል?
2. በአንድ ሀገር ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ዜጎች እኩል የግብር መጠን የማይከፍሉት ለምን ይመስላችኋል?

ጠቅለል አድርገን ስናየው ግብር ወይም ታክስ ማለት መንግስት ለዜጎቹ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚያወጣቸውን ወጪዎች ለመሸፈን እንዲችል በህግ የተጣለ አስገዳጅነት ያለው ክፍያ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ብያኔ የሚያመለክተውም ግብር በህግ የሚጣል ግዴታ መሆኑንና አስቀድሞ በተደነገገ የህግ ማዕቀፍ መሰረትም ተፈጻሚ እንደሚደረግ ነው፡፡ ማንኛውም ግብር ከፋይ በተለየ ሁኔታ ለከፈለው ግብር በግሉ ቀጥተኛ የጥቅም ጥያቄ ሳያነሳ ግብሩን መክፈል ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን የሚጠበቅበትን ግብር ሳይከፍል ቢቀር በአስተዳደራዊና በወንጀል ህጎች ተጠያቂ የሚሆን ይሆናል ማለት ነው፡፡ በነገራችን ላይ ግብር የሚጣለውም ሆነ የሚሰበሰበው በመንግስት ብቻ ነው ፡፡ ግለሰቦች ግብር የመጣልና የመሰብሰብ ስልጣን የላቸውም፡፡

ስለግብር ሲነሳ አብረው የሚነሱ ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነሱም ግብር የሚጣልበት የገቢ ምንጭና የሚጣለው ግብር ወይም ታክስ መጠን ናቸው፡፡ ግብር የሚጣልባቸው የገቢ ምንጮች ገቢ የሚያስገኙ ማናቸውም የምርት፣ የአገልግሎትና የንግድ ወይም የስራ ዘርፎች ሲሆኑ የግብር መጠን ደግሞ በእነዚሁ ገቢዎች ላይ የሚጣለው የገንዘብ መጠን ነው፡፡ በዚህም ግብር ከፋዮች በገቢያቸው ልክ

ግብር እንዲከፍሉ ይደረጋል:: በዚሁ መሰረት ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ግብር ከፋዮች አነስተኛ ግብር የሚከፍሉ ሲሆን፣ በአንጻሩ ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ግብር ከፋዮች ደግሞ ከፍ ያለ ግብር ይከፍላሉ ማለት ነው:: ይህም የግብርን አፈጻጸም ፍትሀዊነት ያሳያል::

(ምንጭ:- https://www.eag.gov.et/ ግብር የመክፈል ግዴታና የህግ ማእቀፍ)

## ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

**፩. ተከታዮቹ አረፍተ ነገሮች በምንባቡ መሰረት የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ 'እውነት' ትክክል ካልሆነ ደግሞ 'ሐሰት' በማለት መልሱ::**

1. ግብር መንግስት ዜጎቹ በአግባቡ ኑሯቸውን እንዲመሩ የሚከፍላቸው ክፍያ ነው::
2. አንድ ግብር ከፋይ ለከፈለው ግብር ቀጥተኛ የጥቅም ጥያቄ ማንሳት ይችላል::
3. ከፍ ያለ ግብር ከፋዮች የሚባሉት ከፍተኛ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው::
4. መንግስት ከግብር ውጪ ሌሎች የገቢ ምንጮች እንደማይኖሩት የሚታወቅ ነው::
5. በአሁኑና በጥንታዊው ዘመን የነበረው የመንግስት ሚና ተመሳሳይ አይደለም::

**፪. በምንባቡ መሰረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተስማሚ መልሶችን ምረጡላቸው::**

1. አንድ ሀገር ግብር የሚሰበስበው ለምንድን ነው?
   ሀ. ኢኮኖሚውን ለማሳደግ
   ለ. ማህበራዊ እድገትን ለማፋጠን
   ሐ. ፖለቲካዊ እድገትን ለማፋጠን
   መ. ሁሉም
2. ከሚከተሉት ውስጥ የአንድ ሀገር ዋና የገቢ ምንጭ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ግብር እና ታክስ
   ለ. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚሰጡት ርዳታ
   ሐ. የወጪ እና ገቢ ንግድ
   መ. ሁሉም
3. ዜጎች መንግስት የተባለውን አካል የፈጠሩት ለምንድን ነው?
   ሀ. ህይወታቸውን ከአደጋ እንዲጠብቅላቸው
   ለ. ነፃነታቸውን እንዲያስከብርላቸው
   ሐ. ንብረታቸውን ከማናቸውም አደጋ እንዲጠብቅላቸው
   መ. ሁሉም መልሶች ናቸው
4. የአንድ ሀገር ዜጎች ከመንግስት የሚፈልጉትን ነገር ለማግኘት ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል?
   ሀ. ጠንክረው ሰርተው ሀብታም መሆን
   ለ. ልጆቻቸውን ማስተማር
   ሐ. የተጣለባቸውን ግብር መክፈል
   መ. በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ መሳተፍ
5. ድሮ ድሮ የመንግስት ሀላፊነት የነበረው ምንድን ነው?
   ሀ. የዜጎችን መሰረታዊ ፍላጎት ማሟላት
   ለ. ዜጎችን ከጥቃት መከላከል
   ሐ. መሰረተ ልማቶችን ማስፋፋት
   መ. ንግድና ቱሪዝምን ማስፋፋት

6. ከሚከተሉት ውስጥ በምንባቡ መሰረት በትክክል ያልተገለፀውን ምረጡ፡፡
   ሀ. ግብር የህግ አስገዳጅነት ያለው ክፍያ ነው፡፡ ለ. ግብር የሚጣለው በባለስልጣናት ይሁንታ ነው፡፡
   ሐ. ግብር አለመክፈል በወንጀል ህግ ተጠያቂ ያደርጋል፡፡ መ. ግብር እና ታክስ የሚሰበሰበው በመንግስት አካል ብቻ ነው፡፡
7. ዜጎች የሚከፍሉት የግብር መጠን መሰረት የሚያደርገው ምንድን ነው?
   ሀ. የዜጎችን መብትና ግዴታ ለ. የሠራተኞችን የሥራ ዘርፍ
   ሐ. የግብር ከፋዮችን የገቢ ምንጭ መ. ቀደም ሲል የከፈሉትን የግብር መጠን
8. ከሚከተሉት ውስጥ የግብርን ፍትሃዊነት የማያመለክተው የቱ ነው?
   ሀ. ዝቅተኛ ገቢ ባለው የስራ ዘርፍ ላይ የተሰማራ ነጋዴ አነስተኛ ግብር ይከፍላል፡፡
   ለ. ከፍተኛ ገቢ ያለው ነጋዴ ከፍተኛ ግብር ይከፍላል፡፡
   ሐ. በሆቴል አገልግሎት ዘርፍ የተሰማሩ ነጋዴዎች አነስተኛ ግብር ይከፍላሉ፡፡
   መ. የመንግስት ሰራተኞች ከገቢያቸው ጋር የተመጣጠነ ግብር ይከፍላሉ፡፡

### ፫. በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ

1. “ግብር ለአንድ ሀገር የጀርባ አጥንት ነው፤ የሚባለው ለምንድን ነው?
2. የአንድ ሀገር መንግስት ከግብርና ታክስ በተጨማሪ ገቢ ሊያገኝ የሚችልባቸውን አማራጮች ግለፁ፡፡
3. ግለሰቦች ግብር የመጣልና የመሰብሰብ ስልጣን የማይሰጣቸው ለምን ይመስላችኋል?
4. አንድ ሰው ሊሰራቸው የሚችሉ ገቢ የሚያስገኙ የስራ ዘርፎች ምንምን ናቸው?
5. ዜጎች ግብር ባይከፍሉ ምን የሚፈጠር ይመስላችኋል?

## ክፍል አራት፡ ቃላት

### ፩. በ “ሀ” ስር የተዘረዘሩትን ከምንባቡ የወጡ ቃላት በ “ለ” ስር ከተዘረዘሩት አውዳዊ ፍቺቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ዘርፎች | ሀ. ጥፋተኛ |
| 2. ለማቀላጠፍ | ለ. ሁሉን አቀፍ፣ አጠቃላይ |
| 3. የጀርባ አጥንት | ሐ. መስኮች፣ አይነቶች |
| 4. ሁለንተናዊ | መ. የመቆጣጠሪያ መርሆች |
| 5. ተጠያቂ | ሠ. ሀላፊነት |
| 6. የሚጣለው | ረ. ተገቢነት፣ አለማዳላት |

7. በአንጻሩ
8. ፍትሀዊነት
9. ስልጣን
10. የህግ ማዕቀፍ

ሰ. ለማፋጠን፣ በአግባቡ ለማስኬድ
ሽ. ወሳኝ፣ መሰረታዊ
ቀ. የሚወሰነው፣ የሚተመነው
በ.ተቃራኒው

፪. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ስጧቸው ፡፡

1. ገነባ
2. ጉልህ
3. ወደኋላ
4. ተጀመረ
5. ማግለል
6. ዳረገ
7. ተሸማቀቀ
8. ግዙፍ
9. መጠየፍ
10. ቀዳሚ

## ክፍል ስምስት፡ ጽሕፈት

፩. “ግብር” እና “ቀረጥ” ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰበሰቡ የመንግስት ዋና የገቢ ምንጮች እንደሆኑ ከላይ በቀረበው ምንባብ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን በሁለቱ መካከል የሚስተዋል ልዩነትም አለ፡፡ በመሆኑም በሁለቱ ጽንሰ ሀሳቦች መካከል የሚታየውን ልዩነት በጽሑፍ አብራርታችሁ ግለፁ፡፡

፪. በሀገራችን ስራ ላይ የዋሉት የግብር ዓይነቶችና የግብር ደረጃዎች የተለያዩ ናቸው፡፡ በመሆኑም የሚያውቁ ሰዎችን በመጠየቅ ወይም መፃህፍት በማንበብ ስንት የግብር ዓይነቶች እንዳሉ፤ እንዲሁም ስንት የግብር ደረጃዎች እንደሚተገበሩ አብራርታችሁ በጽሑፍ ግለፁ፡፡

## ክፍል ስድስት፡-ሰዋስው

### ከስማዊ ሀረግ ውስጥ ቅፅል ማውጣት

ምሳሌ፡ አጫጭር ልጆች መጡ፡፡

ቅፅል፡- አጫጭር

አበበ ለወንድሙ ጥቁር በግ ገዛለት፡፡

ቅፅል፡- ጥቁር

፩. በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ቀፅሎች ለይታችሁ አውጡ፡፡

ሀ. አብርሃ ሁለት ትላልቅ በጎች ሸጠ፡፡

ለ. አለም አዲስ ቀሚስ ገዛች፡፡

ሐ. አቤል ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡

መ. በሩን ለማቆም ወፍራም ገመድ ያስፈልጋል፡፡

ሠ. ሰይፉ ሰፊ ቤት ተከራየ፡፡

ረ. አጭሩ ልጅ የባጃጅ ሹፌር ነው፡፡

ሰ. እኔና ጓደኛዬ ሩቅ መንገድ ስለሄድን ደከመን፡፡

ሸ. ሕፃኑ ትኩስ ወተት ይወዳል፡፡

ቀ. አስተማሪያችን ጥቁር ጫማ ያዘወትራል፡፡

በ. ባሮ ወንዝ ላይ ረዥም ድልድይ ተዘርግቷል፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሁለት ምንባቦች ቀርበዋል፡፡የምንባቦቹ ትኩረት ግብር ነው፡፡ በዚህም ግብር መክፈል ውዴታና ግዴታ መሆኑ፤ ስለግብር አይነቶች፣ ግብርን መክፈል ለሃገርና ህዝብ ያለው ከፍተኛ ጠቀሜታ በዋና ጭብጥነት ተነስተዋል፡፡ ንግግር ለማድረግ ያመች ዘንድ ተማሪዎች በቡድን ተዋቅረው አወያይና ቃለ ጉባኤ ያዥ በመምረጥ ስለግብር መክፈል ግዴታና የህገወጥ ንግድ(ኮንትሮባንድ) ጉዳት ላይ ተወያይተው የክፍል ውስጥ ንግግር አድርገዋል፡፡

በበተጨማሪም ለቃላት አውዳዊና ተቃራኒ ፍችዎች መስጠት፤ የግብር እና ቀረጥ ልዩነት፣ የግብር ዓይነቶች እና የግብር ደረጃዎች የሚመለከቱ ሀሳቦችን በጽሁፍ ማቅረብ፤ በሰዋስው ትምህር ክፍልም ከስማዊ ሃረግ ቅጽልን ማውጣት በምዕራፉ ትምህርት ዋና ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች

1. ግብርን አለመክፈል የሚያስከትሏቸው ጉዳቶች ምን ምን ናቸው?
2. ሁሉም ሰው ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት ብላችሁ ታምናላችሁ?
3. ህገ ወጥ ንግድ (ኮንትሮባንድ) የሚያደርሳቸውን አስረዱ፡፡
4. ቅጽልን የሚመለከት አምስት ምሳሌዎች ስጡ፡፡
5. በስምና በቅጽል መሃከል ያለውን ልዩነት አስረዱ፡፡

## ክፍል ሰባት:- የግንዛቤ ማመሳከሪያ ነጥቦች

ከዚህ በታች በምዕራፉ የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች ምን ያህል እንደተረዳችኋቸው ለማረጋገጥ የሚረዱ ማመሳከሪያ ነጥቦች ተዘርዝረዋል:: በመሆኑም ዝርዝሮቹን በጥንቃቄ በማንበብ፤ ተረድታችኋቸው ከሆነ ከፊትለፊታቸው ባለው ሳጥን ውስጥ የ(V) ምልክት በማድረግ አረጋግጡ:: ያልተረዳችሁት ወይም የሚያጠራጥራችሁ ከሆነ ግን በሳጥኑ ውስጥ የ (?) ምልክት በማድረግ ያልተረዳችኋቸውን ነጥቦች ደጋግማችሁ ከልሱ::

| ተ.ቁ | ማመሳከሪያ ነጥብ | (√) | (?) |
|---|---|---|---|
| 1 | ያዳመጥሁትን ምንባብ መልዕክት ተረድቻለሁ:: | | |
| 2 | ካዳመጥሁት ምንባብ የወጡ ጥያቄዎችን በትክክል መልሻለሁ:: | | |
| 3 | በቀረበው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጠቃሚ ውይይት አድርጌያለሁ:: | | |
| 4 | ምንባቡን በፀጥታ በማንበብ ጭብጡን ተረድቻለሁ:: | | |
| 5 | ካነበብሁት ምንባብ ዝርዝር መረጃዎችን አውጥቻለሁ:: | | |
| 6 | ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ሰጥቻለችሁ:: | | |
| 7 | በቀረበው ርዕስ አስረጅ ድርሰት ፅፌያለሁ:: | | |
| 8 | ከስማዊ ሀረጎች ውስጥ ቅፅሎችንና ስሞችን ለይቻለሁ:: | | |

# ምዕራፍ ዘጠኝ: ልቦለድ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ የቀረበውን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ:-

- አዳምጣችሁ የጽሑፉን መልዕክት ታስረዳላችሁ፡፡
- የአጭር ልቦለድ ምንነትን ታብራራላችሁ፡፡
- የአጭር ልቦለድን ባህሪያት ታስረዳላችሁ፡፡
- የልቦለዱን ጭብጥ ትረዳላችሁ፡፡
- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- አንቀጽ ትጽፋላችሁ፡፡
- የአረፍተ ነገር ተዋቃሪዎችን ትለያላችሁ፡፡
- የግል ደብዳቤ ታዘጋጃላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ: ማዳመጥ

### ጠቃሚ ምክር

#### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

**ሀ. ተማሪዎች! መምህራችሁ "ጠቃሚ ምክር" በሚል ርዕስ አንድ አጭር ጽሁፍ ያነቡላችኋል፡፡ ምንባቡን በጥሞና ካዳመጣችሁ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን እየሆናችሁ በመወያየት መልሱ፡፡**

1. ምክር ሲባል ምን ማለት ነው?
2. በአካባቢያችሁ ምክር የሚሰጡ እነማን ናቸው?

#### ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

**ሀ. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በቃል መልሱ፡፡**

1. ዋኔዋ ለአዳኙ የሰጠቻቸው ምክሮች ምን ምን ናቸው?
2. አዳኙ የዋኔዋን ሁለተኛውን ምክር ለመስማት የፈለገው ለምንድን ነው ?
3. አዳኙ የዋኔዋን የመጨረሻውን ምክር ለመቀበል ደስተኛ የሆነ ይመስላችኋል? ለምን?
4. ዋኔዋ ከአዳኙ ለማምለጫነት የተጠቀመችው ብልሃት ምንድን ነው?
5. በአካባቢያችሁ ያጠፋ ሰው ሲመከር አይታችሁ ታውቃላችሁ? በሂደቱ ምን ምን እንደተመለከታችሁ ገጠመኞቻችሁን በቡድን/ጥንድ ተነጋገሩ፡፡

6. አዳኙ ሁለተኛውን ምክር እንደሰማ ዋኔዋን የተከተላት ለምንድን ነው?
7. ያዳመጣችሁት ጽሁፍ ፍሬ ሀሳብ ምንድን ነው?

፪. ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት ካዳመጣችሁት ምንባብ አንፃር ፍቻቸውን ግለፁ::

ምሳሌ፡- አስተዋለ፡- አገናዘበ፡ ልብ አደረገ

1. የልቡን ሲነግሩት
2. ማረኝ
3. ተፀፀተ
4. የሚጉላላ
5. ተላላ
6. አልጠቅምህም
7. አፋፍ
8. ጉድ ሰራኝ
9. ውለታ
10. ወቄት

## ክፍል ሁለት፡ ንግግር

ምክር በባህላዊ መንገድ ወይም በዘመናዊ መልኩ ሊሰጥና በህብረተሰቡ ውስጥ የሚታዩትን የሀሳብ ልዩነቶችና ግጭቶች መፍቻነት ጥቅም ላይ ይውላል:: ይሁን እንጅ በነዚህ ሀሳቦች ላይ የሚሰጡ ተቃራኒ ሀሳቦች አሉ:: ማለትም ግጭትን በፍርድ ቤት ሙግት መፍታትና ግጭትን በሀገር ሽማግሌዎች ምክርና ተግሳጽ መፍታት በተመለከተ ልዩ ልዩ ሀሳቦች ይሰጣሉ:: በመሆኑም እናንተም በሀገር ሽማግሌዎች የሚሰጥ ምክር ግጭትን በቋሚነት ለመፍታት የተሻለ ነው/ አይደለም በሚል ርዕስ በቡድን ሆናችሁ ክርክር አድርጉ::

## ክፍል ሦስት፡ ንባብ

### እናቲቱ

**የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

1. አጭር ልቦለድ ምንድን ነው?
2. አጭር ልቦለድ ተለይቶ የሚታወቅባቸው ባህሪያት አሉ? ምን ምን ይባላሉ?
3. ከዚህ ቀጥሎ እናቲቱ በሚል ርዕስ አንድ አጭር ልቦለድ ቀርቦላችኋል:: የልቦለዱ መልዕክት ምን ይመስላችኋል?

ፀጥታ ባረበበት ጎጆ ውስጥ ሁለት ነፍሳት ተፋጥጠው ነበር። ፀጥታው ድንገት ተገሠሠ። "...ሶስት መቶ አምሣ ብር ባለማግኘትሽ አይንሽ ሊጠፋ ነው!"

በልጅቱ ድምፅ ውስጥ ስጋት አለ።

"ይሆናል!"

እናቲቱ ቀሊል ትከሻዎቿን በግዴለሽነት ሰበቀች።

"...ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ደመኛሽ የምትንሰፈሰፊለት ልጅሽ ነው!"

"በመድኃኒዓለም ይገፍሻለሁ ልጄ! ወንድምሽ በሌለበት አታሳቅቂው! ...እንዲያው በመድኃኒ...."

"ኤድያ! ...ምነው በማህጸንሽ ውስጥ ውሃ ሆኖ በቀረ! ...የሱ ወንድምነት ባፍንጫዬ ይውጣ...ይሄ... ይሄ ...ጭንጋፍ...!"

"በ...ፈጠረሽ!"

እናቲቱ ተማፅኖዋን አቀረበች። "ባይሆንለት ባይሞላለት ነው ብየሻለሁ። ቢደላው ኮ አስችሎት አይቀመጥም ነበር...!"

"እሺ አሁን አንቺ ከየት ታመጫለሽ?"

እናቲቱ መልስ አልነበራትም።

አባብጠው ውሃ በሚያገፉ ዓይኖቿ የልጇን ፊት ለመመልከት ሞከረች። ቁጣ አክስሏታል።

አይኖቿ ከልጇ ፊት ሲሸሹ ከግድግዳው ጋር ተላተሙ። ስንጥቅጥቅና ሽንቁር በበዛበት ግድግዳ ላይ ጎልቶ የሚታየው የታላቅ ልጅዋ ምስል ነበር። የዲግሪ ቆብ የጫነ ዕለት የተነሣው ፎቶ። በልጅነቱ ያጣውን ያባቱን መልክ ወርሷል። የተሸበሸበ ግንባር፤ ደም የጎረሰ አይን፣ የተነፋ ከንፈር አለው።

"አሁን እሡም ተማርሁ ሊል ነው?"

አምና ሐምሌ ላይ ነበር የተመረቀው።

ከተመረቀ ከሁለት ወራት በኋላ ትምህርቱን በቋጨበት በዚያው አዲስ አበባ በአንድ ትልቅ የንግድ ድርጅት ውስጥ እንደተቀጠረ ባህርዳር ከታናሽ እህቱ ጋር ለምትኖረው እናቱ ደውሎ ነግሯታል። በቃ፤ ከዚያ በኋላ ኮቴውን አልሰማችም። ድምጹን አላዳመጠችም። ሲሣዩን አልተካፈለችም።

ቀን-ቀናት- ሣምንት- ሣምንታት-ወር-ወራት-አመት።

እናቲቱ የልጇ ከፊቷ መሠወር አሠጋት።

ልጂቱ የወንድሟ እጅ መራቅ አበገናት።

"...ከእኔ የበለጠ ተንከባክብሽ አሳደግሽው!... አስተማርሽው!...እኔ የሱን ጥብቆ እንዳጥብ ለሱ አሻሮ እንድቆላ ፈረድሽብኝ...እናም የመጨረሻው ዕጣ ፈንታዬ አመድ ውስጥ መገኘት ሆነ...እሱ ግን ተምሮ ትልቅ ቦታ ደረሰ...መማሩ ግን ለእናቱ የሚሆን ርኅራሄ አልፈጠረለትም...ይኸው ዓይንሽን ስትታመሚ

እንኳ እግዜር ይማርሽ መች አለሽ?!"

የልጂቱ ድምፅ ተንጉደጎደ።

በቅርብ ቀን ነው የአይን ህመም የተፀናወታት። ከየት እንደመጣ ምን እንዳመጣባት ልብ አላለችውም። ድንገት አይኖቿ አባብጠው እኻ ማጉረፍ ያዙ። ይኸው በየሌሊቱ እንቅልፍ የላትም። በየመዓልቱ እረፍት አላገኘችም። ደህንነት ርቋታል።

እናም አይኗ ወደጥንተ ደህንነቱ እንዲመለስ ጓጓች። ጓጉታም አልቀረች። የግል ሀኪም ደጅ ጠናች። ሀኪሙ ግን ከቶ የማትችለውን ጠየቃት። ሶስት መቶ አምሣ ብር።

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እናቲቱ ለህክምና የሚያስፈልጋትን ገንዘብ የምታገኝ ይመስላችኋል: ከማን ?
2. በእናቲቱና በልጅትዋ መሀከል ያለው የሀሣብ አለመግባባት መንስኤው ምንድን ነው?
3. የቀረበላችሁ ልቦለድ ታሪክ እንዴት ይጠናቀቃል ብላችሁ ትገምታላችሁ?



ምሥል 8 ፡ እናት እንጀራ እየጋገረች ከልጇ ጋር ስትነጋገር

"እሱሥ ግድ የለም! አንዴ አምጾብሻል!...እኔ አጠገብሽ ያለሁት እድለ ቢስ እንኳ ልታደግሽ አቅም አጣሁ!....ምን ላርግ!..ያንድ መናኛ መሥሪያ ቤት የፅዳት ሠራተኛ!..."

በወር መቶ ብር ይከፈላታል። መቶ ብሩ የሷንና የእናቷን ጉሮሮ መድፈን ስለሚቻለው አጣጥላው አታውቅም ነበር። አሁን ግን የእናቷን አይን የማሳከም አቅም እንደሌለው ስታውቅ ናቀችው።

"እንደድሮው 'ተበደሪ' ብልሽ አሻፈረኝ አልሽ!"

ልጂ ከመመረቁ በፊት ሰፈርተኛውን ያስመረረች ተበዳሪ ነበረች። ልጂን እንዳይከፋው የብዙ ቱጃር ሰፈርተኞችን ደጅ ጠንታለች። ስራ ከያዘ በኂላ ግን መበደሩን እርግፍ አድርጋ ተወችው።

"እኔም እንዳልበደር አስማልሽኝ!...መበደርን የምትፈሪው ዕዳ መክፈሉን ተማርረሽ ሳይሆን ለልጅሽ ክብር ስትይ እንደሆነ አውቃለሁ።"

"በሰፈሩ ውስጥ ያሉት ወሬኞች ክፉዎች ናቸው። ብበደር ልጅዋ ገንዘብ ነፈጋትና ተቸገረች

ይሉኛል፡፡ ልጄን ያብጠለጥሉብኛል፡፡ አንድ ቀን እትብቱ ወደተቀበረበት አፈር ይመለስ ይሆናል፤ ያኔ እናቱን የረሣ እያሉ መቆሚያ መቀመጫ ያሳጡብኛል፡፡ ስለዚህ ባልበደር ይሻላል" ያለቻትን አስታወሰች፡፡

የጎጆው በር ባይከፈት ኖሮ የልጅቱ ወቀሣ የሚገታ አልነበረም፡፡

"እንደምን ሠንብታችኋል!"

ወደ ውስጥ ዘለቁ፡፡

የታላቁ ልጅ የክርስትና አባት ናቸው፡፡

"ዘሀር ምስጌን ደህና ሰንብተዋል?"

"....ተሻለሽ?"

ከተቀመጡ በኋላ፡፡

የፊታቸው ወዝ ያብረቀርቃል፡፡

"ደህና ነኝ!"

እናቲቱ ለወጉ ያህል መለሰች፡፡

"ምን ደህና ነሽ?" እንደባሰብሽ ልትልኪብኝ ሲገባ ተሌላ ሰው አፍ ሰማሁት... በውነቱ ደግ አይደለም፡፡" አሉ የእናቲቱን አይን ሣይሆን ወለል ወለሉን እያዩ፡፡ "አሁን ወደ ሀዘን ቤት ስሄድ እግረ መንገዴን ልጠይቅሽ ብየኮ ነው"

"አሁን ልትታከም አስባለች..." አለች ልጂቱ፡፡

"እስታሁን መቆየቷ ራሱ ትልቅ ስህተት ነው!"

"ለመታከሚያ ግን ብዙ ብር ጠየቁን" ልጅቱ ፈጠን አለች፡፡

"ምን ያህል?"

"ሶስት መቶ አምሳ"

በድምጽዋ ውስጥ ተስፋ አለ፡፡

እንደማይጨክኑ ገምታለች፡፡ በለጋስነታቸው ስመጥር አዛውንት ናቸው፡፡ እንኳን ለተዛመዳቸው ለባዕድ እንኳን ዘግነው በመስጠት ይታወቃሉ፡፡ ውጭ አገር የሚኖር ታናሽ ወንድማቸው ገንዘብ በላከላቸው ቁጥር በመንደር እየተዟዟሩ ወገን ይጠይቃሉ፡፡

አንድ ድክመት ግን ነበረባቸው፡፡

እንደኪሣቸው ሁሉ አንደበታቸው መቋጠር አያውቅም፡፡ በየሄዱበት ሁሉ ስለልግሰናቸው እንዳወጉ አሉ፡፡

"ሶስት መቶ አምሣ አልሽኝ?!"

ልጂቱ ራሷን በአዎንታ ነቀነቀች፡፡

"ቀላል ነዋ! አይንኮ በምንም ዋጋ አይተመንም!" አዛውንቱ ዘና አሉ፡፡

ልጅቱና እናቲቱ አረመሙ፡፡

አዛውንቱ ዙሪያ ገባውን ገረመሙት፡፡ ሁሉ ነገር ባዶና ቀዝቃዛ ሆነባቸው፡፡ እናም መዳፋቸውን በነጩ ካፓርታቸው የውስጥ ኪስ ውስጥ ከተቱት፡፡

"ሶስት መቶ አምሣማ!"

አሉ ደገሙና፡፡

የልጂቱ ልብ ስስ ደረቷን ከውስጥ ደበደበው፡፡ ልውጣ ልውጣ የሚለውን ትንፋሿን ላፍታ ገድባ ያዘችው፡፡ ያዛውንቱ መዳፍ የሚመለስበትን ቅጽበት ናፈቀች፡፡

"ሶስት መቶ …አ…ም…ሣ…ማ!"

ክብደት በሌለው ድምጽ እያጉተመተሙ ያበጠ የገንዘብ ቦርሣቸውን አወጡ፡፡ ልጂቱ ጣቷን አቆላልፋ ጠበቀች፡፡ ትኩሣት በመላው ሰውነቷ ተለቋል፡፡ ወደ እናቷ ተመለከተች፡፡ የእናቷ አይኖች እብጠታቸውን ጨምረው ታይዋት፡፡

ያዛውንቱ ዓይኖች ድንገት ግድግዳው ላይ ከተሠቀለው ፎቶ ላይ አረፉ፡፡

"ለመሆኑ ይሄ ልጅ ይደውላል?"

"አዎ ይደውላል!"

ልጂቱ የወንድሟን ፎቶ በልቧ ረገመች፡፡

"ገንዘብስ እየላከ ነው?"

"አዎ ይልካል!" እናቲቱ መለሠች፡፡

የልጅቱ ፊት እንደ እስስት ቆዳ መቀያየር ያዘ፡፡

"ታዲያ በወር ሁለት መቶ ባውንድ እየዛቀ ሽራፊ ሣንቲም ብቻ መወርወር ዋጋ የለውም! ስትታመሚም መታከሚያ ገንዘብ ዛቅ አድርጎ መላክ ነበረበት፡፡ ልጅ የዚህ ጊዜ ያልሆነ ለመቼ ሊሆን ነው?…ውነቴን ነው!… እኔ ወንድሜ ነው እንዲህ በስተርጅና እሚያቀማጥለኝ…መታከሚያ መላክ ነበረበት" አሉ የቦርሣቸውን አፍ እያሠፉ፡፡

"ልኮልኛልኮ!" መለሰች እናቲቱ

"ለመታከሚያ የላከው ብር ትናንት ደረሰኝ…

እንዴት ያለ የተባረከ ልጅ መሠሎት! የኔ ነገር አያስችለውም መቼም!…"

"ጎሽ…ስንት ላከ ?"

"የሚበቃኝን ያህል ልኮልኛል!"

ፈገግ ልትል ሞከረች፡፡ ፈገግታዋ ግን ለነፋስ እንደተጋለጠ የጧፍ ብርሃን ዕድሜ አልነበረውም፡፡

አዛውንቱ ቦርሣቸውን ወደኪሣቸው መለሱት፡፡

ልጂቱ ብድግ ብላ ወደ ጽልመታማው ጓዳ ገባች፡፡

"በይ እንግዲህ ታከሚው!…ጊዜ ልትሰጭው አይገባም፡፡ ተሰናብተው ወጡ፡፡

በሩን አልፈው ሲሰወሩ እናቲቱ "እፎይ!…" አለች፡፡ በህመሟ ውስጥ ደስታ ተሰማት፡፡ የልጅዋ ክርስትና

አባት ወደ ሀዘን ቤት እንደሚሄዱ ነግረዋታል:: እዚያ ሄደው ስለችሮታቸው ለሰፈርተኛው ሁሉ ያወራሉ:: ችሮታው ከደረሳቸው ያጡ የነጡ ሰዎች መካከል የሷ ስም እንደማይኖር ርግጠኛ ሆናለች:: ስለዚህም የልጇ ስም በክፉ አይነሣም:: ፈጽሞ!

(በዕውቀቱ ስዩም፤ እናቲቱ (1994፤ 66-67) ብሌን መጽሄት ለማስተማር እንዲያመች ተደርጎ የተወሰደ)

## ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

ሀ. የልቦለዱን ታሪክ መሠረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች በቃላችሁ ምላሽ ስጡ::

1. እናቲቱና ልጅትዋ የሚኖሩበት ቤት ምን ይመስላል?
2. እናቲቱ ከልጅትዋ ጋር ክርክር የገባችበት ጉዳይ ምን ነበር?
3. "እንደድሮው 'ተበደሪ' ብልሽ አሻፈረኝ አልሽ!" ብላ ልጅቷ እንድትናገር ያደረጋት ምክንያት ምንድን ነው?
4. እናቲቱ ሊጠይቁዋቸው ከመጡት ዘመዳቸው ለመታከሚያ የሚሆን ገንዘብ ለመቀበል ያልፈለጉት ለምንድን ነው?
5. ልጅቱ ወንድሟን አምርራ የምትተችበት ምክንያት ምንድን ነው?
6. እናቲቱ ወንድ ልጃዋን በተመለከት ያላት አስተያየት ምን ይመስላል? ምክንያቱስ ይታወቃል?

ለ. የልቦለዱን ታሪክ መሰረት በማድረግ ከታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አሟሉ::

1. የልቦለዱ ርዕስ _____እናቲቱ______________________________
2. መቼና የት ተፈፀመ ______________________________________
3. የገፀ-ባህሪያት ብዛት ________________________________________
4. ዋና ገፀ ባህሪ _____________________________________________
5. ዋናው ገፀባህሪ ምን ይፈልጋል ________________________________
6. ዋናው ገፀባህሪ ያጋጠሙት ችግሮች _____________________________
7. መሰናክል አንድ:-----------------------------------------------
8. መሰሰናክል ሁለት--------------------------------------------
9. ገጸባህሪው ከደረሰበት ችግር ለመውጣት ያደረገው ጥረት------------------
10. የመጨረሻው ውጤት---------------------------------------------------------

### የልቦለድ ገፀ ባህሪያት

ገፀባህሪያት በልቦለድ አለም ስጋ ለብሰው፣ ባህሪ ተጎናፅፈው፣ መጠሪያ ተሰጥቷቸው፣ መኖሪያ ተበጅቶላቸው፣ የሚንቀሳቀሱ፤ የሚተነፍሱ፤ የሚናገሩ፤ የሚበሉ፤ የሚጠጡ፤ እንደ አውኑ አለም ሰዎች የሚኖሩ፤ የሚሞቱ፤ የሚርባቸው፤ የሚጠማቸው፤ የሚፋቀሩ፤ የሚጣሉ፤ የሚደሰቱና የሚያዝኑ የልቦለድ አለም ሰዎች ናቸው።

በልቦለድ ውስጥ የሚገኙ ገፀባህሪያት በተለያየ መንገድ ሊከፈሉ ይችላሉ። ከነዚህም መካከል፡-

1. ዋና ገፀ-ባህሪ፡- በልቦለዱ ውስጥ የሚተረከው ታሪክ በዋነኛነት የሚመለከተው ባለታሪክ ነው።
2. ንዑስ-ገፀ-ባህሪ፡- ከዋናው ገፀባህሪ አንፃር የተለየ ፍላጎት፣ ተግባርና ግብ ይዞ የሚቀረጽ ባለታሪክ ነው።

(ዘሪሁን አስፋው፡- የስነ-ጽሁፍ መሠረታዊያን 1992፤ ገጽ፡- 160)

### አጭር ልቦለድ

አጭር ልቦለድ የራሱ ቅርጽና ይዘት ያለው፣ ከሌሎች የስነጽሁፍ ዘሮች ተለይቶ የሚታወቅባቸው ባህሪያት ያሉት፤ በራሱ ክልል ሲጠናና ሲመረመር የራሱ የሆነ ኪነጥበባት ስርዓት የሚታይበት፤ በራሱ መጠነርእይ ውል ያላቸው ማህበረሰባዊ አውነታዎችን ሊያሳይ የሚችል አንድ የስነጽሁፍ ዘር መሆኑ የታወቀ ነው። አጭር ልቦለድ የሚከተሉት ባህርያት አሉት። እነሱም፡-

1. ነጠላ ውጤት
2. ጥድፊያ
3. ቁጥብነት ናቸው።

፫. በቡድን ሆናችሁ በመወያየት የሚከተሉትን አባባሎች ፍች ከገለፃችሁ በኋላ አረፍተ ነገር አረባቸው።

ምሳሌ፡- ባፍንጫዬ ይውጣ

ፍቺ፡- ይቅርብኝ

አረፍተነገር፡- እንዲህ ከሆነስ በአፍንጫዬ ይውጣ።

| ተ.ቁ | አባባል | ፍች/ትርጉም | ዐረፍተ ነገር |
|---|---|---|---|
| 1 | እጅ ራቀ | | |
| 2 | ውሃ ሆነ | | |
| 3 | ዐይኑ ደም ለበሰ | | |
| 4 | ከንፈሩን ነፋ | | |

| ተ.ቁ | አባባል | ፍች/ትርጉም | ዐረፍተ ነገር |
|---|---|---|---|
| 5 | ልብ አለች | | |
| 6 | እድለ ቢስ | | |
| 7 | ያጣ የነጣ | | |
| 8 | እስስት ቆዳ | | |
| 9 | እትብቱ የተቀበረበት | | |
| 10 | አመድ አፋሽ | | |

## ክፍል አራት፡ ቃላት

ሀ. የሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ ውስጥ የያዙትን አገባባዊ ፍች በቃል አስረዱ፡፡

1. ረበበ
2. ሰበቀ
3. ከሰለ
4. ተመረቀ
5. ሠወረ
6. መድፈን
7. ዘገነ
8. ቋጠረ
9. ወገን
10. ስስ

*የቃላት አውዳዊ ፍች* ፡- አንድ ቃል በተለየዩ አውዶች ውስጥ ሲገኝ የሚኖረው አገባባዊ ፍች እንደ ዓረፍተ ነገሮቹ ይለያያል፡፡ የአንድ ቃል ትክክለኛ ፍች የሚታወቀው በዓረፍተ ነገር ውስጥ ገብቶ ከሌሎች ቃላት ጋር በመሆን መልዕክት ሲያስተላልፍ ነው፡፡

## ክፍል አምስት፡ ጽሕፈት

ሀ.ቀጥሎ ከአጭር ልቦለዱ የተወሰዱ ሀረጎችና ዓረፍተ ነገሮች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ሀረጎችና ዓረፍተ ነገሮች የሚያስተላልፉትን ሃሳብ በራሳችሁ አገላለፅ አብራርታችሁ ፃፉ፡፡

1. ቁጣ አክስሏታል
2. ሲሣዩን አልተካፈለችም
3. እኸ ማጉረፍ ጀመሩ
4. ገረመሙት
5. ከግድግዳ ጋር ተላተሙ
6. ችሮታ
7. ዛቅ አድርጎ
8. ደጅ ጠንታለች
9. ያብጠለጥሉብኛል
10. እሚያቀማጥለኝ

፪. ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላት በምንባቡ ውስጥ በተተውት ባዶ ቦታዎች ውስጥ በማስገባት አንቀጹን አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡

1. አብቦ
2. ይነዙት
3. አደባልቆ
4. አፍርቶ
5. ዘቅዝቆ
6. ለድርቆሽ
7. ዥንጉርጉር
8. ፀደይ

ግቢ በሚሉት ሰፊ ሜዳ ____________ የሚያስጠብቁት ከሰርዶ ካክርማ ከጉድይና ከዋራት አንድ ላይ ____________ ያደገው ሳር፡- ቀደም ብሎ የበቀለው __________ ዘግየት ብሎ የበቀለው ቢጫ፣ ሰማያዊ፣ ነጭና ቀይ አበባ____________ ሰብለ ወንጌል ከተቀመጠችበት______________ ሲመለከቱት ያን ሰፊ ግቢ ለማስጌጥ ከዳር እስከ ዳር የተዘረጋ አምሮ የተሰራ______________ ምንጣፍ ይመስል ነበር፡፡ ፀሃይ እየሞቀ በሄደ መጠን በዚያ ሰፊ ግቢ የተነጠፈው ሳርና በቤቶች አካባቢ የተተከሉ የፍሬ አትክልት አንድ ላይ ባየር_______________ የነበረው ገነታዊ መዓዛ ሽቶ በብዙው እንደተረፈረፈበት መዋኛ ከውስጡ መውጣት አያስመኝም ነበር፡፡

፫.ከዚህ ቀጥሎ ቅደም ተከተላቸዉ ተዘበራርቆ የተቀመጡትን ዐረፍተ ነገሮች በማስተካከል አንድ አንቀጽ ጻፉ ፡፡

1. ቅጠሉን የድንጋይ ወፍጮ ላይ አድርጋ እስኪልም ድረስ ጨቀጨቀችው፡፡
2. ከእውነተኛ ፍቅር ጋር የሰጠችው ፍቱን መድሐኒት ቶሎ ብሎ እንደሚፈውሰው እየተማመነች በጅምር ወደተወችው የማጀት ሥራዋ ተመለሰች፡፡
3. በመጨረሻም ወለላ ሲመስል ትንሽ ውሃ ጨመረችበትና በሸክላ የተሰራች ትንሽ ብቸሬ ውስጥ ጨመረችው፡፡
4. ማሚቴ የተረፈውን መራራ አፉ ላይ ጠብ፣ ጠብ…እያደረገች ካንጠፈጠፈችለት በኋላ ቀስ አድርጋ የእንጨት ትራሱ ላይ አሳረፈችው፡፡
5. ፈጠን ፈጠን እያለች ወጣችና ወደ ጓሮ ሄደች፡፡
6. ዳሞቴም የታዘዘለትን መራራ ጭማቂ በአንድ ትንፋሽ ዥው አድርጎ ጨለጠው፡፡
7. የምታስበው ራታቸው በሰዓቱ እንዲደርስ አብዝታ ጥድፍ-ጥድፍ ብትልም እንኳን የዳሞቴ ነገር አልተዘነጋትም፡፡
8. ተንከባክባ ካሳደገቻቸው ፈዋሽ እፅዋት ከአንደኛው ላይ ትንሽ ቅጠሎች በጠስ፤ በጠስ አደረገችና ተመለሠች፡፡
9. ለባለቤቷ የተዘጋጀለትን መድሃኒት እንዲጠጣ ነገረችውና ደገፍ አድርጋ አንገቱን አቃናችለት፡፡
10. የጠጣው መድሃኒት መራራነት ጭምትርትር ያለ ፊቱ ላይ ተጽፎ ይነበባል፡፡

፬.ቀጥሎ አንድ ጽሁፍ ቀርቧል፡፡ ይህንን ጽሁፍ በቡድን ሆናችሁ አንዱ ሲያነብ ሌሎቻችሁ አድምጡ፡፡ ከዚያም የጽሁፉን መልዕክት ተወያዩበት፡፡ በመጨረሻም ይህንን ጽሁፍ መነሻ በማድረግ ለጓደኛችሁ ደብዳቤ ፃፉ፡፡

ለተወዳጅዋ እህቴ ለወይዘሪት ብስራት፡፡ አይቼሽ ድንገተኛው ፍቅርሽ የዘወትር ሰቀቀን ሆኖብኛል፡፡ በፍቅርሽ ወጥመድ ውስጥ ገብቼ በጉምዥት ካራ መተፍተፍ ከጀመርኩ ውዬ አድሬያለሁ፡፡ ዳሌሽ፣ ጡቶችሽ፣ ፀጉርሽ፣ አንገትሽ ብዬ ውበትሽን ለማድነቅ አልሞክርም፡፡ ቃላት አጥሮብኝ በጅምር ከምተወው አለመሞከሩን መርጫለሁ፡፡ ፈጣሪ ብዙ ሰዎችን መሥራት የሚችልበትን ጊዜ በአንቺ ላይ አጥፍቷል፡፡ ተጠቦ ተጭንቆ የሰራሽ በመሆንሽ ኩራት ይሰማሻል፡፡ አንቺን በማፍቀሬ እኔም ኩራት ይሰማኛል፡፡ በዓይኖችሽ ግርፍታ ከተገረፍኩ ወዲህ ዋኘቼ ከማልወጣበት የፍቅር ባህር ውስጥ ገብቻለሁ፡፡ ከአንቺና አንቺን ከወደደው ከእኔ ሰውነት በቀር ሌላ ማየት አስጠልቶኛል፡፡ የምበለው አይስማማኝም፣ የሰዎች ወሬ አይጥመኝም፡፡ ምን አለፋሽ ዘመድ የሌለው እብድ ሆኜልሻለሁ፡፡ ይህ ሁሉ አንቺን በማፍቀሬ አንቺን በመውደዴ ነው፡፡ ብስራት! ፍቅረኛዬ እንድትሆኚ መርጬሻለሁ፡፡ እንደ ማትጨክኚብኝ አምናለሁ፡፡ በእኔ መጨከን ያን ተጭንቆ ተጠቦ የሰራሽን አምላክ ማስቀየም ነው፡፡ ዓይኖችሽ ብዙ በማንበብ እንዲቀሉ አልፈልግም፡፡ መልሰሽ አጭር ቢሆን ደስ ይለኛል፡፡ ቁርጥ ያለ፡፡ እሽ ወይም እምቢ፡፡ ይህን ያልኩሽ ያንቺን መልስ ማንበብ ይሰለቸኛል ብዬ አይደለም፡፡ ብዙ በመፃፍ እንደ አለንጋ ጣቶችሽ በብዕር እንዲዶለድሙ አልፈልግምና ነው፡፡ በተስፋ መልስሽን እጠብቃለሁ፡፡ ሰላምና ጤና ካንቺ ጋር ይሁን፡፡

የፍቅርሽ ምርኮኛ መዳቡ ዳዲ

ህዳር 21 ቀን 1950 ዓ.ም

(ምንጭ ሰለሞን ስሜ፣ ደብዳቤው፡፡ ለማስተማር እንዲያመች ሆኖ የተወሰደ)

### የደብዳቤ አፃፃፍ ሥርዓት

ሰዎች ደብዳቤ ለተለያዩ ዓላማዎች ይጽፋሉ፡፡ የሚያስተላልፉትን ሀሳብ መነሻ በማድረግ ደብዳቤዎችን በተለያዩ መንገዶች መከፋፈል ይቻላል፡፡ እነዚህንም የሰላምታ ደብዳቤ እና የስራ ደብዳቤ ብሎ መመደብ ይቻላል፡፡ ሁለቱ የደብዳቤ አይነቶች የየራሳቸው ያፃፃፍ ስርዓት አላቸው፡፡

1. የሰላምታ ደብዳቤ የሚፃፈው በሁለት ሰዎች፣ በቤተሰብ ወይም በፍቅረኛሞች መካከል ሊሆን ይችላል፡፡
2. የሥራ ደብዳቤ የሚባለው አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት ለሚሰራበት መስሪያ ቤት፣ የንግድ ስራ፣ ወዘተ. አስመልክቶ ለቢሮ ሃለፊ ወይም ለንግድና መሰል ድርጅቶች የሚፅፈው የደብዳቤ አይነት ነው፡፡

ይህ የደብዳቤ አፃፃፍ የሚከተላቸው ቅደም ተከተላዊ የአፃፃፍ ስርዓቶች አሉት፡፡ ለምሳሌ ያህል የደብዳቤው ቁጥር፣ የተፃፈበት ቀን፣ የላኪው ድርጅት ወይም ግለሰብ ሙሉ ስምና አድራሻ፣ የተቀባዩ ድርጅት ሙሉ ስምና አድራሻ፣ ደብዳቤው የተፃፈበት ጉዳይ፣ የመዝጊያ ሀረግ፣ የላኪው ግለሰብ ወይም ድርጅት ኃላፊ ፊርማ፣ ክብ ማህተም የደብዳቤው መልዕክት የሚመለከተው ግለሰብ/ድርጅት ካለ በአድራሻ ግልባጭ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ስድስት:-ሰዋስው

### ሥርወ-ቃል

ሥርወ ቃል ማለት አንድ ቃል ቅጥያዎችን ከማስቀጠሉ በፊት ያለው መሰረታዊ ቅርፅ ነው። ስርወ-ቃል የቃሉን መሰረታዊ ትርጉም የሚሸከም አሀድ ነው። ለምሳሌ "ቤታችንን" የሚለውን ቃል ስንመለከት፤

የተሰጠው ቃል፡- ቤታችንን

ስርወ-ቃል፡- ቤት

ቅጥያ 1፡- -ኣችን

ቅጥያ 2፡- -ን

እንደምትመለከቱት ይህ ስርወ-ቃል ሁለት ቅጥያዎችን አስቀጥሏል። ቅጥያዎቹም የተለያዩ ተግባራትን ለመፈፀም የገቡ ናቸው። ይኸውም፡- /-ኣችን/ የሚያመለክተው ቤቱ የማን እንደሆነ ሲሆን፤ /-ን/ ደግሞ የተሳቢ ምልክት ነች። ይሁንና እነዚህ ቅጥያዎች ሊቀጠሉ የቻሉት በስርወ-ቃሉ ላይ ነው። ስርወ-ቃል ከሌለ ቅጥያም አይኖርም።

፩.ቀጥሎ በተዘረዘሩት ቃላት ውስጥ የሚገኙትን ቅጥያዎችና ሥርወ-ቃሎች ለይታችሁ ጻፉ።

| ተራ ቁ. | የተሰጠው ቃል | ቅድመ ቅጥያ | ስርወ-ቃል | ድህረ ቅጥያ |
|---|---|---|---|---|
| ሀ | በቀረ | | | |
| ለ | የልጅዋን | | | |
| ሐ | እንደድሮው | | | |
| መ | ከተመረቀ | | | |
| ሠ | በማህፀንሽ | | | |
| ረ | ነበረች | | | |
| ሰ | የተሸበሸበ | | | |
| ሸ | እንደተቀጠረ | | | |
| ቀ | ከልጅዋ | | | |
| በ | በጣዩችሽ | | | |

፬. የሚከተሉትን ዓ.ነገሮች ባለቤት፤ ተሳቢና ግስ(ማሰሪያ አንቀጽ) ለይታችሁ አሳዩ፡

ምሳሌ፡- 1. እናቲቱ ትከሻዋን ነቀነቀች፡፡

ባለቤት፡- እናቲቱ

ተሳቢ፡- ትከሻዋን

ግስ (ማስሪያ አንቀጽ)፡- ነቀነቀች

1. እናቲቱ የታላቅ ልጅዋ ምስል ታያት፡፡
2. ልጅቱ ድምፅዋ ተንጎደጎደ፡፡
3. ልጁ የአባቱን መልክ ወርሷል፡፡
4. የልጅቱ ወቀሳ የሚገታ አልነበረም፡፡
5. ወይኒቱ የወንድምዋ እጅ መራቅ አበገናት፡፡
6. እናቲቱ የግል ሀኪም አማከረች፡፡
7. ልጁ እንደተመረቀ ሥራ ያዘ፡፡
8. ሽማግሌው ከኪሳቸው ቦርሳውን አወጡ፡፡
9. እናቲቱ የሰፈር ወሬ ይጠላሉ፡፡
10. ልጁ ለእናቱና ለእህቱ ደብዳቤ ፃፈ፡፡

፭. ከዚህ በታች በነጠላ ቁጥር የቀረቡ ስሞች ወደ ብዙ ቁጥር በተለያዩ ስልቶች ተቀይረዋል፡፡ እናንተም የቀረበላችሁን ምሳሌ መነሻ በማድረግ ነጠላ ስሞችን ወደ ብዙ ቁጥር ለውጣችሁ በተሰጠው ሰንጠረዥ ውስጥ ሙሉ፡፡

| ተ.ቁ | ስም | ብዙ ቁጥር በአማርኛ ስልት | ብዙ ቁጥር በግዕዝ ስልት |
|---|---|---|---|
| 1 | ክፋ | ክፋዎች | |
| 2 | ነፍስ | ነፍሶች | ነፍሳት |
| 3 | ሳምንት | ሳምንቶች | ሳምንታት |
| 4 | ወሬ | | |
| 5 | አመት | | |
| 6 | ቀን | | |
| 7 | መምህር | | |
| 8 | መልአክ | | |
| 9 | ተማሪ | | |
| 10 | መሰንቆ | | |
| 11 | ህፃን | | |
| 12 | መጽሀፍ | | |
| 13 | ቤት | | |

፬. ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ መጠንን ለማሳየት የገቡትን ገላጭ ቃላትና ሀረጋት ለይታችሁ አውጡ

ምሳሌ፡- አንድ ድክመት ነበረባቸው

መጠን ጠቋሚ ቃል፡- አንድ

1. ሁለት ነፍሶች ተፋጠው ነበር፡፡
2. ከሁለት ወር በኋላ ተገናኙ፡፡
3. መቶ ብር በወር ይከፈላታል፡፡
4. ሦስት መቶ ሀምሳ ብር በማጣትሽ አይንሽ ሊጠፋ ነበር፡፡
5. ብዙ በጎች አሉት፡፡
6. ጥቂት መጽሀፎች ገዛሁ፡፡
7. አያሌ ህጻናት ሜዳው ላይ ይጫወታሉ፡፡
8. አንድ ስንዝር ገመድ አምጣልኝ፡፡
9. በርካታ ሀሳቦች አሉት፡፡
10. አስራ ሁለት ወር አንድ ዓመት ይሆናል፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዘህ ምዕራፍ ልዩ ልዩ ርእሰ ጉዳዮች በትምህርነት ተነስተዋል፡፡ በመነሻው አንድ አጭር ተረክ ተነቦ ለማዳመጥና ለንግግር ክሂሎች ማስተማሪያ የሚሆኑ መልመጃዎች ተሰርተዋል፡፡ በዚህም የተረኩን ጭብጥ፣ የቃላትና ሀረጋት አገባባዊ ፍችዎች በቃል መልስ ተሰጥቶባቸው፤ ተማሪዎቹ አከራካሪ የሆኑ ርዕሶችን በቡድን መርጠው በመወያየት ክርክር ተደርጓል፡፡

የቀረበውን አጭር ልቦለድ በማንበብ በተለያዩ መልመጃዎች መነሻነት ስለ ጭብጡ፣ ስለታሪኩ አወቃቀር፣ ፈሊጣዊ አባባሎች ፍች መልሶች በቃልና በጽሁፍ ተሰጥተዋል፡፡ ስለአጭር ልቦለድ ምንነትና ባህርያት በቀረበው አጭር ማስታወሻ መነሻነት ገለጻና ውይይት ተደርጓል፡፡ የቃላት አገባባዊ ፍች ተሰጥቷል፡፡ ከአጭር ልቦለዱ የተወሰዱ ሀረጎችና ዓረፍተ ነገሮች የሚያስተላልፉት ሃሳብ ተብራርቶ በጽሁፍ ቀርቧል፡፡ ቃላት በተገቢው ቦታቸው በአንቀጽ ውስጥ ገብተው አንቀጹ ተስተካክሎ እንደገና ተጽፏል፡፡ የደብዳቤ አይነቶችን፤ አጻጻፍ ስርኣትን በቀረበው አጭር ማስታወሻ አማካኝነት ገለጻ ተደርጎ የግል ደብዳቤ ተማሪዎቹ ጽፈዋል፡፡ በሰዋስው ክፍል ስለስርወ ቃል ምንነት ገለጻ ቀርቦ ቅጥያዎችና ሥርወ-ቃሎች ተለይተው እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡ የዓረፍተ ነገሮች ባለቤት፤ ተሳቢና ግስ(ማሰሪያ አንቀጽ) ተለይተው ቀርበዋል፡፡ በነጠላ ቀጥር የቀረቡ ስሞች ወደ ብዙ ቁጥር በተለያዩ ስልቶች አማክኝነት ተለውጠዋል፡፡ መጠንን ለማሳየት የገቡ ገላጭ ቃላትና ሀረጋት ከዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ተለይተው ወጥተዋል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የዋኄዋ ምክር ሰውየውን የለወጠው ይመስላችኋል? እንዴት? አስረዱ።
2. የአጭር ልቦለድ ባህርያትን በአጭሩ አስረዱ።
3. እናቲቱ በሚለው ልቦልድ ውስጥ ትክክለኛ ሀሳብ ነው የምትሉት የማንን ነው?
4. የዓረፍተ ነገር ተዋቃሪዎችን ባጭሩ አስረዱ።
5. "የጎረቤቶቻችንን" በሚለው ቃል ውስጥ ስርወ ቃሉንና ቅጥያዎችን ለይታችሁ አሳዩ።

## ክፍል ሰባት፡ የግንዛቤ ማመሳከሪያ ነጥቦች

ከዚህ በታች በምዕራፉ የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች ምን ያህል እንደተረዳችኋቸው ለማረጋገጥ የሚረዱ ማመሳከሪያ ነጥቦች ተዘርዝረዋል። በመሆኑም ዝርዝሮቹን በጥንቃቄ በማንበብ፤ ተረድታችኋቸው ከሆነ ከፊትለፊታቸው ባለው ሳጥን ውስጥ የ(V) ምልክት በማድረግ አረጋግጡ። ያልተረዳችሁት ወይም የሚያጠራጥራችሁ ከሆነ ግን በሳጥኑ ውስጥ የ (?) ምልክት በማድረግ ያልተረዳችኋቸውን ነጥቦች ደጋግማችሁ ከልሱ።

| ተ.ቁ | ማመሳከሪያ ነጥብ | (√) | (?) |
|---|---|---|---|
| 1 | ያዳመጥሁትን ፅሑፍ መልዕክት ተረድቻለሁ። | | |
| 2 | የአጭር ልቦለድ ምንነትን ተረድቻለሁ። | | |
| 3 | የአጭር ልቦለድ ባህሪያትን አውቄያለሁ። | | |
| 4 | የልቦለዱን ጭብጥ ተረድቻለሁ። | | |
| 5 | ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ሰጥቻለሁ። | | |
| 6 | አንቀጽ በትክክል ፅፌያለሁ። | | |
| 7 | የአረፍተ ነገር ተዋቃሪዎችን ለይቻለሁ። | | |
| 8 | ከሀረጋት ውስጥ መጠን አመልካች ቃላትን ለይቻለሁ። | | |
| 9 | ነጠላ ቁጥር ስሞችን በግዕዝ እና በአማርኛ ስልት ወደ ብዙ ቁጥር ስሞች ቀይሬያለሁ። | | |
| 10 | ከቃላት ውስጥ ስርወ-ቃላትን ለይቼ አውጥቻለሁ። | | |

# ምዕራፍ አሥር ፡ አርበኝነት

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ ስር የቀረበውን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኂላ፡-

- ካዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ መልዕክቱን ታስረዳላችሁ፡፡
- ካዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ ዝርዝር መረጃዎችን ታወጣላችሁ፡፡
- በተመረጡ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ትወያያላችሁ፤ ትናገራላችሁ፡፡
- የምንባቡን ጭብጥ በቃል ታስረዳላችሁ፡፡
- ለቃላት ተመሳሳይ እና አገባባዊ ፍቾ ትሰጣላችሁ፡፡
- በተሰጠው ርዕሰ ጉዳይ ድርሰት ትፅፋላችሁ፡፡
- ስማዊ ሀረጎችን እና ግሳዊ ሀረጎችን ትለያላችሁ፡፡
- የተውሳከ ግሶችን ተግባር ታብራራላችሁ፡፡
- አዎንታዊ አረፍተ ነገሮችን ወደ አሉታዊ አረፍተ ነገር ትቀይራላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ኮሎኔል አብዲሳ አጋ

ተማሪዎች! መምህራችሁ "ኮሎኔል አብዲሳ አጋ" በሚል ርዕስ ኢትዮጵያዊው ጀግና የፈፀሙትን ዓለማቀፋዊ ጀግንነት የሚያወሳ ታሪካዊ ጽሑፍ ያነቡላችኋል፡፡ በምታዳምጡት ምንባብ መሰረት የሚመለሱ ልዩ ልዩ ጥያቄዎችም ቀርበዋል፡፡ በመሆኑም ጥያቄዎቹን በትዕዛዛቸው መሰረት መልሱ፡፡ከዚያ በፊት ግን በቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ላይ በመወያየት የተስማማችሁበትን መልስ ለመምህራችሁ በቃል ተናገሩ፡፡

#### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

አርበኝነት ምንድነው? እንዴት ይገለፃል?

ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ከተወያያችሁ በኂላ መልሳችሁን ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡



ሥዕል 9 ፡ ኮሎኔል አብዲሳ አጋ



ሥዕል 10፡ ኮሎኔል አብዲሳ አጋ ከሌሎች አርበኞች ጋር

## ድህረ ማዳመጥ ጥያቄዎች

**፩. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ያዳመጣችሁትን ታሪክ መሰረት በማድረግ በቃላችሁ መልሱ፡፡**

ሀ. ኮሎኔል አብዲሳ አጋ የተማሩበት የጦር ትምህርት ቤት ምን ይባላል?

ለ. ኮሎኔል አብዲሳ አጋ ከፋሽስቱ የጣልያን ጦር ጋር መዋጋት የጀመሩት በስንት ዓመታቸው ነው?

ሐ. ኮሎኔል አብዲሳ አጋ የታሰሩት የት ሀገር ነው?

መ. የጣልያን ፖሊሶች ኮሎኔል አብዲሳ አጋን በእስር ቤት ውስጥ የደበደቧቸው በምን ምክንያት ነበር?

ሠ. ኮሎኔል አብዲሳ አጋ በእስር ቤት ውስጥ እያሉ እንደ አበደ ሰው የሚጮሁት ለምንድን ነበር?

ረ. ኮሎኔል አብዲሳ አጋ ከእስር ቤት ለማምለጥ የተማከሩት ሰው የየት ሀገር ዜጋ ነበር?

ሰ. የጦር አዛዡ ለኮሎኔል አብዲሳ አጋ የሸለማቸው ምንድን ነው?

ሸ. ኮሎኔል አብዲሳ አጋ ዜግነታቸውን አልቀይርም ያሉት ለምን ይመስላችኋል?

**፪. ከዚህ በታች የተሰጡት ቃላት ካዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ የተወሰዱ ናቸው፡፡ በመሆኑም በምንባቡ መሰረት ፍቺ ከሰጣችሁ በኋላ አረፍት ነገር ስሩባቸው፡፡**

ሀ. አጉላላ

ለ. ወህኒ

ሐ. ተልትለው

መ. ማጤን

ሠ. እረኛ

ረ. ዝነኛ

ሰ. ቆረጡ

ሸ. ቋጠሩ

**፫. ከዚህ በታች ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት ያደረጉ፣ በምክንያትና ውጤት ላይ የተመሰረቱ ሀሰቦች**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ከፋሽስቱ ጣልያን ጋር በጀግንነት ተዋጉ | ሀ. ከእስር ቤት አመለጡ |
| 2. ከእንግሊዝ የጦር አውሮፕላን የተወረወረ ወረቀት አንስተው በኪሳቸው ያዙ | ለ. ዝነኛ ሆኑ |
| | ሐ. ሠላሳ ሁለት ዓመት እስራት ተፈረደባቸው፡፡ |
| 3. እንደ አበደ ሰው ጮኹ | |
| 4. ብርድልብሳቸውን ተልትለው ቀጣጥለው ቋጠሩት | መ. ከእስረኞች ተለይተው ለብቻ ታሰሩ፡፡ |
| | ሠ. ወደሀገራቸው ኢትዮጵያ በክብር ተመለሱ፡፡ |

5. ከጠላት ጋር እየገጠሙ ድል አገኙ
6. አርበኞች ጀግንነታቸውን አመኑ
7. ዜግነቴን አልለውጥም አሉ
8. እስራቱ ወደ ገንዘብ ተለወጠ

ረ. ቆስለው ተማረኩ።
ሰ. ምግብ ለምነው በሉ።
ሸ. ሐኪም ቤት ተወስደው መርፌ ተወጉ።
ቀ. የአንድ ጦር ክፍል አዛዥ አደረጓቸው።

## ክፍል ሁለት፡ ንግግር

ተማሪዎች! በምትኖሩበት አካባቢ የሚኖሩ፣ ለሀገር ባበረከቱት ተግባር ታዋቂ የሆኑ ሰዎችን በመምረጥ ታዋቂ የሆኑበትን ተግባር ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ።

## ክፍል ሦስት፡ ንባብ

# የልማት አርበኛው ጄኔራል

### የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. አርበኝነት ምን ዓይነት ተግባር ነው?
2. አርበኝነትና ሀገር ወዳድነት ይመሳሰላሉ? እንዴት? በቃል አስረዱ።

ተወለዱበትና ለሚኖሩበት አካባቢ በከፍተኛ ሁኔታ የደከሙ ዜጎች መኖራቸው ጥርጥር የለውም። ለአገርና ወገን ሲታገሉ የልፋቱ፣ የድካሙና የአንግልቱ ክብደትና ቅለት እንደየሰዎቹ፣ እንደ የአካባቢያቸውና እንደ አየር ንብረቱ ቀላልና ከባድ ሊሆን ይችላል። ጥቂት ሰዎች አቅደው፣ አውጥተው አውርደው ለብዙኃን አለኝታና መከታ፣ እነርሱ ቀልጠው ለወገኖቻቸው ብርሃን፣ ለአገራቸው ቤዛ ይሆናሉ። ምን ጊዜም የትም ቦታ ለበጎ ሥራ ዕውን መሆን መስዋዕት የሆኑ ወይም የሚሆኑ አይጠፉም። ጥቂቶች በነደፉትና ተግባራዊ ባደረጉት ሥራ በርካቶች ይጠቀማሉ። በማኅበራዊም ሆነ በፖለቲካ ተሳትፎ በጎ ሰዎች ለአንድ ድርጅት መቀጠል ወይም አለመቀጠል ምክንያት ይሆናሉ። ይህንን እውነታ በተጨባጭ አብነት አስደግፎ መመልከቱ ተገቢ ነው።

በጉራጌ (በተለይ በምዕራብ ቤተ ጉራጌ)፣ በልማት ፋናወጊነታቸው አንቱ ከተባሉት ተወላጆች መካከል የልማትና የጦር ሜዳ አርበኛ የነበሩት ሌተናል ጄኔራል ወልደሥላሴ በረካ አንዱ ናቸው። ጄኔራሉ፣ በ1950ዎቹ መጀመሪያ ላይ ታቅዶ ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ የተደረገው የጉራጌ መንገዶች ሥራ ድርጅትን በመምራት ለውጤት አብቅተዋል። ለረዥም ጊዜ የጉራጌ ብሔረሰብ ራስ ምታት ሆኖ የቆየውን የመንገድ ችግር ለመፍታት ጄኔራሉና አጋሮቻቸው ያደረጉት ውጣ ውረድ እጅግ ከባድ ነበር። በዚያ ‹‹የጨለማ ወቅት›› (ከ1943 ዓ.ም. ጀምሮ) ሰባት ቤትን በመኪና መንገድ ማገናኘት እልህ አስጨራሽና ፈታኝ ትግል እንደነበር በወቅቱ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥ የነበሩ ወገኖች ያስታውሳሉ። የጉራጌ መንገዶች ሥራ ድርጅት አሃዱ ተብሎ ሥራው የተጀመረው ከወልቂጤ ወደ ሆሳዕና በሚዘልቀውና 132 ኪሎ ሜትር ርዝመት ባለው መንገድ በ1956 ዓ.ም. ነበር።

በከተማም ሆነ በገጠር በግንባር በመገኘት የመንገድን አስፈላጊነት በማሳመን ኅብረተሰቡ ሳያሠልስ ድጋፍ እንዲያደርግ ከፍተኛ የማግባባትና የውትወታ ሥራ ተሠርቷል። በዚህም ሂደት ጥቅማቸው የሚነካባቸው የመሰላቸው አንዳንድ ሰዎች የመንገዱ ሥራ እንዳይሳካ እንቅፋት በመሆን ሁከት እስከ መፍጠር ደርሰው ነበር። ይሁን እንጂ ሌተናል ጄኔራል ወልደ ሥላሴ በረካና የልማቱ ደጋፊዎች ፈተናውን ተቋቁመው የጀመሩትን የመንገድ ሥራ የሰባት ቤት ወረዳዎችን በማስተሳሰር አለመግባባቶቹን በብሔረሰቡ ባህል መሠረት ፈተዋል፤እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል እንዲሉ። የታሰበውንና የታቀደውን የልማት ስራም ዕውን በማድረግ ለውጤት ማብቃት ችለዋል፤

የጄኔራሉ የልማት ራዕይ ገደቡ ውስን አልነበረም። የጉራጌ መንገዶች ሥራ ድርጅት፣ ሰባት ቤትን በአጭር ጊዜ ውስጥ በማገናኘት በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካም ጭምር ግንባር ቀደም ድርጅት ለመሆን ችሎ እንደነበር በወቅቱ የወጡ ዘገባዎች ያስረዳሉ። የዚህ ድርጅት ጥረትና ትጋት ሌሎች ኢትዮጵያውያንም በየአካባቢያቸው ልማት እንዲያለሙ መንስዔ ሆኗል። ለአብነት ያህልም የዓለምገና-ወላይታ-ሶዶ መንገድ ተጠቃሽ ነው። የአገር መከላከያ ሚኒስቴር፣ የአውራ ጎዳና ባለሥልጣንና ሌሎችም ያደረጉት ድጋፍ እንደዘበት የሚረሳ አይደለም። ‹‹ሥራ በኅብረት ለአገር ልማት›› በሚል ብሂል በወቅቱ ዋናውን የወልቂጤ ሆሳዕና መንገድ በማስቀደም ሌሎችንም ከ500 ኪሎ ሜትር በላይ የክረምትና በጋ መንገድ ለመስራት ተችሏል።

በዚህ ሁሉ ፈታኝና እልህ አስጨራሽ የመንገድ ሥራ፣ የሌተናል ጄኔራል ወልደ ሥላሴ በረካ ሚና እጅግ ከፍ ያለ ነበር። ዛሬ፣ ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ የሚደበዝዝ ሳይሆን ፍሬው እጅግ ደምቆ የሚያበራና የሚንቦገቦግ ሥራ ሠርተውና አሻራ አሳርፈው አልፈዋል። ይህም በመሆኑ ለልፋታቸው፣ ለውጣውረዳቸው፣ ለትጋታቸውና ለጥንካሬያቸው መታሰቢያ ይሆን ዘንድ የብሔረሰቡ ተወላጆች ባደረጉት ድጋፍ በወልቂጤ ከተማ ላይ ሐውልት ቆሞላቸዋል። መንገድ የልማት ሁሉ በር ከፋች ስለሆነ እኚህ የቁርጥ ቀን ልጅ የሕዝቡን ተነሳሽነት አስተባብረው ያሠሩት መንገድ፣ ከኢትዮጵያ አልፎ በአፍሪካም ጭምር አቻ ያልተገኘለት አኩሪ የራስ አገዝ ልማት ሥራ በመሆኑ የተለየ ሥፍራ ያሰጣቸዋል፤አርአያነታቸውም ለዘለዓለም ሲወሳ ይኖራል።

(ምንጭ፦ ብርሃን ዓለሙ። 2014። ሪፖርር ጋዜጣ። ለማተማር በሚመች መልኩ ተሻሽሎ የቀረበ)

## ድህረ ንባብ ጥያቄዎች

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ምንባቡ የሚያስተላልፈው ጭብጥ ምንድን ነው? ባጭሩ ግለፁ።

ለ. በባለታሪኩ ፋና ወጊነት የተጀመረው የመንገዶች ሥራ ድርጅት የተጀመረው የት ነው?

ሐ. በምንባቡ 2ኛ አንቀጽ ደራሲው "በዚያ የጨለማ ወቅት" ሲል ምን ማለቱ ነው?

መ. ጄኔራሉ እቅዳቸው እንዳይሳካ እንቅፋት የሆኑባቸውን ፈተናዎች እንዴት ተወጡት?

ሠ. "የጄኔራሉ የልማት ራዕይ ገደቡ ውስን አልነበረም" የተባለው ከምን የተነሳ ነው?

ረ. ጸሐፊው ባለታሪኩን "የተለየ ሥፍራ ሊሰጣቸው ይገባል" ያለው በምን ምክንያት ነው?

፪. በምንባቡ መሰረት ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጡላቸው።

1. የጉራጌ መንገዶች ሥራ ድርጅት የመጀመሪያ እቅዱ የተወጠነው መቼ ነበር?

ሀ. በ1940ዎቹ ለ. በ1950ዎቹ ሐ. በ1960ዎቹ መ. በ1970ዎቹ

2. ለረዥም ጊዜ የጉራጌ ብሔረሰብ ራስ ምታት ሆኖ የቆየው ምን ነበር?

ሀ. የንጹህ ውሃ ተደራሽነት ለ. የባለሙያ እጥረት

ሐ. የመንገድ ችግር መ. የኑሮ ውድነት

3. የልማት አርበኛው፣ ሌተናል ጄኔራል ወልደሥላሴ፣ በልማት ፋናወጊነታቸው ይበልጥ አንቱ የተባሉት ከሚከተሉት በየትኛው አካባቢ ነው?

ሀ. በምዕራቡ ቤተ ጉራጌ አካባቢ ለ. በአዲስ አበባና አካባቢው

ሐ. በጉራጌ ዞን ትልልቅ ከተሞች መ. በሁሉም የጉራጌ አካባቢዎች

4. ሌተናል ጄኔራል ወልደሥላሴ በረካ ላበረከቱት አስተዋጽኦ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በብሔረሰቡ ተወላጆች ምን ተደርጎላቸዋል?

ሀ. ኒሻን ተሸልመዋል። ለ. የገንዘብ ስጦታ ተበርክቶላቸዋል።

ሐ. ሀውልት ቆሞላቸዋል። መ. በስማቸው መንገድ ተሰይሞላቸዋል።

5. በምንባቡ መሰረት የጉራጌ መንገድ ሥራ ድርጅት ውጤታማ እንዳይሆን እንቅፋት በመሆን ሁከት እስከ መፍጠር የደረሱት እነማን ናቸው?

ሀ. የመንገድን ጥቅም በውል ያልተረዱ ሰዎች ለ. ጥቅማቸው የሚነካባቸው የመሰላቸው ሰዎች

ሐ. ስንፍና የተጠናወታቸው ጥቂት ግለሰቦች መ. በስራው ለመሳተፍ ጊዜ ያጠራቸው ሰዎች

6. የተለያዩ የልማት አጋሮች ከጉራጌ የመንገድ ስራ ጋር ተባብረው በርካታ መንገዶችን በሰሩበት ወቅት ይከተሉት የነበረው መርሆ ምን የሚል ነበር?

ሀ. ድር ቢያብር አንበሳ ያስር ለ. እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል

ሐ. የጥቂቶች ጥረት ለብዙኃኑ ርካታ መ. ሥራ በኅብረት ለአገር ልማት

7. ከሚከተሉት መካከል በጉራጌ መንገዶች ሥራ ድርጅት ጥረትና ትጋት የለማው የትኛው ነው?

ሀ. የአዲስ አበባ ወልቂጤ መንገድ ለ. የዝዋይ ቡታጅራ መንገድ

ሐ. የአዲስ አበባ ጂማ መንገድ መ. የዓለምገና ወላይታ ሶዶ መንገድ

8. ከሚከተሉት መካከል ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የጉራጌ መንገድ ሥራ ድርጅት ከአገር አልፎ በአህጉር ደረጃ ፋና ወጊ ነው ማለት ይቻላል።

ለ. የጄኔራሉ የልማት ውጥንና ትግበራ እንቅፋት ገጥሞት ነበር ለማለት አያስደፍርም።

ሐ. ጥቂቶች በነደፉትና ተግባራዊ ባደረጉት ሥራ በርካቶች መጠቀማቸው የተለመደ ነው።

መ. ሌተናል ጄኔራል ወልደ ሥላሴ ከልማት አርበኝነታቸው ባሻገር የጦር ሜዳም ጀግና ናቸው።

## ክፍል አሬት: ቃላት

፩. በምንባቡ መሠረት በ"ሀ" ክፍል የተዘረዘረትን ቃላት በ"ለ" ክፍል ከተዘረዘረት ተመሳሳያቸው ጋር አዛምዱ።

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ብሂል | ሀ. ምክንያት |
| 2. ሲወሳ | ለ. ደንቃራ |
| 3. መንስዔ | ሐ. ጥረት |
| 4. እንቅፋት | መ. አድካሚ |
| 5. ሚና | ሠ. አነጋገር |
| 6. በጎ | ረ. አርአያ |
| 7. ትጋት | ሰ. መልካም |
| 8. እልህ አስጨራሽ | ሸ. ሲነገር |
| 9. ሳያሠልስ | ቀ. ድርሻ |
| 10. ፋና ወጊ | በ. በተከታታይ |

፪. ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ሀ. አለኝታ

ለ. አንቱ የተባሉ

ሐ. ውጣውረድ

መ. እልህ አስጨራሽ

ሠ. ሁከት

ረ. እንደዘበት

ሰ. አሻራ አሳርፈው

## ክፍል አምስት: ጽሕፈት

አርበኝነት በጦር ሜዳ ጀብዱ መፈጸም ብቻ እንዳልሆነ በክፍል ሶስት የቀረበው ምንባብ ያስተምረናል። በልማት፣ በስፖርት፣ በትምህርትና መሰል ዘርፎች አርበኞች (ጀግኖች) እንዳሉ መገንዘብ ይኖርብናል። እናንተም በየአካባቢያችሁ ማህበረሰብን ሊጠቅም በሚችል ስራ ብዙ ከደከሙና ጉልህ አስተዋጽኦ ካበረከቱ ግለሰቦች መካከል አንዱን/ዷን በመምረጥ ባለታሪኩን/ኳን ወይም ሌሎች ሰዎችን በመጠየቅ ስራውን/ዋን በጽሑፍ ግለጹ።

## ክፍል ስድስት:-ሰዋስው

### ተውሳከ ግስ

ተውሳከ ግስ የሚለው ቃል የግእዝ ቃል ሲሆን ተጨማሪ ማለት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ተውሳከ ግስ ማለት የግስ ተጨማሪ ማለት ሲሆን በሰዋስው አገላለጽ ተውሳከ ግስ ማለት ግስን የሚያጎላምስ ማለት ነው፡፡ ግስን የሚያጎላምሰው ደግሞ ከጊዜ፣ ከቦታ፣ ከሁኔታ፣ ወዘተ. አንጻር ነው፡፡ በቋንቋው

ውስጥ የሚገኙ የተውሳከ ግሶች በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ የተውሳከ ግስ ግብሮች

በሌሎች ቃላትና ሐረጎች ሊፈፀሙ ይችላሉ፡፡

ጌታሁን አማረ፡ ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው (1989)

፩. ከዚህ በታች የቀረቡት ተውሳከ ግሶች ናቸው፡፡ እነዚህን ቃላት ተጠቀሙባችሁ አረፍተ ነገር በመመስረት የተውሳከ ግስን ተግባር አሳዩ፡፡

ሀ. ገና

ለ. ክፉኛ

ሐ. ምንኛ

መ. ቶሎ

ሠ. እንደገና

ረ. ግምኛ

፪. ከታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙትን የአረፍተ ነገሮች ባለቤቶችና ማሰሪያ አንቀፆች ለይታችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. መምህሩ ተማሪዎችን ገሰፁ፡፡

ለ. ሰው አውሮፕላንን ሠራ፡፡

ሐ. አማርኛ ቋንቋ ኬንያ ውስጥ ይነገራል፡፡

መ. የሰው ልጅ ቋንቋን ፈጠረ፡፡

ሠ. እንስሳት መግባቢያ አላቸው፡፡

ረ. አዲስ አበባ ውስጥ ብዙ ህዝብ ይኖራል፡፡

፫. ከላይ በትዕዛዝ ሁለት የቀረቡትን አዎንታዊ አረፍተ ነገሮች ወደ አሉታዊ አረፍተ ነገሮች ቀይሩ፡፡

ምሳሌ፡- ገበሬው አዝመራውን ሰበሰበ፡፡ (አዎንታዊ አረፍተ ነገር)

ገበሬው አዝመራውን አልሰበሰበም፡፡ (አሉታዊ አረፍተ ነገር)

ተማሪዎች! አረፍተ ነገሩን አፍራሽ ያደረጉት በግሱ ላይ ከመነሻና ከመድረሻ የተቀጠሉት [አል- -ም] የተባሉት ቅጥያዎች ናቸው፡፡ በዚሁ መሰረት ከላይ በተዘረዘሩት አረፍተ ነገሮች ውስጥ በሚገኙት ግሶች መነሻና መድረሻ ላይ [አል- -ም] የተባሉትን አፍራሽ ቅጥያዎች በመጨመር ወደ አሉታዊ አረፍተ ነገር ቀይሯቸው፡፡



## የምዕራፉ ማጠቃለያ

የምዕራፍ አስር ጭብጥ በዋነኛነት ትኩረቱ አርበኝነት ነው፡፡ በምዕራፉ ትምህርት መጀመሪያ ላይ በቀረበው የኮሎኔል አብዲሳ አጋ ህይወት ታሪክ አማካኝነት የማዳመጥና  የንግግር ክሂሎች ትምህርት ቀርቧል፡፡ የምንባቡ ፍሬ ሃሳብና ዝርዝር ይዘቶች በቃል ቀርበዋል፡፡ ቃላት ካዳመጡት ምንባብ አንጻር ፍች ተሰጥቷቸው ዓረፍተ ነገር ተመስርቷል፡፡ በምክንያትና ውጤት ላይ የተመሰረቱ ሀሰቦች ተዛምደው ቀርበዋል፡፡ ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ታዋቂ ሰዎችን ህይወት ታሪክ መነሻ በማድረግ ንግግር አድርገዋል፡፡

በንባብ ትምህርት ክፍልም "የልማት አርበኛው ጄኔራል» በሚል የቀረበውን ምንባብ አንብበው ጭብጡን አስረድተው፤ የባለታሪኩን የተለየ ገድል ገልፀዋል፡፡ ለቃላት ተመሳሳይና አውዳዊ ፍችዎች ተሰጥተዋል፡፡ ተማሪዎች በአካባቢያቸው  ማህበረሰብን ሊጠቅም በሚችል ስራ ብዙ ከደከሙና ጉልህ አስተዋጽኦ ካደረጉ ሰዎች መሐከል አንዱን በመምረጥ የሕይወት ታሪኩን የተላያዩ ሰዎችን በመጠየቅ አዘጋጅተው በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ በመጨረሻም በሰዋስው የትምህርት ክፍል ስለ ተውሳከ ግስ በቀቀረበው አጭር ማስታወሻ አማካኝነት ገለጻ ተደርጎ በመልመጃነት በቀረቡት አረፍተ ነገሮች  አማካኝነት የተውሳከ ግስን ተግባር ለማሳየት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም አረፍተ ነገር አፍራሽ ለማድረግ የሚረዱ በግሱ መነሻ እና መድረሻ ላይ ስለሚገቡት ቅጥያዎች ማብራሪያ ተሰጥቶ አዎንታዊ አረፍተ ነገሮች ወደ አሉታዊ አረፍተ ነገሮች ተቀይረው እንዲቀርቡ ሆኗል ፡፡



### የክለሳ ጥያቄዎች

1. የኮሎኔል አብዲሳ አጋ አስደናቂ ገድሎች ምንምን ናቸው?
2. ሌተናል ጄኔራል ወልደሥላሴ በረካን ልዩ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው?
3. የሁለቱ ታዋቂ ሰዎች የጀግንነት ተግባር ተመሳሳይ ነው?
4. ጀግንነት በምን በምን መስኮች ይገለጻል? በምሳሌ አስረዱ፡፡
5. ተውሳከ ግስን ከሌሎች የቃል ክፍሎች የሚለየው ምንድነው?

## ክፍል ሰባት፡- የግንዛቤ ማጠሳከሪያ ነጥቦች

ከዚህ በታች በምዕራፉ የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች ምን ያህል እንደተረዳችኋቸው ለማረጋገጥ የሚረዱ ማጠሳከሪያ ነጥቦች ተዘርዝረዋል፡፡ በመሆኑም ዝርዝሮቹን በጥንቃቄ በማንበብ፤ ተረድታችኋቸው ከሆነ ከፊትለፊታቸው ባለው ሳጥን ውስጥ የ(V) ምልክት በማድረግ አረጋግጡ፡፡ ያልተረዳችሁት ወይም የሚያጠራጥራችሁ ከሆነ ግን በሳጥኑ ውስጥ የ (?) ምልክት በማድረግ ያልተረዳችኋቸውን ነጥቦች ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

| ተ.ቁ | ማመሳከሪያ ነጥብ | (√) | (?) |
|---|---|---|---|
| 1 | ያዳመጥሁትን ምንባብ መልዕክት ተረድቻለሁ፡፡ | | |
| 2 | ካዳመጥት ምንባብ ዝርዝር መረጃዎችን አውጥቻለሁ፡፡ | | |
| 3 | በመረጥሁት ርዕሰ ጠቃሚ ውይይት አድርጌያለሁ፡፡ | | |
| 4 | ያነበብሁትን ምንባብ ጭብጥ በቃል አስረድቻለሁ፡፡ | | |
| 5 | ለቃላት ተመሳሳይ እና አገባባዊ ፍች ሰጥቻለሁ፡፡ | | |
| 6 | በመረጥሁት ርዕስ ትክክለኛ ድርሰት ፅፌያለሁ፡፡ | | |
| 7 | ከአረፍተ ነገር ውስጥ ስማዊ ሀረጎችን እና ግሳዊ ሀረጎችን ለይቼ አውጥቻለሁ፡፡ | | |
| 8 | ከአረፍተ ነገር ውስጥ ተውሳከ ግሶችን ለይቼ አውጥቻለሁ፡፡ | | |
| 9 | አዎንታዊ አረፍተ ነገሮችን ወደአሉታዊ አረፍተ ነገር ቀይሬያለሁ፡፡ | | |
| 10 | አሉታዊ አረፍተ ነገር እንዴት እንደሚመሰረት ተረድቻለሁ፡፡ | | |

# ፈሊጣዊ አነጋገሮች እና ተረትና ምሳሌዎች

## ተረትና ምሳሌዎች ከነፍቻቸው

| ተረትና ምሳሌዎች | ፍቻቸው |
|---|---|
| መንገድ ለቀደመ ውሀ ለገደበ | ሰው የእጁን ያገኛል |
| መቼ መጣሽ ሙሽራ ምን ቆረጠምሽ ሽምብራ | መቸኮል ክብርን ያሳንሳል |
| መንገድ ሳለ በዱር በቅሎ ሳለ በእግር | መልካሙን ነገር ማስቀደም ተገቢ ነው |
| መርፌ የራሷን ቀዳዳ ሳታይ የሰው ቀዳዳ ትሸፍናለች | ለራስ ሳይሆኑ ለሌላ ሰው መሆን፣ቅድሚያ የራስን ችግር መፍታት ተገቢ ነው |
| ሙቅ ውሃና የሰው ገንዘብ አይጠቅምም | በራስህ ኩራ፣ በጊዜያዊ ደስታ አትታለል |
| ሚስት ከፈቷት ባዳ፣ ማሽላ ከቆረጡት አገዳ | ሁሉም ነገር በቦታው እስካለ ብቻ |
| ሚዳቋ ዘላ ዘላ ከምድር | ዞሮ ዞሮ እዚያው |
| ማን ይናገር የነበረ፣ ማን ያርዳ የቀበረ | ያየ የሰማ ይናገር፣ ትክክለኛ ምስክርነት |
| ማቅ ይሞቃል፣ ሻሽ ያደምቃል | ለሁሉም ሙያ አለው፤ ሁሉም በቦታው ሲሆን ያምራል |
| ማሩን አምርሮ፣ ወተቱን አጥቁሮ | ሀቁን አዛብቶ፣ ውሸት አቀናብሮ |
| ማሽላ ለማሽላ ተያይዞ ቆላ | የማይረባ፣ የተሻለ የሌለው |
| ማሽላና ዘንጋዳ መከታና ጓዳ | ተስማሚ፣ የሚስማሙ |
| ማጣትና ማግኘት እልፍኝና ማድቤት | የሚቃረኑ ነገሮች፣ ልዩነታቸው ሰፊ ነው |
| ማን አለ መርማሪ አለ ፈጣሪ | የሰውን ልብ ከፈጣሪ በቀር ማንም አያውቅም፣ የልብ አውቃ |
| ሜዳ መራመድ ሳታውቅ፣ መሰላል መውጣት ማን አስተማራት | ቀላሉን ነገር መስራት ሳይችሉ ከባዱን ስራ መመኘት፣ አጉል መንጠራራት፣ |
| ምን ቢያርሱ እንደጎመን አይጎርሱ | ውድ ያልሆነ ነገር አያንስም |
| ምን ብቀጥን ጠጅ ነኝ | ቀጭን ብሆንም ጠንካራ ነኝ፣ጠላትህን አቋሙን አይተህ አትናቅ |
| ምንም ቢከፋ ዘመድ ምንም ቢጠብ መንገድ | ከህጉ አትውጣ፣ እውነትን ተከተል |
| ምን ብታውቅ ከዳኛ ጋር አትሟገት | አስተውል |
| ምላጭን ምላጭ አይቆርጠውም | ሌባን ሌባ አያታልለውም |
| ምጥ ለእናቷ አስተማረች | አግባብ ያልሆነ ተግባር፣ ፍፁም ውሸታም ሰው |
| ሰርቆ ከማሰብ እጅን መሰብሰብ | በኋላ ከመፀፀት አስቀድሞ መጠንቀቅ |
| ሰምቶ ዝም አይቶ ዝም | ትዕግስተኛ መሆን |
| ሲበሉ የላኩት | የማያስተውል ፤ ዝንጉ |

| ተረትና ምሳሌዎች | ፍቻቸው |
| --- | --- |
| ሲያረጁ አምባር ይዋጁ | ያለወቅቱ መመኘት፣ ያለፈን ነገር መመኘት፣ ያለዕድሜህ አትመኝ |
| ሲሞቱ ገመድ፣ ሲገዙ ዘመድ አይታጣም | ሰው ሲሾም(ስልጣን ሲያገኝ) ዘመድ ነኝ የሚል ይበዛል |
| ሳይቃጠል በቅጠል | ልጅን በጡት፣ ችግርን በወቅቱ መፍታት ቀላል ነው |
| በቤቷ ቀጋ በውጭ አልጋ | እቤትዋ አመለ መጥፎ፣ ለቤት (ለባሏ) የማትመች፣ ከቤት ውጭ ግን ጥሩ መሳይ |
| ዝም ባለ አፍ ዝንብ አይገባም | ዝምታ ያሥከብራል |
| በጨለማ ቢያፈጡ፣ በደንቆሮ ቢቆጡ | ለማይሻሻል መምከር ትርፉ ድካም ነው |
| ለልጅ ከሳቁለት ለውሻ ከሮጡለት | ለሞኝ ፊት ካሳዩት ከልኩ ያልፋል፣ ቀልድ ስራን ያበላሻል |
| ሳይጠሩት አቤት፤ ሳይልኩት ወዴት | ሳይፈልጉት፣ ሳይታዘዝ የሚመጣ፣ የሚቀላውጥ |
| የተቸገረ ዱቄት ከንፋስ ይጠጋል | የተቸገረ እርጉዝ ያገባል፣ መፍተሄ ሲታጣ መጥፎ ነገርም ይመረጣል |
| ለወዳጁ ማር ለጠላቱ አሜከላ | ለወዳጁ ደግ፣ ለጠላቱ የማይበገር፣ ጀግና፣ ጎበዝ ሰው |
| ሸማ በየፈርጁ ይለበሳል | ሁሉንም በትክክለኛ ቦታው ማዋል ይገባል |
| ቂል ሲረግሙት የመረቁት ይመስለዋል | ቀልድና ቁም ነገር የማይለይ፣ የማያስተውል |
| የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል | ያለመስማማት መጥፎ ውጤትን ያስከትላል |
| አፍንጫን ቢመቱት ዐይን ያለቅሳል | ዘመዳም ናቸው፣ ለወገን ደራሽ ወገን ነው፣ ሰው ለወገኑ ያግዛል |
| የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል | የችኮላ ስራ ውጤታማ አያደርግም፣ ተረጋግቶ መስራት ከስህተት ያድናል |
| ከአጋም የተጠጋ ቁልቋል ዘላለም ያለቅሳል | ከክፉ ሰው ጋር የሚኖር ምቾት የለውም፣ ዘወትር ይጠቃል |
| ሳይገሉ ጎፈሬ ሳይዘምቱ ወሬ= | ያልሰሩትን ሥራ ሰራሁ ማለት ያስንቃል፣ ከወሬ ስራ ይቀድማል |
| ሾላ በድፍን | የማይታወቅ፣ ምስጢሩ ግልጽ ያልሆነ |
| የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ | ሁልጊዜ ስኬት የለም፣ እንደተለመደው አይኖርም |
| እህል ላበደረ አፈር፣ ወርቅ ላበደረ ጠጠር | ደግ ላደረገልህ ክፉ መመለስ፣ ውለታ ቢስ መሆን |

# ፈሊጣዊ አነጋገሮች እነፍቻቸውቸው

| ፈሊጣዊ አነጋገሮች | ፍቻቸዉ |
|---|---|
| ክንፉን ጣለ | በጣም አዘነ፣ ደከመ |
| በቅሎዋ ተሸለመች | ለግልቢያ ዝግጁ ሆነች፣ ኮርቻ ተጫነች |
| የቀኝ ክንድ | በጣም የቅርብ ጓደኛ፣ አጋዥ |
| እኔን ክንብል ያድርገኝ | ለሰው ከልብ ማዘን፣ ያንተን ሞት ለኔ ይስጠኝ |
| ነገሬን ከተተው | ገመናዬን ሸፈነልኝ፣ የልቤን ብሶት ደበቀው |
| ለዐይን የሚከብድ ሰው | ግርማ ሞገስ ያለው |
| የዱር ክብር | አዝመራ |
| ተከሽና መጣ | ተውቦ፣ ተሸሽሎ መጣ |
| ፊቱ ከሰለ | ተናደደ፣ ተበሳጨ፣ ጠቆረ |
| የጠጣ ግንባር | በጣም ጠባብ፣ ትንሽ፣ የማይበቃ (ለቦታ) |
| ከርሞ ጥጃ | የማይሻሻል፤የማያድግ፣ ከአመት አመት ለውጥ የሌለው |
| እፍ እፍ አለ | ልታይ ልታይ አለ፣ እወቁኝ እወቁኝ አለ |
| እግረ እርጥብ | እድላም፣ የሚሳካለት |
| እግረ ደረቅ | የማይቀናው፣ እድል የሌለው |
| እጅህ ከምን | ምን ይዘሀል፣ ምን ትሰጠኛለህ |
| ከጅ በጉንጩ | ከሩቅ ካለ በቅርብ ያለ ይጠቅማል |
| እጄን ተቆረጥኩ | ልጄን፣ረዳቴን አጣሁ (በሞት) |
| እጀ ብልህ | ስራ አዋቂ |
| እጀ ሰብ | የሰው ማጥፊያ መድሀኒት |
| እንጀራ በሬው | ስስታም፣ ለትንሽ ነገር የሚጨነቅ |
| እንደ ፍጥርጥሩ | እንደለመደው፣ ራሱ በለመደው መንገድ ያድርግ |

| ፈሊጣዊ አነጋገሮች | ፍቻቸዉ |
|---|---|
| እርም ታህል | በጣም ትንሽ |
| አፍህ ይረፍ | አትናገር፣ ዝም በል |
| ታፍ ታፍ (ከአፍ ከአፍ) | ሳይበዛ፣ ሳይጠራቀም፣ ወዲያው ወዲያው (ለነገር) |
| አመድ አፋሽ | ውለታ ቢስ፣ ሰርቶ እንዳልሰራ መሆን |
| አፈር መለሰ | ቀበረ (ለሬሳ) |
| የአገር ቀንድ | በሀገር የታወቀ ሰው (የሀገር ሽማግሌ) |
| ወግ ጠርቅ | ብዙ የሚያወራ፣ ወሬኛ |
| እንቶ ፈንቶ | ተራ ነገር፣ የማይረባ |
| የፍንጥር | ሰዎች እንስሳትን ከተገበያዩ በኋላ በሻጭ እና በገዥ መካል የሚጠጣ መጠጥ |
| ገበያው ተፈታ | ገበያው አበቃ፣ ተበተነ |
| ገበያው ቆመ | ገበያው ተጀመረ |
| ገበያው ደራ | ገበያው ደመቀ፤ ተሟሟቀ |
| ቅቤ ጠባሽ | አስመሳይ ፤ አታላይ |
| ጥቁር እንግዳ | መጥቶ የማያውቅ ሰው፤ እንግዳ፤ ጉንዳን |
| አገም ጠቀም | ያዝ ለቀቅ፣ ወጥነት የሌለው ተግባር |
| ስም አይጠሩ | እባብ |
| አጣማጅ | የትዳር ጓደኛ |
| አውላላ ሜዳ ላይ መተው | ያለድጋፍ፣ ያላአጋዥ፣ በባዶው ማስቀረት |
| ግብረ በላ | አዘውትሮ የሀብታም ድግስ የሚበላ |
| ግልገል ሚዜ | ሁለተኛ ሚዜ |
| ሥር ሚዜ | አንደኛ ሚዜ |

| ፈሊጣዊ አነጋገሮች | ፍቻቸዉ |
|---|---|
| ለጌታ አደረ | ለሀብታም አገልጋይነት ገባ |
| በአግቦ | በአሽሙር መናገር |
| ገበያ ነች | ቻይ ፤ሆደ ሰፊ |
| ገምጠ ወጥ | በልቶ የሚሄድ፣ መረን፤ ስርዓት የሌለው |
| ገመና ከታች | ሚስጢር ጠባቂ፤ ለችግር ደራሽ |
| ልቡ ተሰበረ | በጣም አዘነ |
| የመከራ በትር | መሪር ሐዘን |
| መሬት ላሰ | ተለማምጠ፣ ለመነ |

(ምንጭ፤ ደበበ ኃይለጊዮርጊስ፡ 2007፤ቅድመ ኮሌጅ አማርኛ)